# ከ 1ኛ ክፍል እስከ 4ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የመንገድ ደህንነት ግንዛቤን ለማዳበር የተዘጋጀ መማሪያ /ማጣቀሻ፣ አጋዥ መጽሐፍ/ ካሪኩለም ጋይድ

## መቅድም

መጽሐፉ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች የመኪና መንገድ አጠቃቀም ስርዓትን ሲማሩ በየደረጃው ሊያዳብሯቸው የሚችሉት የህይወት ክህሎቶች ምን ምን እንደሚሆኑ እንዲያመለክት ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን፣ የስርዓተ ትምህርቱ መመሪያው የየክፍሉን ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት መምህራኑንም ሆነ ሌሎችን የመጽሐፉን ተጠቃሚዎች እንዲያግዝ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

አንድ ትምህርት ሲሰጥ ያን ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎች ይደርሱበታል ተብሎ የሚታሰብ ግብ ይኖራል። ይህ ግብ በአጠቃላይ ዓላማዎች ስር በተወሰነ መጠን የሰፈረ ሲሆን፣ ከዚያ በላቀና በበለጠ መልኩ ከሚያደርጉት ተግባራዊ ትምህርት ሊያዳብሩት እንደሚችሉ ይታመናል።

በኢትዮጵያ ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት በ1996 ዓ.ም. በተዘጋጀው ከ1ኛ-4ኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ እና የኤስቴቲክስና ሰውነት ማጎልመሻ ስርዓተ ትምህርት (ካሪኩለም ጋይድ) መሠረት ተማሪዎች በተዘጋጀላቸው መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ስለመንገድ አጠቃቀም ስርዓትና የመንገድ ላይ አደጋዎች እንዴት ማስወገድ እንደሚችሉ መሠረታዊ የሆነ ትምህርት እንዲካተት ተደርጓል።

በትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤት ስር በተቋቋመው በብሔራዊ መንገድ ደህንነት አስተባባሪ ጽ/ቤት አማካኝነት በተዘጋጀው በዚህ ማጣቀሻ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ነጥቦች በኢንስቲትዩቱ የተቀረፁትን የመንገድ አጠቃቀም ትምህርቶች የሚያዳብሩና የሚያጎለብቱ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ ነው። በመሆኑም፤ በየክፍሉ በመጨረሻ ላይ ተዘጋጅተው የቀረቡት የትምህርቱ አጠቃላይ ዓላማዎች፣ ዝርዝር ዓላማዎች፣ የማስተማር መማር ዘዴዎች፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ የክትትልና ግምገማ ስርዓቱ ከላይ ከተጠቀሰው ኢንስቲትዩት ካሪኩለም ጋይድ በከፊል ሲወሰድ፣ ይህ መጽሐፍ ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎች እንዲሁም ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያገለግል በመሆኑ ማጣቀሻነቱን መሠረት በማድረግ ሰፊና ዘርዘር ብሎ እንዲቀርብ ተሞክሯል።

በትምህርቶቹ ውስጥ በተካተቱት መልኩ፣ የመንገድ አጠቃቀም ትምህርት የሚሰጥ ከመሆኑ በተጨማሪ፣ በመንገድ ደህንነት መስሪያ ቤትና በት/ቤቶች አማካኝነት የትራፊክ ትምህርት ክበባት በየትምህርት ቤቶቹ እየተቋቋሙ በመሆኑ ክበባቱ ይህን መጽሐፍ በመጠቀም የክበቡን አባሎችም ሆኑ ሌሎች ተማሪዎችን ሲያስተምሩ እንዲገለገሉበት ጭምር ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

"ካሪኩለም ጋይድ" አቅጣጫ መሪ እንጂ የመጨረሻውን ነጥብ አሟጦ አመላካች ባለመሆኑ፣ መምህራንም ሆኑ የትራፊክ ክበብ አባላትን የሚያስተምሩ አካላት የራሳቸውን ፈጠራ እና ግንዛቤ በማከል ትምህርቱን በሚጥም፣ ግልጽ እና ግብ መቺ በሆነ መልኩ እንዲቀርብ የማድረግ ሙያዊ ኃላፊነት እንደሚኖርባቸው የሚዘነጋ አይሆንም።

**አዘጋጁ**

## ማውጫ


**መጽሐፍ ክፍል አንድ** **ገፅ**

1. በአካባቢያችን ያሉ ነገሮች
2. ሰዎች ለመጓጓዣ አገልግሎት የማጠቀሚቸው ነገሮች
   1.1 ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች
   1.2 ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች
3. ጥቅም የሚሰጡ ነገሮች ጉዳትንም ሊያስከትሉ ይችላሉ
4. አደጋ የሚያደርሱ ነገሮች
5. ስነስርዓትን መያዝ የሚሰጠው ጥቅም
6. የአካባቢያችን አንፃራዊ መገኛ
7. የመንገድ ላይ አደጋዎች
8. የመኪና መንገድ ስናቋርጥ መውሰድ ያለብን ጥንቃቄ
9. የመንገድ ላይ የትራፊክ መብራት ጠቀሜታ
10. ድራማ፡- አለማመዛዘን ያስከትላል ሀዘን
11. ድርሩጮ
12. መከለሻ ጥቅል ሃሳቦች

**መጽሐፍ ክፍል ሁለት**

1. በመኪና መንገድ ላይ የሚታዩ ነገሮች
2. የመርካቶው አደጋ
3. በተሽከርካሪ ነገሮች የሚደርሱ አደጋዎች
4. መኪናዎች አደጋ የሚያደርሱባቸው ምክንያቶች
5. መንገድ ስንጠቀም መውሰድ የሚገባን ጥንቃቄ
6. ድራማ፡- የመኪና መንገድ ላይ የእግር ኳስ ጫወታ
7. መኪና በምንጠቀበት ወቅት መውሰድ ያለብን ጥንቃቄ
8. የደህንነት ቀበቶ ማሰር የሚኖረው ጠቀሜታ
9. የእሽቅድምድም ጨዋታ
10. የጠንቃቃ ልጅ ተግባር

**መጽሐፍ ክፍል ሦስት**

1. እግረኞች በመንገድ አጠቃቀም ማወቅ የሚገባቸው ነገሮች
2. አደጋዎችን ለመቀነስ ምን ማድረግ ይኖርብናል
3. ተሽከርካሪዎችና ዓይነታቸው
4. የመንገድ ላይ ተጠቃሚዎች
5. የመንገድ ላይ ትራፊክ ማለት ምን ማለት ነው?
6. ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ለራሳችን ብቻ ነውን?
7. የመጓጓዣ ዓይንቶችና ጠቀሜታቸው
8. የመኪና አደጋ የሚደርስባቸው ዋነኛ ምክንያቶች
9. ትራንስፖርት ለንግድ መስፋፋት የሚኖረው እገዛ
10. በት/ቤቶች አካባቢ ሊወሰድ የሚገባ ጥንቃቄ
11. ከቤና ጓደኞቹ
12. በመኪና ስንጓዝ ቀድመን ማሟላት የሚገባን ጥንቃቄ
13. በመኪና በምንጓዝበት ወቅት መወሰድ የሚገባን ቅድመ ጥንቃቄ
14. አሽከርካሪዎች መከተል ያለባቸው የጥንቃቄ ደንቦች

15. እግረኞች መከተል ያለባቸው የጥንቃቄ ደንቦች__________________
16. ባለሁለት አቅጣጫ መንገድን ስንጠቀም ማድረግ ያለብን ጥንቃቄ_________
17. የአስተዋይነት ጠቀሜታ ______________________________

**<u>መጽሐፍ ክፍል አራት</u>**

1. የተሽከርካሪዎች አጀማመር አጭር ታሪክ______________________
2. ተሽከርካሪዎች ወደ ኢትዮጵያ መግባት የጀመሩት መቼ ነው ___________
3. የመንገድ ላይ ምልክቶች ጠቀሜታ ______________________
4. የትራፊክ ምልክቶች ምን ያስገነዝቡናል _____________________
5. የመንገድ ላይ ምልክቶች______________________________
6. የመንገድ እና የትራፊክ ምልክቶችን አክብሮ መጠቀም ______________
7. የመመልከት እና የማዳመጥ ችሎታን ማዳበር __________________
8. የህፃናት የማየት ወይም የማዳመጥ ችሎታ የዳበረበት መጠን __________
9. ህፃናት የማየትና የመስመት ችሎታቸውን ለማዳበር ማድረግ ያለባቸው ___
10. ቆርጠን ተንስተናል (መዝሙር)____________________________
11. ብቻችሁን መንገድ ስታቋርጡ ማወቅ የሚገባችሁ__________________
12. መከተል የሚገባቸው የትኩረት ነጥቦች______________________
13. አውራ ጐዳናዎችና መጋቢ መንገዶች ያላቸው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ______
14. የመንገድ ጠቀሜታ _________________________________
15. የትራንስፖርት ዓይነቶች ____________________________
16. ብስክሌት የሚሰጠው የትራንስፖርት ጠቀሜታ __________________
17. አርቆ የሚመለከት ካሰበበት ይደርሳል _______________________

# መ ግ ቢ ያ

ሰዎች በትራንስፖርት መገልገያዎች በመጠቀም የእርስ በርስ ግኙነታቸውን ከማጠናከራቸውም በተጨማሪ አንዱ ያመረተውን ሌላው እንዲገለገልበት በማድረግ ኢኮኖሚያቸውን እንዲያዳብሩ ጠቀሜታ ይሰጣል፡፡

ከተለያዩ የትራንስፖርት አውታሮች አንዱ የሆነው የየብስ ትራንስፖርት ሲሆን፣ 90% የአገራችን የሰውና የጭነት እንቅስቃሴ የሚስተናግደው በመንገድ ትራንስፖት መሆኑ ይታወቃል፡፡

የመንገድ ትራንስፖርት የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ቢሆንም በአሽከርካሪዎች፣ በተሽከርካሪዎች፣ በእግረኞች፣ በመንገድ እና በሌሎች ምክንያቶች መንስኤነት የመንገድ ላይ አደጋዎች እንደሚከሰቱ ይታወቃል፡፡

በአገራችን አሳሳቢ በሆነ መጠን የመንገድ ላይ አደጋዎች ይደርሳሉ፡፡ ከ1990 እስከ 1994 ድረስ የደረሰውን አደጋ በመተንተን በብሄራዊ የመንገድ ደህንነት አስተባባሪ ጽ/ቤት በወጣው ጥናት መሰረት የመኪና አደጋ በአማካይ በየዓመቱ ከ2,000 ሰዎች በላይ ህይወታቸውን እንደሚያጡ፣ ከ8,000 በላይ ሰዎች ደግሞ የአካል ጉዳት እንደሚደርስባቸውና እስከ 500 ሚሊዮን ብር የሚሆን የአገሪቱ ሀብት እንደሚወድም ያሳያል፡፡

በአደጋ ከሚሞተው ሰው ከመቶ 48 ያህሉ በመኪና መንገድ ተጠቃሚ የሆነው እግረኛ ሲሆን 45 ከመቶው በመኪና ተሳፍረው ሲጓዙ አደጋ የሚደርስባቸው እና 7 ከመቶው አሽከርካሪዎች ናቸው፡፡

የተሽከርካሪዎች ቁጥር እየበዛ መሄድ በዚሁ ከቀጠለ የጉዳቱ መጠን ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ሁኔታው አሳሳቢ ነው የሚባለው በነዚህ ምክንያቶች የተነሳ በመሆኑ፣ ሁሉም ወገን የመንገድ ላይ አጠቃቀም ስርዓትን በተገቢው መንገድ በመጠቀም የሚደርሰውን አደጋ በእጅጉ ለመቀነስ መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡

በዚህ በአራት ክፍሎች በተከፈለ፣ የመንገድ አጠቃቀም ስርዓትና ደንብ ማስገንዘቢያ መጽሐፍ የመንገድ ላይ አደጋን በእጅጉ ለመቀነስ እግረኞች ማድረግ ያለባቸው ጥንቃቄ ምን መሆኑን እንዲያውቁ በማድረግ እንዴትና በምን ሁኔታ አደጋ እንደሚደርስ በማወቅ አደጋን ለመቀነስ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ግንዛቤ ያስጨብጣል፡፡

ይህ መጽሐፍ በትምህርት ገበታ ላይ ለሚሳተፉ ህፃናት ግንዛቤ ማስፍያ የሚሆን የማጣቀሻ ምንጭ ተደርጐ እንዲወሰድ ታስቦ የተዘጋጀ ቢሆንም፣ አዋቂዎችም ቢያነቡት ምልከታውን ሊያጠናክሩላቸው የሚያስችሉ ነጥቦችን የያዘ ሲሆን፣ ልጆቻቸው ምን ዓይነት የመንገድ አጠቃቀም ስርዓት መከተል እንደሚገባቸው በማሳወቅ ለሚሰጡት ትምህርት አጋዥ ሊሆናቸው ይችላል፡፡

ህፃናት ትልልቅ ሰዎች የሚያደረጉትን እያስመሰሉ በመስራት የታላላቆቻቸውን ልምድ የሚቀስሙ በመሆኑ አዋቂዎች ልጆቻቸውን ይዘው በሚጓዙበትና መንገድ በሚያቋርጡበት ወቅት ተገቢውን የመንገድ አጠቃቀም ስርዓቶችን መከተል ይገባቸዋል፡፡

ትክክለኛ የሆነ ተግባር እያዩ የሚያድጉ ህፃናት፣ ትልልቅ ሰዎች በሚሆኑበት ወቅት ይህን የተስተካከለ ልምድ ይዘው እንደሚቀጥሉ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡

ወላጆች ተገቢውን የመንገድ አጠቃቀም አውቀው እነሱ እየተገበሩ ልጆቻቸው ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እያስተማሯቸው ከዘለቁ መንገድን የአደጋ ምንጭ ሳይሆን ጠቃሚታው የጐላ የህብረተሰቡ መልካም የኑሮ አጋዥ ነገር ማድረግ ይቻላል፡፡

የብሔራዊ የመንገድ ደህንነት ማስተባበሪያ በአገራችን እየደረሱ ያሉ የመንገድ ላይ አደጋዎችን ለመቀነስ ብሎም ለማስቀረት በርካታ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል፡፡

**የእግረኞችን አደጋ ለመከላከል ከሚያደርጋቸው ጥረቶች ውስጥ ሊጠቀሱ የሚችሉት፡-**

- የፍጥነት መቆጣጠሪያ ራዳሮችን በመንገዶች ላይ በመጠቀምና እና ሁኔታውን በመከታተል ለአሽከርካሪዎች ትምህርት መስጠት፣
- በየክልሉ በተቋቋሙት ጽ/ቤቶች አማካኝነት የተለያዩ ሴሚናሮችን እና ስብሰባዎችን ለአሽከርካሪዎችና ለትራንስፖርት ማህበራት በመስጠት ግንዛቤን ማዳበር፣
- የመገናኛ ብዙሃኖችን በመጠቀም ህዝቡ የመንገድ አጠቃቀም ደንቦችን እንዲያውቅ ማድረግ፣
- በት/ቤቶች ደረጃ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ክበባት እንዲቋቋሙ በመንቀሳቀስ፣ ተማሪዎች ተግባራዊ ግንዛቤያቸውን እንዲያዳብሩ ሁኔታዎችን እያመቻቸ ይገኛል፡፡

ተማሪዎች ያላቸውን የመንገድ አጠቃቀም ግንዛቤ ለማዳበር እንዲረዳ ማስተባበሪያው ይህ መጽሐፍ እንዲዘጋጅ ሲያደርግ ሁለት ዋነኛ ታሳቢ ምክንያቶች አሉት፡፡

1ኛ. አደጋ ከሚደርስባቸው ወገኖች አንዱ ተማሪው በመሆኑ በቂ ግንዛቤ በማስጨበጥ ተማሪዎች ከአደጋ የተጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግ፣

2ኛ. በተደራጀ መልክ በት/ቤቶች የሚሰጡ የመንገድ ደህንነት ትምህርቶች የተማሪዎችን ግንዛቤ ሊያዳብር የሚችል ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ወጣቶች አድገው የነገ አሽከርካሪ በሚሆኑበት ወቅት ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ዝንባሌያቸው የዳበረ እንዲሆን ሊያግዛቸው ይችላል፣ ለቤተሰባቸውም የተሻለ የመንገድ አጠቃቀም ግንዛቤ ያስተምራሉ በሚል እምነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

በብሔራዊ የመንገድ ደህንነት አስተባባሪ ጽ/ቤት አማካኝነት በባለሙያ እንዲዘጋጅ የተደረገው መጽሐፍ ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ያሉ በየትምህርት ቤቱ የሚገኙ ተማሪዎች በዋናነት እንዲጠቀሙበት የታሰበ ሲሆን መጽሐፉ በየርዕሱ ስር የተግባር ጥያቄዎች ያሉት በመሆኑ መምህራን ወላጆችና ግንዛቤ ያላቸው ሁሉ በተግባር ከተማሪዎች ጋር በመስራት ዓላማውን የተሳካ እንዲያደርጉ ትብብራቸው ይጠየቃል፡፡

# መጽሐፍ ክፍል አንድ







መልዕክት፦ <u>የመኪና አደጋን ለመቀነስ በአንድነት እንነሳ</u>

## 1. በአካባቢያችን ያሉ ነገሮች

በአካባቢያችን የተለያዩ በርካታ ነገሮች ይገኛሉ። እንደምንኖርበት አካባቢ የምናያቸውም ነገሮች የተለያዩ ናቸው። ህፃናት አካባቢያቸውን ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጐት እንዳላቸው ይታወቃል። በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን በመጠቀም መጫወት፣ አካባቢያቸውን መፈተሽ፣ ሁሉን ነገር መሞከር ይወዳሉ። የሚያደርጉት ጫወታ እንደ አካባቢያቸው ሁኔታ የሚወሰን ነው። በገጠር አካባቢ እና በከተማ ውስጥ የሚኖሩ ልጆች የተለያዩ ዓይነት ጫወታዎች ይጫወታሉ።

ሰዎች አካባቢያቸውን መገንዘብ ከቻሉ አደጋ በማያስከትል ሁኔታና በተገቢው መልኩ በአካባቢያቸው ያሉትን ነገሮች በመጠቀም ህይወታቸውን ደስተኛ ሊያደርጉት ይችላሉ፤ ነገር ግን አካባቢያቸውን በበቂ ሁኔታ የመገንዘብ እና አካባቢያቸው የሚፈልግባቸውን ስርዓት አክብረው የመተግበር ግንዛቤው በኑሮ ሂደት ውስጥ ወይም በትምህርት የሚያካበቱት ስለሆነ ህፃናት በዚህ ላይ አቅም (ችሎታ) ይጐድላቸዋል።

በአካባቢያችን አደጋ የማያደርሱ ነገሮች ያሉትን ያህል፣ አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮችም አሉ። በከተሞች ውስጥ በአካባቢያችን ጐልቶ የሚታየው አደጋ የሚያስከትል ነገር የመኪና አደጋ በመሆኑ ህፃናት ይህንኑ ተገንዝበው ራሳቸውን ከአደጋ መጠበቅ አለባቸው።

በገጠር አካባቢዎች፣ ድልድይ የሌላቸው ወንዞች እና ተመሳሳይ ነገሮች ህፃናት ላይ አደጋ የሚያደርሱባቸው ሁኔታዎች ስለሚኖሩ ህፃናት በወንዞች፣ በእንስሳት... ወዘተ አደጋ እንዳይደርስባቸው ማድረግ የሚችሉት አካባቢያቸውን ተገንዝበው መንቀሳቀስ ሲችሉ ነው።

ስለዚህ ቀዳሚው የሰው ልጅ ትምህርት አካባቢውን መገንዘብ መቻል ነው። አካባቢያችንን ተገንዝበን፣ ከአካባቢያችን ካሉ ነገሮች የትኞቹ፣ እንዴት እና መቼ አደጋ ሊያደርሱብን ወይም ላያደርሱብን እንደሚችሉ አውቀን መንቀሳቀስ ከቻልን በአካባቢያችን ተጠቅመን ይበልጥ ደስተኛ ልንሆን እንደምንችል ልንገነዘብ ይገባል።

አንድ ሁኔታ ውስጥ ዝም ብለን ከመግባታችን በፊት ወይም ምንም ተግባር ከመፈፀማችን በፊት አካባቢያችን ምን እንደሚመስል መገንዘብ ይኖርብናል። ከምን ነገሮች ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባንና ትኩረት መስጠት ያለብን ለምን ነገር መሆን እንደሚገባው ታላላቆቻችንን ወይም ወላጆቻችንን በመጠየቅ ስለ አካባቢያችን ያለንን ግንዛቤ ማስፋት ይጠበቅብናል።

**<u>የተግባር ጥያቄ</u>**
**<u>መልሳችሁን ለጓደኞቻችሁ፣ ለወላጆቻችሁ ወይም ለመምህራኖቻችሁ ግለፁ</u>**

1. በምትኖሩበት አካባቢ የምታስተውሏቸው ምን ምን ነገሮች አሉ?
2. በአካባቢያችሁ ካሉ ነገሮች አደጋ የሚያስከትሉ እና አደጋ የማያስከትሉ ነገሮች ምን እንደሆኑ ዘርዝራችሁ ግለፁ?
3. አካባቢያችንን ቀድመን ማወቅ ምን የሚሰጠን ጠቀሜታ ይኖራል?
4. አደጋ እና አካባቢ ምን ተያያዥነት አላቸው?
5. እናንተ አካባቢ ያሉ ልጆች ምን ዓይነት ጫወታዎች ይጫወታሉ?

## 2. ሰዎች ለመጓጓዣ አገልግሎት የሚጠቀሟቸው ነገሮች

ሰዎች ለመጓጓዣ አገልግሎት የተለያዩ ነገሮችን ሲጠቀሙ ቆይተዋል፤ አሁንም እየተጠቀሙ ይገኛሉ። እነዚህን የመጓጓዣ አገልግሎቶች በመጠቀም በቀላል ሁኔታ ራሳቸው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንዲጓጓዙ የሚያስችላቸው ብቻ ሳይሆን ልዩልዩ ምርቶቻቸውን ጭምር በመጫን ወደ ተለያዩ ቦታዎች ለመውሰድ የሚያስችሏቸው ነገሮች ናቸው።

ሰዎች ተቀምጠው የሚጓጓዙባቸው ወይም ዕቃዎቻቸውን የሚጭኑባቸው ባህላዊ የመጓጓዣ ዘዴ እና ዘመናዊ የመጓጓዣ ዘዴ ተብለው በሁለት ዋና ክፍሎች የተከፈሉ ናቸው።

### 1ኛ. ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች

ከባህላዊ መጓጓዣ ውስጥ የሚጠቀሱት የጋማ ከብቶች ናቸው። የመጓጓዣ አገልግሎት የሚያስፈልገን በእግራችን የምናደርገው ጉዞ እንዳያደክመን ለማድረግ እና ወደ አስብንበት ቦታ በፍጥነት ለመድረስ እንዲረዳን ነው።

እንስሳት በብዙ አካባቢዎች ለመጓጓዣነት ጠቀሜታ ይሰጣሉ። በአገራችን በአብዛኛው ቦታ የመኪና መንገድ ባለመስራቱ የጋማ ከብቶች ለመጓጓዣነት እና ለዕቃ መጫኛነት በስፋት ጥቅም ላይ ሲውሉ ይታያል። የጋማ ከብቶች የሚባሉት ፈረስ፣ በቅሎ፣ አህያ ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው።




**ስዕል 3**
**ፈረስ**

በአገራችን አብዛኛዎቹ ክፍሎች በቅሎና ፈረስ ለመጓጓዣ አገልግሎት ጥቅም ላይ ይውላሉ።



ስዕል 2
*አህያ ላይ የተቀመጠ ልጅ*

*በአንዳንድ አካባቢዎች ከብት የሚጠብቁ እረኞች ከብቶችን ለግጦሽ ይዘው በሚሄዱበት ወቅት ወይም ከብቶችን ከግጦሽ በኋላ ወደ ቤት ይዘው በሚመለሱበት ጊዜ ወይም ከገበያ መልስ በአህዮች ላይ በመቀመጥ ሲጓዙ ይታያል፡፡*



**ስዕል 3**
*ግመል*
***ግመል**በበረሃማ እና በቆላማ አካባቢዎች ግመል ለመጓጓዣነት እና ዕቃ መጫኛነት ያገለግላል፡፡*

*ከላይ ያየናቸው ከባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ባህላዊ መጓጓዣዎች ሰዎች ተቀምጠውባቸው ከቦታ ወደ ቦታ እንዲጓጓዙባቸው ከመርዳቱ በተጨማሪ ልዩልዩ የግብርና እና የፋብሪካ ምርቶችን እንዲጓጓዙባቸው በማድረግ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡*

## 2ኛ. ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች

ዘመናዊ መጓጓዣዎች የሚባሉት በሞተር አማካይነት የሚንቀሳቀሱ ነገሮች ናቸው። በሞተር አማካይነት ከሚንቀሳቀሱ ነገሮች አንዱ መኪና ነው። በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ ዓይነት መኪናዎች ተሰርተው በከተሞች ውስጥና በአንዳንድ ገጠራማ አካባቢዎች ለሰውና ለዕቃ ማጓጓዣነት በስፋት ጥቅም ላይ ውለው ይታያሉ።

ሰዎች ጉዟቸውን ለማቃለል እና ሸክማቸውን ለመቀነስ ከሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው የሚባሉት፡-

- አውቶቡስ የተለያየ መጠን ያለው ሆኖ፣ ብዙ ሰዎችን በማሳፈር ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ የሚያጓጉዝ ነው። ትልቁ አውቶቡስ ወደ 62 ሰው ሲይዝ፣ መለስተኛው ከ25 እስከ 44 ሰው ያሳፍራል።



**ስዕል 4**
**አገር አቋራጭ አውቶቡስ**

- በከተማ ውስጥ ብቻ ሰዎችን ከቦታ ወደ ቦታ የሚያመላልሱ አውቶቡሶች የከተማ አውቶቡስ ተብለው ይጠራሉ። በአዲስ አበባ ከተማ በርካታ የከተማ አውቶቡሶች ለበርካታ ተሳፋሪዎች የመጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣሉ። ከአዲስ አበባ ከተማ ቀጥሎ በአገራችን ከሚገኙት ከተማዎች ውስጥ በጅማ ከተማ ጥቂት የከተማ አውቶቡሶች አገልግሎት ይሰጣሉ። የከተማ አውቶቡስ ወደ ክፍል ሀገር እንደሚጓዙት ረጅም እና መካከለኛ ርቀት አቋራጭ አውቶቡሶች የተወሰነ የሰው መጠን ብቻ የሚጭኑ ሳይሆኑ ሰዎች ቆመው ጭምር እንዲጓዙ ተደርጎ የተሰራ በመሆኑ በዛ ያሉ ተሳፋሪዎችን ማስተናገድ ይችላል። ሆኖም በከተማችን እጅግ በርካታ ሰዎች የሚሳፈሩበት ነው። ይህ ሊሆን የቻለው የከተማ አውቶቡስ እጥረት በመኖሩ እንጂ የከተማ አውቶቡሶች በጣም ብዙ ሰዎችን እንዲጭኑ ተብለው ስለተሰሩ አለመሆኑን ልጆች መገንዘብ ይገባችኋል።



ስዕል 5
የከተማ አውቶቡስ

- ልዩልዩ ጭነቶችን ለመጫን የምንጠቀምባቸው መኪናዎች የጭነት መኪና ተብለው ይታወቃሉ፡፡ የጭነት መኪናዎች ከፊት ሹፌሩን እና አንድ ወይም ሁለት ሰው ሊያሳፍር የሚችል ጋቢና የሚባል ቦታ ሲኖራቸው፣ ከኋላ በኩል ዕቃ መጫኛ አካል አላቸው፡፡ በአገራችን እስከ 400 ኩንታል ክብደት ያላቸው ዕቃዎችን በአንድ ጊዜ መጫን የሚችሉ በርካታ የመኪና ዓይነቶች ሲኖሩ ከነዚህም ውስጥ ከሚጠቀሱት ጥቂቶቹን በስዕል አማካኝነት እንይ ፡-




ስዕል 6
ከባድ የጭነት መኪና


በስዕሉ ላይ እንደታየውና ሌሎችም ዓይነት የጭነት መኪናዎች ዕቃዎችን በማጓጓዝ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

* በከተማዎች ውስጥ ከ4-11 ሰዎችን በመጫን አገልግሎት የሚሰጡ የህዝብ ማመላለሻ ታክሲዎች ተብለው ይታወቃሉ፡፡ በአገራችን ዋና ከተማ በሆነችው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከ12000 የሚበልጡ ታክሲዎች ሰዎችን በየቀኑ በከተማዋ ክልል ውስጥ ያንገዛሉ፡፡ በሌሎች የአገራችን ከተሞች፤ በጐንደር፣ በባህርዳር፣ በመቀሌ፣ በአዋሳ፣ በጅማ፣ በናዝሬት፣ በአምቦ፣ በነቀምት፣ በድሬደዋ ወዘተ፤ ታክሲዎች በከተማው ላሉ ሰዎች የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡



**ስዕል 7**
**ታክሲ**

* ሰዎች ለግላቸውና ለቤተሰባቸው መጠቀሚያ የሚያውሏቸው ተሽከርካሪዎች የቤት መኪናዎች ተብለው ይታወቃሉ፡፡ የተለያዩ ዓይነት የቤት መኪናዎች ያሉ ሲሆን፣ በነዚህ ከ4-10 ሰዎች ሊሳፈሩባቸው ይችላሉ፡፡ የቤት መኪናዎች በቅርፃቸው የተለያዩ በመሆናቸው፣ ሰዎች እንደ ሀብታቸው መጠንና እንደ ፍላጐታቸው የተለያዩ የቤት መኪና ዓይነቶችን በመግዛት ይገለገላሉ፡፡





**ስዕል 8**
**የቤት መኪናዎች**

## ተግባራት

### ተግባር አንድ

**ለነዚህ ጥያቄዎች  አጫጭር መልስ ስጡ**

1. ከባህላዊ ማጓጓዣዎች ውስጥ የተወሰኑትን ጥቀሱ?
2. እናንተ ባላችሁበት አካባቢ ሰዎች የሚጠቀሙባቸው ባህላዊ ማጓጓዣዎች ምን ምን እንደሆኑ ግለፁ?
3. ዘመናዊ ማጓጓዣ ከሚባሉት ውስጥ የምታውቋቸውን ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው?
4. ባላችሁበት አካባቢ ዘመናዊ ማጓጓዣ ከሚባሉት ውስጥ በብዛት ያሉት የትኞቹ ናቸው?
5. የከተማ አውቶቡስ እና የአገር አቋራጭ አውቶቡስ ያላቸው ልዩነት ምንድን ነው?
6. የጭነት መኪናዎች ያሏቸው ሁለት ዋነኛ ክፍሎች ምን ምን ይባላሉ?
7. የትኛውን የመጓጓዣ ዓይነት ተጠቅማችሁ ነው ወደ ት/ቤት የምትሄዱት?
8. ለመጀመሪያ ጊዜ በመኪና ስትጓዙ ምን ስሜት እንደተሰማችሁ በማስታወስ ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡

### ተግባር ሁለት

**ትክክል ለሆነው ሀሳብ እውነት፣ ትክክል ላልሆነው ሀሳብ ስህተት በማለት መልሱ፡፡**

1. የመጓጓዣ አገልግሎት መጠቀም የሚያስፈልገን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በፍጥነት ስለሚያደርሱን ነው፡፡
2. ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ከዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች የበለጠ ፍጥነት አላቸው፡፡
3. ግመል በሁሉም የአገራችን ክፍል የመጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
4. ባህላዊ ማጓጓዣዎችን ለእቃ እና ለሰዎች መጠቀም እንችላለን፡፡
5. የከተማ አወቶቡሶች ሰዎችን ሲያጓጉዙ የሚታዩት በከተማዎች ውስጥ ብቻ ነው፡፡

## 3. ጥቅም የሚሰጡ ነገሮች ጉዳትም ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

ባህላዊ እና ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች የሚሰጡንን ጥቅም ከቀዳሚው ትምህርታችን ተገንዝበናል፡፡ ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን በአግባቡ ካልተጠቀሙ ወይም በነዚህ ነገሮች አማካኝነት አደጋ እንዳይደርስባቸው ጥንቃቄ ካላደረጉ የተለያዩ አደጋዎች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ፡፡

ባህላዊ የመጓጓዣ አገልገሎት የሚሰጡ የጋማ ከብቶችን አዋቂ ሰው በሌለበት ቦታ በመያዝ ለመቀመጥ መሞከር የተለያዩ አደጋዎችን ሊያስከትል ይችላል፡፡ እነዚህ እንሰሳት የኋላ እግራቸውን አንስተው በመራገጥ አደጋ ሊያደርሱብን ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ወላጆቻችን ካልፈቀዱልን እና ካልያልን በስተቀር ለመቀመጥ መሞከር የለብንም፡፡



ስዕል 9
**የጋማ ከብት ከሆነው አንዱ ሲራገጥ**

እንስሳት መራገጥ ብቻ ሳይሆን፣ ከተቀመጥንባቸውም በኋላ ሊጋልቡ ወይም በፍጥነት ሊጓዙ ስለሚችሉ ከጀርባቸው ላይ በመውደቅ ከፍተኛ አደጋ ሊያደርሱብን ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ልጆች፣ እንስሳት የመጓጓዣ ጠቀሜታ የሚሰጡን ቢሆንም አደጋ የሚያደርሱበት ሁኔታም ስለሚኖር ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል፡፡

ዘመናዊ የመንጓጓዣ ዓይነቶች ናቸው ተብለው የተጠቀሱት አገልግሎት የሚሰጡን መኪናዎች በተለያዩ የጥንቃቄ ጉዳለቶች የተነሳ በእግረኞችም ሆኑ በተሳፋሪዎች ላይ ከፍተኛ አደጋ ማድረስ የሚችሉ ነገሮች ናቸው፡፡ መኪናዎች አደጋ እንዳያደርሱብን መውሰድ ስላለብን ጥንቃቄ እስክንማር ድረስ #ህይወት ዋጋ አላት; የሚለውን መዝሙር እንዘምር፡፡

***<u>ህይወት ዋጋ አላት</u>***

እናቴንም……….እወዳታለሁ፣
አባቴንም ……..እናፍቃለሁ፣
አገሬንም ……..አከብራለሁ፣
ህይወቴንም …..እጠብቃለሁ፡፡

ጠንቃቃ ነኝ ……..ትጉህ ወጣት፣
ቦታ እንምረጥ…….ለመጫወት፡፡
ቦታ እንምረጥ …..ለመጫወት፣
ህይወት ህይወት….አለው ብልጫ፣
ህይወት ህይወት…..አለው ብልጫ፡፡

ልጆች፣ ሰው ህይወቱን ከአደጋ ጠብቆ የሚያቆይ ከሆነ አገሩን፣ ወላጆቹን እና ራሱን ሊጠቅም እንደሚችል በመገንዘብ ለጫወታ ብለን የምናደርጋቸው ነገሮች አደጋ እንዳያደርሱብን መጠንቀቅ እንዳለብን ከመዝሙሩ እንገነዘባለን፡፡

## የተግባር ጥያቄዎች


### ለነዚህ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ሰጡ

1. ዘመናዊ ማገንዣዎች ከሚያደርሷቸው አደጋዎች ውስጥ የሰማችሁትን ወይም የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው?
2. በባህላዊ ማገንዣነት አገልግሎት የሚሰጡን እንስሳት ከተጠቀሰው አደጋ በተጨማሪ ምን ዓይነት አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?
3. ራሳችሁን ከአደጋ ለመጠበቅ ምን ማድረግ ጠቃሚ ነው ትላላችሁ?
4. በአካባቢያችን ዘመናዊም ሆነ ባህላዊ የመጓጓዣ አገልገሎት በሚሰጡ ነገሮች የደረሱ አደጋዎችን ከወላጆቻችሁ ጠይቃችሁ ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው?
5. ህይወት ዋጋ አላት ከተባለው መዝሙር ምን ትምህርት አገኛችሁ?

## 4. አደጋ የሚያደርሱ ነገሮች

አደጋ በተለያዩ ነገሮች አማካኝነት ሊደርስ ይችላል፡፡ በገጠር አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ከቤታቸው ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች ሲጓዙ የሚያቋርጧቸው ወንዞች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ወንዞች በሚሞሉበት ወቅት አደጋ እንዳያደርሱ ወይም ጥልቀት ያላቸው ከሆኑ እንዳያሰምጡ ወንዞቹን ለመሻገሪያ አገልግሎት እንዲሰጡ በተሰሩ ድልድዮች በመጠቀም መሻገር ይገባችኋል፡፡

ወንዝ ውስጥ ገብቶ መጫወት ወይም መዋኘት አደጋ ሊያስከትል የሚችልበት ሁኔታ ስላለ እንደነዚህ ካሉ አደጋ ሊያስከትሉ ከሚችሉ ነገሮች እራሳችሁን መጠበቅ ይኖርባችኋል፡፡




**ስዕል 10**
**ድልድይ**

ድልድይ በሌለበት ሁኔታ ወንዝ ውስጥ ገብተን ለመሻገር መሞከር አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡ በመሆኑም ለመሻገር ከመሞከራችን በፊት በእድሜ ከፍ ያሉ ሰዎች እርዳታ እንዲያደርጉልን ትብብራቸውን መጠየቅ ይበልጥ የሚመረጥ ይሆናል፡፡

በከተሞች ውስጥና በገጠር አንድአንድ አካባቢዎች ሰዎች የመብራት አገልግሎት የሚያገኙት ከኤሌክትሪክ ሀይል ነው፡፡ የኤሌክትሪክ ሀይል ለተለያዩ ጠቀሜታዎች የሚያገለግል መሆኑ ይታወቃል፡፡ ጠቀሜታውም ከፍተኛ ነው፡፡ ከጠቀሜታው ውስጥ የመብራት አገልግሎት መስጠት፣ እንጀራ ለመጋገር ማገዶ ተክቶ ማገልገል፣ ምግብን ለማቀዝቀዝ የሚያገለግል ፍሪጅ እንዲሰራ ማድረግ፣ ቴፕ፣ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ እንዲሰራ ሀይል መስጠት የሚሉት የተወሰኑት ናቸው፡፡

ኤሌክትሪክ፣ ጠቀሜታው ከፍተኛ ቢሆንም፣ ቤታችን ውስጥ የምንገለገልበት ወይም ውጭ የኤልክትሪክ ማስተላለፊያ ሽቦ የተላጠ ወይም የተበጠሰ ከሆነ በእጅ መንካት የሚያስከትለው አደጋ ህይወት ሊያሳጣ የሚችል ነው፡፡

ልጆች፣ የኤሌክትሪክ ሽቦዎች ተበጥሰው መንገድ ላይ ወድቀው በሚታዩበት ወቅት ለትላልቅ ሰዎች መንገር እንጂ መንካት (መያዝ) አይኖርባችሁም፡፡ ቤት ውስጥም ቢሆን ማብሪያና ማጥፊያ በአግባቡ ተጠቅሞ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለማግኘት መሞከር እንጂ የተበጠሰ ወይም የተለያዩ ሽቦዎችን ለመቀጠል መሞከር አደጋ የሚያስከትል በመሆኑ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲገጥማችሁ ትልልቅ ሰዎች እንዲሰሩት ወይም እንዲያበሩላችሁ መጠየቅ ይኖርባችኋል፡፡



**ስዕል 11**
**ትልቅ ሰው የቤት ውስጥ መብራት ሲሰራ**

ልጆች! በሰፈራችሁ በኤሌክትሪክ ገመድ (ሽቦዎች) መነሻ የደረሰ አደጋ መኖር አለመኖሩን ከወላጆቻችሁ ጠይቁና ስለሁኔታው ተወያዩ፡፡

ሰዎች ላይ ከፍተኛ አደጋ እያደረሱ ካሉ ነገሮች አንዱ እና ከፍተኛው የመኪና አደጋ ነው፡፡ በሃገራችን ይህ አደጋ የሚደርሰው በአብዛኛው በእግረኞች ላይ ነው፡፡ እግረኞች በመኪና መንገድ ላይ ወይም ሲያቋርጡ ጥንቃቄ ካልወሰዱ ወይም ማድረግ የሚገባቸውን ጥንቃቄ ካላደረጉ የመኪና አደጋ ሊደርስባቸው ይችላል፡፡

በመኪና መንገድ ውስጥ ገብቶ መጓዝ አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡ የሚደርሱ አደጋዎች ህይወትን ሊያሳጡ ይችላሉ፡፡ ሁኔታው ወላጆች ላይ ከፍተኛ የሆነ ሀዘንም ያስከትላል፡፡

ስለዚህ የምትወዷቸው ወላጆቻችሁን ማሳዘን ስለማይገባችሁ ጤንነታችሁና ህይወታችሁ ተጠብቆ፣ ትምህርታችሁን ተምራችሁ ለአገር የምትጠቅሙ ዜጎች እንድትሆኑ እራሳችሁን ከተለያዩ አደጋዎች መጠበቅ ይኖርባችኋል፡፡

የተግባር ጥያቄውን ከመስራታችሁ በፊት "አለው ዘዴ" የሚለውን መዝሙር ተለማምዳችሁ በመዘመር ለወላጆቻችሁ አሰሙ፡፡ ለመዝሙሩ የሚሆን ዜማ መምህራችሁ እንዲያመጡላችሁ ጠይቋቸው፡፡

**አለው ዘዴ**

*መንገድ ማቋረጥ................በትኩረት፣*
*ትምህርትን መማር ......... በትጋት፣*
*ወንዝን መሻገር ............... በብልሀት፣*
*መብራትን ማብራት ........ በስርዓት፣*
*ጥናትን ማጥናት ............ በትዕግስት፣*

አለው ዘዴ አለው ብልሃት፣
ህይወትን በጤና ለመምራት፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች**

**እነዚህን ጥያቄዎች መሠረት አድርጋችሁ ተገቢውን መልስ ስጡ**

1. አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ እና በአካባቢያችን ያሉ ነገሮች ምንና ምን ናቸው?
2. ሰዎች ላይ ከፍተኛ አደጋ እያስከተሉ ካሉ ነገሮች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ምንድን ነው?
3. መኪና መንገድ ውስጥ ገብቶ መሄድ ምን አደጋ ሊያስከትልብን ይችላል?
4. ወንዞችን በምን ሁኔታ ስንጠቀም ነው አደጋ ሊያስከትሉብን የሚችሉት?
5. መንገድ ላይ የወደቀ የኤሌክትሪክ ሽቦ ስናይ፣ ቤት ውስጥ ማብሪያ ማጥፊያ የሌለው የኤሌክትሪክ መስመር ሲኖር መውሰድ ያለብን የጥንቃቄ እርምጃ ምን መሆን አለበት?
6. ድልድይ የሌላቸውን ወንዞች ለመሻገር ከመሞከራችን በፊት ማድረግ የሚገባን ቅድመ ጥንቃቄ ምንድን ነው?
7. የኤሌክትሪክ ኃይል ምን ጥቅም ይሰጣል?
8. "አለው ዘዴ" ከሚለው መዝሙር ምን ተማራችሁ?

## 5. ስነ ስርዓትን መያዝ የሚሰጠን ጥቅም

የሰው ልጅ ሁሉም ነገሮች ለሱ ጥቅም በሚሰጡ ሁኔታዎች እንዲፈፀሙ ለማድረግ ይጥራል፡፡ እያንዳንዱን ነገርም በተፈለገው ሁኔታ እንዲፈፀሙ የሚያስችለው የራሱ አካሄድ አለው፡፡ ይህ ሁኔታ በነዋሪው ማህበረሰብ የተከበረ መሆን አለበት፡፡ ነዋሪው እያንዳንዱን ነገር በስነስርዓት መጠቀም ካልቻለ ልናገኝ የምንችለው ጥቅም ሳይሆን ጉዳትን ነው፡፡

ስለዚህ ነው እያንዳንዱን ነገር መፈፀም የሚያስችለን የስነስርዓት ደንብ የሚወጣው፡፡ ለምሳሌ ትምህርት ቤቶች ዕውቀት የሚጨበጥባቸው ቦታዎች ናቸው፡፡ የሰው ልጅ አስተሳሰብ ሰፊ ሆኖ እንዲያድግ መማር ያስፈልጋል፡፡ ትምህርት ለሰው ልጅ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው፡፡ የትምህተርትን ጠቀሜታ የምናገኘው ተገቢውን የትምህርት ቤት ስነስርዓት ስናከብር መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከት/ቤት ስነስርዓት ማስጠበቂያ ደንቦች ውስጥ ስዓቱን ጠብቆ ት/ቤት መድረስ፣ የመማሪያ መጽሐፍትንና ደብተሮችን አሟልቶ መያዝ፣ ዩኒፎርም መልበስ የመሳሰሉት እንዲሟሉ የት/ቤት ደንብ ያስገድዳል፡፡ እነዚህንና ሌሎች ደንቦችን የማያከብር ተማሪ ደንብ ባለማክበር የስነስርዓት እርምጃ ሊወስድበት ይችላል፡፡

ስነስርዓትን መጠበቅ የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ ሰዎች በመንገድ ላይ በሚሄዱበት ጊዜ ስነስርዓት መጠበቅ አለባቸው፡፡ መኪናዎች ሲጓዙ የመንገድ ስነስርዓትን መጠበቅ አለባቸው፡፡ እግረኞችም ሆኑ አሽከርካሪዎች የመንገድ ላይ ስርዓትን ጠብቀው የማይጓዙ ከሆነ ለአደጋ የተጋለጡ ይሆናሉ፡፡ በራሳቸውም ሆነ በሌላው ላይ አደጋ እንዲደርስም ያደርጋሉ፡፡

ተማሪዎች፣ የትምህርት ቤት ስነስርዓትን የማያከብሩ ልጆች አታውቁም? አዎን አንዳንድ ተማሪዎች በስርዓቱ ት/ቤት አይደርሱም፣ እንዳንዶች የመማሪያ ደብተሮቻቸውን ይዘው ላይመጡ ይችላሉ፡፡ ልክ እንደነዚህ ዓይነት ልጆች ሁሉ የመንገድ ስርዓትንም የማያከብሩ ሰዎች በራሳቸውም ሆነ በሌላው ላይ አደጋ ሊያስከትሉ እንደሚችሉ መገንዘብ ይኖርባችኋል፡፡

ስለዚህ አደጋ እንዳይደርስባችሁ መንገድ ላይ በምትጓዙበት ጊዜ የመንገድ አጠቃቀም ደንቦችን ማክበር ይጠበቅባችኃል፡፡


<u>የተግባር ጥያቄ</u>

<u>ለነዚህ ጥያቄዎች የሚሆኑ ግልጽ መልሶች ስጡ</u>

1. ሁሉም ነገር በአግባቡ እንዲፈፀም ደንብ መኖሩ ምን የሚሰጠው ጠቀሜታ አለ?
2. የት/ቤት ደንቦች ተብለው ከተገለፁት በተጨማሪ ሌሎች ደንብ ነክ ነገሮችን ዘርዝሩ?
3. አሽከርካሪዎችም ሆኑ እግረኞች የመንገድ ላይ ስርዓትን ካልጠበቁ ምን ሊያጋጥማቸው ይችላል? ዘርዝር አድርጋችሁ ግለፁ?
4. ትምህርት ለሰው ልጅ ምን ጠቀሜታ ይሰጣል?
5. የመንገድ አጠቃቀም ደንቦች ከሚባሉት ውስጥ የምታውቋቸውን ግለፁ?

## <u>6. የአካባቢያችን አንፃራዊ መገኛ</u>

ሰዎች የአካባቢያቸውን አቅጣጫ ለመረዳት እንዲያስችላቸው ስያሜ ሰጥተዋቸዋል፡፡ እነዚህም አቅጣጫዎች ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምስራቅና ምዕራብ ተብለው በአራት ይከፈላሉ፡፡ እጃችንን ወደ ጐን ዘርግተን፣ ፀሐይ ጠዋት ወደምትወጣበት አቅጣጫ በማየት ብንቆም ፊት ለፊት የምናየው አቅጣጫ ምስራቅ ሲባል፤ በጀርባችን በኩል ያለው አቅጣጫ ደግሞ ምዕራብ ተብሎ ይጠራል፡፡ ቀኝ እጃችን የተዘረጋበት አቀጣጫ ደቡብን ሲያመለክት፣ ግራ እጃችን የተዘረጋበት አቅጣጫ ደግሞ ሰሜንን የሚየመለክት ይሆናል፡፡




**ስዕል 12**

**የአካባቢያችን አንጻራዊ መገኛ**

ጠዋት ፀሐይ የምትወጣበትን አቅጣጫ መሠረት በማድረግ የተለያዩ ነገሮች /ቦታዎች/ በየትኛው አቅጣጫ እንደሚገኙ መናገር እንችላለን፡፡
አሁን ያላችሁበት ቦታ ከትምህርት ቤቱ በር በየትኛው አቀጣጫ ይገኛል ብላችሁ ታስባላችሁ? እስኪ ከመምህራችሁ ጋር ተነጋገሩበት፡፡

## 7. የመንገድ ላይ አደጋዎች

መምህራችሁ ስለ አካባቢያችን አንፃራዊ መገኛ ተጨማሪ ምሳሌዎችን እንዲሰጧችሁ በመጠየቅና የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠያየቅ ግንዛቤያችሁን ማሳደግ ትችላላችሁ፡፡

ትላልቅ ሰዎችም ሆኑ ህፃናትና ወጣት ተማሪዎች ራሳቸውን ከመንገድ ላይ አደጋ መጠበቅ ይገባቸዋል፡፡ ሰዎች በመንገድ ላይ ሲጓዙ ጥንቃቄ ካላደረጉ በተለያዩ ነገሮች አደጋ ሊያደስባቸው ይችላል፡፡ የተበጠሰ የኤሌክትሪክ ሽቦም ሆነ፣ የውሃ ሙላት አደጋ ሊያደርስባቸው ይችላል፡፡ መንገዱን በአግባቡ አይተን የማንሄድ ከሆነ ድንጋይ ወይም የእንጨት ጉቶ አደናቅፎን አደጋ ሊደርስበን ይችላል፡፡

ሰዎች ራሳቸውን ከተለያዩ አደጋዎች ለመጠበቅ የሚችሉት በሚወሰዱት ጥንቃቄ ብቻ ነው፡፡ ተማሪዎችም በመንገድ ላይ በሚጓዙበት ወቅት ጥንቃቄ በማድረግ አደጋ እንዳይደርስባቸው ራሳቸውን መጠበቅ ይገባቸዋል፡፡

በመንገድ ላይ በምንጓዝበት ጊዜ አደጋ እንዳይደርሰብን የሚያስችሉን እርምጃዎች የጥንቃቄ እርምጃዎች ይባላሉ፡፡ እናንተና ጓደኞቻችሁ ማወቅ የሚገባችሁ የጥንቃቄ እርምጃዎች ምን ሊሆኑ እንደሚገባቸው ከመምህራችሁ፣ ከታላላቅ ወንድሞቻችሁ ወይም ወላጆቻችሁ በመጠየቅ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

## 8. የመኪና መንገድ ስናቋርጥ መውሰድ ያለብን ጥንቃቄ

በገጠር መንደር ውስጥም ሆነ በከተማ የምንገኝ ወጣቶች የመኪና መንገድ ስናቋርጥ ጠንቃቆች መሆን ይገባናል፡፡ ጫወታ እየተጫወትን ወይም ወሬ እያወራን መንገድ ለማቋረጥ መሞከር የለብንም፡፡

በጉዞ ጊዜ መንገዶችን ስንጠቀም በመኪና መንገዱ ዳር እና ዳር የእግረኞች መንገድ ካለ በዚያ መንገድ ተጠቅሞ መጓዝ፣ በተለይ ለእግረኞች ተብሎ የተሰሩ መንገዶች ከሌሉ የመንገዱን ግራ ጠርዝ በመያዝ መጓዝ ይኖርብናል፡፡



ስዕል 13
እግረኛ የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዞ ሲጓዝ

የመኪና መንገዱን ግራ ጠርዝ ይዘን ስንጓዝ ወሬ እያወራን ወይም ጫወታ እየተጫወትን ጐን ለጐን ሆነን መጓዝ አይኖርብንም፤ ምክንያቱም በዚህ ሁኔታ የምንሄድ ከሆነ መንገዱን በስፋት ስለምንይዘው እና መንገዱን ስለምናጠብ የሚተላለፍ መኪና አደጋ ሊያደርስብን ይችላል፡፡



ስዕል 14
ጐን ለጐን ሆነው ሲጓዙ

የመኪና መንገድ የምናቋርጥ ከሆነ፣ በከተሞች ውስጥ ለእግረኞች ማቋረጫ ተብሎ ነጭ ቀለም (ዜብራ) የተቀባባቸው ምልክቶች ካሉ ቅቡ ባለበት አቅጣጫ ብቻ ማቋረጥ ይኖርብናል፡፡ የእግረኛ ማቋረጫ ምልክቶች ያላቸው መንገዶች ላይ የሚጓዙ አሽከርካሪዎች፣ ሰዎች በዚያ በኩል ሊያቋርጡ እንደሚችሉ በመገመት ሊጠነቀቁ ይገባል፤ ነገር ግን አንዳንድ አሽከርካሪዎች በቸልተኝነት እና ሀሳባቸውን ሌላ ነገር ላይ በማድረግ ሁኔታውን ሳያገናዝቡ በፍጥነት የሚያሽከረክሩበት ጊዜ ስለሚኖር በእግረኛ ማቋረጫዎች ተጠቅመን መንገዱን ከማቋረጣችን በፊት መኪና ሊደርስብን እንደማይችል ቀድመን ማረጋገጥ አለብን፡፡ በአንድ መንገድ ላይ በሁለቱም አቅጣጫዎች መኪናዎች ወደላይና ወደታች የሚሄዱ ከሆነ ግራ ቀኝ ግራ አቅጣጫ መኪና መኖር አለመኖሩን ወይም በቅርብ ርቀት አለመድረሱን በማየት በጥንቃቄ መሃል ድረስ ካቋረጥን በኋላ ቀሪውን ለማቋረጥ ወደቀኝ በማየት ተጠንቅቀን ማቋረጥ አለብን



ስዕል 15
የእግረኛ ማቋረጫ ምልክት

በደሴት የተከፈለ መንገድ ከሆነ መጀመሪያ በቆምንበት ግራ አቅጣጫ መኪና መኖር አለመኖሩን ወይም በቅርብ ርቀት አለመድረሱን በማየት የመንገዱን ግማሽ ያህል ካቋረጥን በኋላ ደሴቱ ላይ ስንደርስ ወደ ቀኝ እጃችን አቅጣጫ በመዞር በዚያ በኩል የሚመጣ መኪና አለመኖሩን አረጋግጠን የመንገዱን ቀሪ ግማሽ ክፍል በጥንቃቄ ማቋረጥ አለብን፡፡ ከዚህ በተለየ ለማቋረጥ መሞከር አደጋ ሊያስከትልብን ይችላል፡፡



ስዕል 16
የመንገድን ግማሽ አቋራጭ ወደ ቀኝ ማየት

በገጠር መንገዶች የምንጠቀም ተማሪዎች የእግረኛ ማቀረጫ ምልክቶችን ልናገኝ የምንችልበት ሁኔታ ስለማይኖር ግራና ቀኛችንን ዞር ዞር ብለን በማየት ከዚያ በድጋሚ ወደ ግራ አቅጣጫ በመመልከት መኪና ወይም ሌሎች አደጋ የሚያደርሱ ሁኔታዎች በመንገዱ ላይ አለመኖራቸውን ሰናረጋግጥ ፈጠን ባለ እርምጃ መንገዱን ማቋረጥ ይኖርብናል፡፡

<u>የተግባር ጥያቄዎች</u>

<u>ለነዚህ ጥያቄዎች የሚሆኑ መልሶችን በመስጠት ተወያዩበት</u>

1. የመኪና መንገድ ይዘን ስንጓዝ ምን ጥንቃቄ መውሰድ አለብን?
2. የመኪና መንገድ ይዘን ሰንጓዝ ጐን ለጐን ሆነን ነው ወይስ በሰልፍ መልክ ሆነን መጓዝ ያለብን?
3. በገጠርና በከተማ ያሉ የመኪና መንገዶችን ለማቋረጥ ማድረግ ያለብን ጥንቃቄ ያለው ተመሳሳይነት እና ልዩነት ምንድነው?
4. እናንተ የመኪና መንገድ ላይ ስትሄዱ ከዚህ በፊት በምን ሁኔታ ነበር ስትጎዙ የነበራችሁት?
5. በመኪና መንገዶች ላይ የእግረኛ መተላለፊያ ምልክቶች መኖራቸው ለአሽከርካሪዎች ምን ጠቀሜታ ይሰጣል?
6. ሁሉም አሽከርካሪዎች የእግረኛ ማቋረጫ ምልክት በማየት ብቻ ተገቢውን ጥንቃቄ ያደርጋሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?
7. በመንገድ ላይ ስንጓዝ አደጋ ሊያደርስብን የሚችለው መኪና ብቻ ነው? ወይስ ሌሎች አደጋ ሊያደርሱብን የሚችሉ ነገሮችም አሉ? ካሉ ምን ነገሮች አደጋ እንዳያደርሱብን መጠንቀቅ አለብን?
8. ህፃናት ስለሆናችሁ አደጋ እንዳይደርስባችሁ መጠንቀቅ የኛ ተግባር አይደለም ብላችሁ ታስባላችሁ?
9. የመኪና መንገድ ስናቋርጥ ግራና ቀኛችንን ዞር ዞር ብለን ማየት የሚገባን ለምንድነው?
10. ጐን ለጐን ሆነን ወይም እየተጫወትን በመኪና መንገድ ለመሄድ መሞከር አደጋ ሊያስከትል የሚችለው ለምንድነው?

ልጆች የነዚህን ጥያቄዎች መልስ ለወላጆቻችሁ ወይም ለመምህራችሁ ንገሯቸውና ምን ያህል ትክክል እንደሆናችሁ አረጋግጡ፡፡


## 9. የመንገድ ላይ የትራፊክ መብራት ጠቀሜታ

በአገራችን ከሚገኙ ከተሞች ውስጥ በጥቂቶቹ ለምሳሌ በአዲስ አበባ፣ በአዋሳ፣ በባህርዳር፣ በመቀሌ… ወዘተ፣ የመንገድ ላይ የትራፊክ ስነስርዓት ማስጠበቂያ የመብራት ምልክቶች በአንዳንድ ቦታዎች ተተክለው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

የመንገድ ላይ የመብራት ምልክቶች የሚሠሩት በኤሌክተሪክ ኃይል ሲሆን፣ የመኪና እና የእግረኛ እንቅስቃሴ አደጋ በማይፈጥርበት ሁኔታ እንዲከናወን እገዛ ያደርጋሉ፡፡

የመንገድ ላይ የትራፊክ ማስተላለፊያ መብራቶች ሶስት ዓይነት ቀለም ያላቸው ሲሆን፤ ቀለሞቹም አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ናቸው፡፡ አረንጓዴ መብራት ሲበራ መኪናዎች እንዲተላለፉ መፍቀጃ በመሆኑ አረንጓዴ የመንገድ መብራት ሲበራ እግረኞች የመኪና መንገዱን ለማቀረጥ መሞከር የለባቸውም፡፡ ቢጫው መብራት የሚያመለክተው ቀጣዩ የመብራት ምልክት ቶሎ ሊበራ እንደሚችል መስጠቀቂያ በመሆኑ እግረኞችም ሆኑ አሽከርካሪዎች ጥንቃቄ እንዲወስዱ ማሳሰቢያ ነው፡፡ ከፊትለፊታቸው ቀይ መብራት በሚበራበት ጊዜ መኪናዎች መንቀሳቀስ ያቆማሉ፡፡ ለአሽከርካሪዎች የቀዩ መብራት የሚያመለክተው እንዲያቆሙ በመሆኑ፣ እግረኞች ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው መንገዱን ሊያቋርጡ ይችላሉ፡፡

ልጆች፣ የኛ አገር መብራት እግረኞች ማቋረጥ እንደሚችሉ የሚያመለክት የተለየ ምልክት የሌለው በመሆኑ እንጂ ትክክለኛው እግረኞች እንዲያቋርጡ መፍቀጃ ምልክት ከዚህ ትንሽ የተለየ መሆኑን መገንዘብ ይኖርባችኋል፡፡ ዓለም አቀፍ ይዘት ያለውን እግረኛ እንዲያቋርጥ መፍቀጃ የመብራት ምልክት በቀጣዮቹ ክፍለ ትምህርት ታገኛላችሁ፡፡



**የትራፊክ እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ መብራት**

ስዕል 17

<u>የተግባር ጥያቄዎች</u>

<u>የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት፣ ስህተት ከሆኑ ሀሰት እያላችሁ መልስ ስጡ</u>

1. በመንገድ ላይ የተተከሉ የመብራት ምልክቶች የሚያገለግሉት ለተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ብቻ ነው፡፡
2. ለተሽከርካሪዎች አረንጓዴ መብራት ሲበራ እግረኞች መንገዱን ማቋረጥ ይችላሉ፡፡
3. በመንገድ ላይ የተተከሉ የመብራት ምልክቶች የሚሰሩት በኤሌክትሪክ ኃይል እገዛ ነው፡፡
4. ብጫ መብራት ሲበራ እግረኞችም ሆኑ ተሽከርካሪዎች መንዱን ሊያቋርጡ ይችላሉ፡፡
5. ሁል ጊዜ ከቢጫው መብራት ቀጥሎ ሲበራ የሚታየው አረንጓዴው መብራት ብቻ ነው፡፡

<u>ቀደም ሲል የተማራችሁትን መስረት በማድረግ መልስ ስጡ</u>

1. የመንገድ ላይ የትራፊክ መብራቶች ስንት ዓይነት ቀለም አላቸው? የእያንዳንዱን ጠቀሜታ ጭምር ግለፁ?
2. ቀይ ቀለም ያላቸው ነገሮችን ለመምህራችሁ ንገሯቸው (ለምሳሌ፡- ደም፣ ቲማቲም)
3. ብጫ ቀለም ያላቸው ምን ነገሮችን ታውቃላችሁ? (ለምሳሌ፡- ብርቱካን፣ ሚሪንዳ)
4. በአካባቢያችሁ የሚገኙ አረንጓዴ ቀለም ያላቸው ነገሮች ምንድናቸው? (ለምሳሌ ሳር)

<u>ተግባራት</u>

1. በመኪና መንገድ ላይ ያሉ የመብራት ምልክቶች ያሏቸውን ቀለሞች በተለያዩ ወረቀቶች ላይ በክብ በመቀባት ለጓደኞቻችሁ እያሳያችሁ ምን ጠቀሜታ እንዳላቸው እንዲገልፁ በማድረግ ተራ በተራ ተጫወቱ፡፡
2. እነዚህን ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ ሳይሳሳት ለመለሰው ተማሪ አጨብጭቡለት፡፡ መምህሮቻችሁ ወይም ወላጆቻችሁ ከላይ ለተጠቀሱት ጥያቄዎች የሰጣችሁት መልስ ትክክለኛ መሆኑን እንዲያረጋግጡላችሁ ጠይቋቸው፡፡

<u>10. ድራማ፡- አለማመዛዘን ያስከትላል ሀዘን</u>

<u>**ቅድመ ክንውን፡-**</u> ሶስት ተማሪዎች ቀይ ብጫ እና አረንጓዴ ቀለም የተቀባባቸውን ወረቀቶች ይይዛሉ፡፡ ሌሎች ሶስት ተማሪዎች እንደ መኪና ብብብብ እያሉ አጐንብሰው እንዲሄዱ ማድረግ፡፡ አራት ተማሪዎች መንገድ እንደሚያቋርጥ ሰው የመንገዱን ዳር ይዘው ይቆማሉ፡፡

ሶስቱ እንደ መኪና ለመሄድ የተዘጋጁት ተማሪዎች ቀዩን ምልክት ሲያዩ ይቆማሉ፡፡ በዚህ ጊዜ እግረኞቹ ትክክለኛውን የመንገድ ማቀረጥ ዘዴ ተጠቅመው፣ ማለትም ግራ ቀኝ ግራ በማየት መንገዱን ያቋርጣሉ፡፡ ወዲያውኑ ብጫ ቀለም የተቀባውን ምልክት በማሳየት ቀጥሎ አረንጎዴው ምልክት ሊታይ ሲል ሁለት ተማሪዎች እንደ ጓደኞቻቸው መንገዱን ለማቋረጥ በሩጫ ሲገቡ መኪና ሲገጫቸው ማሳየት



ስዕል 18
የመኪና መንገድ ላይ ልጆች እየተሯሯጡ ሲጫወቱ

ይህን ድራማ የሚሰሩትን ልጆች መምህራችሁ መርጠው በየተግባሩ እንዲመድቧቸው ጠይቁዋቸው፡፡ ልጆቹ ድራማውን ከተለማመዱ በኋላ ለክፍል ተማሪዎቻቸው እንዲያቀርቡ በማድረግ በጥንቃቄ መንገዱን ስለተሻገሩበት ሁኔታና አደጋ እንዴት ሊደርስ እንደቻለ ከድራማው በኋላ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

**<u>የተግባር ጥያቄዎች</u>**

1. የመጀመሪያዎቹ ልጆች አደጋ ሳይደርስባቸው ሊያልፉ (መንገዱን ሊያቋርጡ) የቻሉት እንዴት ነው?
2. የመኪና መንገድ በሩጫ ለማቋረጥ መሞከር ምን ጉዳት ሊያስከትል ይችላል?
3. ጠንቃቃ የሆኑ ልጆች የመኪና መንገድ ሲያቋርጡ ምን ዓይነት ተግባር መፈፀም አለባቸው?
4. የእግረኛ መተላለፊያ መንገድ ምን የተለየ ምልክት አለው?
5. አሽከርካሪዎች የእግረኛ ማቋረጫ ምልክት ጋ ሲደርሱ ከሌላው መንገድ የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው የሚባለው ለምንድነው?
6. እናንተ የመኪና መንገድ የምታቋርጡት ምን ዓይነት ጥንቃቄ በማድረግ ነው?

ቀጣዩን ታሪክ ከማንበባችሁ በፊት መምህራችሁ ለዚህ መዝሙር ዜማ እንዲያወጡላችሁ በመጠየቅ ዘምሩ፡፡

**<u>ተጠበቅ ከአደጋ</u>**

መጠንቀቅ ነው.............. ከአደጋ፣
ህይወትህን .................. እንዳትጐዳ፡፡
ትምህርቴንም .............. እወዳለሁ፣
ህይወቴንም ................. ጠብቃለሁ፣
ስለዚህም ......................አስተውላለሁ፣
ተጠንቅቄ ......................እጓዛለሁ፡፡

## <u>11. ድርፉጮ</u>

ድርፉጮ ንቁና ጉበዝ ተማሪ ነው፡፡ የሚኖረው በአንድ አነስተኛ የገበሬዎች መንደር ውስጥ ነበር፡፡ በመንደራቸው ት/ቤት ባለመኖሩ እሱን ከመሳሰሉ የመንደሩ ልጆች ጋር በእግሩ ራቅ ወዳለ ቦታ በመሄድ ይማራል፡፡ ትጉህና ጉበዝ ተማሪ በመሆኑ ለትምህርቱ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡

ከጓደኞቹ አንዱ የሆነው ቶሎሳ ባለፈው ክረምት ዘመዶቹን ለመጠየቅ ወደ ከተማ ሄዶ ነበር፡፡ ስለከተማ ውስጥ ግርግር መብዛት፣ ብዙ መኪናዎች ስለመኖራቸውና አንዳንድ ወጣቶች በመኪና ላይ እየተንጠለጠሉ እንደሚጓጓዙ ማየቱን ለጓደኞቹ ነገራቸው፡፡ በበጋ ወራት ወደ መንደሩ ቡና ለመጫን በሚመጡ መኩናዎች ላይ በመንጠልጠል ወደ ት/ቤት ሊሄዱ እንደሚችሉ ለጓደኞቹ ገለፀላቸው፡፡ የአጐቱ ልጅ እንዴት በመኪና መንጠልጠልና መጓዝ እንደሚቻል እንዳሳየውና ጓደኞቹ እና እሱ በዘዴው መጠቀም እንዳለባቸው በማግባባት አስረዳቸው፡፡

ጠንቃቃው ድርፉጮ ግን ይህንን ሀሳብ ባለመቀበሉ “ድርፉጮ የፈሪ ቁንጮ” በማለት እያበሸቁት ይሳሳቁበት ጀመር፡፡ ድርፉጮ ግን “እኔ የፈሪ ቁንጮ ሳልሆን የጠንቃቆች ቁንጮ ነኝ” በማለት እንደ ድሯቸው ትምህርታዊ ጥያቄዎችን እየተጠያየቁ በእግራቸው መጓዙ እንደሚሻል ይመክራቸው ነበር፡፡

ከጓደኞቹ ጥቂቶቹ በሱ ሀሳብ ሲስማሙ ሌሎቹ ግን የቶሎሳን ሀሳብ ደገፉ፡፡ አንድ ቀን ከት/ቤት ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ወንዙ አካባቢ ባለው ዳገት የተነሳ ቀስ ብሎ የሚጓዝ የጭነት መኪና

አዩ፡፡ ቶሎሳ “እንሂድ እንጠልጠል” ሲላቸው ድርፉጮ እምቢ ሲል ሌሎች እስኪ ቶሎሳ ተንጠልጠልእና አሳየን እያሉ ተንጫጩ፡፡ ከዚያ ቶሎሳ ሮጦ መኪናው ጋ በመድረስ ከኋላው ዘሎ ወጥቶ ተንጠልጥሎ ሲጓዝ በድፍረቱ እና ባደረገው ነገር ተገርመው ተመልከቱት፡፡

ሾፌሩ ስላላየው ብዙ መንገድ ከተጓዘ በኋላ፣ መኪናው ፍጥነቱን ሲቀንስ ሰፈራቸው አካባቢ ደርሶ ስለነበር ዘሎ ወረደና ወደ ቤቱ ገብቶ ምሳውን ከበላ በኋላ የተሰጠውን የቤት ሰራ ሁሉ ሰርቶ ጓደኞቹ ሲመጡ ሊያሳያቸው እነሱ በሚመጡበት አቅጣጫ ሄዶ ቁጭ አለ፡፡

ጓደኞቹ ሲመጡ ስለጉዞውና የቤት ስራውን ሰርቶ መጨረሱን እየነገራቸው በጉብዝናው እየተዝናና ይስቅ ጀመር፡፡

ከብዙ ጊዜ በኋላ አንድ ቀን በተመሳሳይ ሁኔታ በሚተላለፍ መኪና ላይ ተንጠልጥለን እንሂድ ብሎ በነገራቸው መሠረት ቶሎሳ፣ ቢቂላና ከበደ የሚባሉ ጓደኛሞች ቀስ ብለው መኪናው ላይ ተንጠለጠሉ፡፡ ቶሎሳ “እስከአሁን ተሞኝተናል አያችሁ? መኪና ላይ መንጠልጠል ምንም አያስፈራም” በማለት ለጓደኞቹ እየነገራቸው ሳለ ሳያስበው ብረቱን የያዘበት እጁ ስላሚለጨው ከመኪናው ላይ ወደቀ” በቶሎሳ መውደቅ የተነሳ ጓደኞቹ ተደናግጠው ከሚበር መኪና ዘለን እንወርዳለን ብለው በማሰብ ሲዘሉ እየወደቁ ከፍተኛ አደጋ ደረሰባቸው፡፡

ድርፉጮ እና ሌሎች ልጆች ሰፈራቸው እንደደረሱ ስለ እነ ቶሎሳ ሁኔታ ለማወቅ ወደ ቤታቸው ቢሄዱ አጧቸው፡፡ በሁኔታው በመደንገጥ መኪናው ይዟቸው ሄዶ ይሆናል ብለው ለነቶሎሳ ወላጆች ተናገሩ፡፡ ወላጆቻቸውም ወዲያውኑ እነቶሎሳን ፍለጋ ሲሄዱ የሌላ መንደር ገበሬዎች በቃሬዛ ተሸክመው ሲያመጧቸው በማየታቸው በጣም ደነገጡ “ወይኔ ልጆቻችን ይህን ዓይነት አጉል ተግባር ማን አስተማረብን? እያሉ ቃሬዛዎቹን ተሸክመው ወደ መንደራቸው ተመለሱ፡፡

ቶሎሳና ከበደ በጣም ተጐድተው ስለነበሩ በማግስቱ በመሞታቸው መንደርተኛው ሁሉ በጣም አዘነ፡፡ ቢቂላ ህይወቱ ቢተርፍም ከባድ አደጋ ስለደረሰበት እግርና እጆቹ በመስበራቸው አካለ ጉደሎ ሆኖ በመቀረቱና እንደ ጓደኞቹ ት/ቤት ለመሄድ ባለመቻሉ እያዘነ ሁል ጊዜ ይተክዛል፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የዚህ መንደር ልጆች ተመሳሳይ የመኪና አደጋ እንዳይደርባቸው የወላጆቻቸውን ምክር በመስማት መኪና ላይ መንጠልጠል ተው፡፡

<u>የተግባር ጥያቄዎች</u>

<u>ለነዚህ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ</u>

1. ተማሪዎች ከዚህ ታሪክ እናንተስ ምን ትማራላችሁ?
2. ለአደጋው መፈጠር ቶሎሳ የፈፀመው ተግባር ምን ነበር?
3. እናንተስ ቢቂላን ወይም ከበደን ብትሆኑ ስላግባቧችሁ ብቻ እንደዚህ ዓይነት ተግባር ትፈጽማላችሁ?
4. በአካባቢያችሁ መኪና ላይ ተንጠልጥለው ሲሄዱ ያያችኋቸው ልጆች አሉ? ተግባራቸውስ ትክክል ነው ትላላችሁ?
5. ለነዚህ ዓይነት ልጆች ምን ምክር ትሰጧቸዋላችሁ?
6. ከድርፉጮ የምንማረው የጥንቃቄ ጠቃሚነት ነው ወይስ ፈሪነት?

## <u>12. መከለሻ ጥቅል ሀሳቦች</u>

- አካባቢያችሁን መገንዘብ ከቻላችሁ በአካባቢያችሁ ያሉትን ነገሮች በመጠቀም ህይወታችሁን ደስተኛ ማድረግ ትችላላችሁ፡፡
- እንደ አካባቢያችሁ ሁኔታ አደጋ ሊያስከትሉም ሆነ አደጋ ላያስከትሉ የሚችሉ ነገሮች ስለሚኖሩ ለይተን ማወቅ አለብን፡፡
- የመጓጓዣ አገልገሎት የሚሰጡ ነገሮች ባህላዊና ዘመናዊ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

- ባህላዊ የመጓጓዣ አገልግሎት የሚሰጡት የጋማ ከብቶች ይባላሉ፡፡
- ዘመናዊ የመጓጓዣ አገልገሎት ከሚሰጡት ነገሮች አንዱ መኪና ነው፡፡
- ጥቅም የሚሰጡ ነገሮችን በአግባቡ መጠቀም ካልቻልን ጉዳት ሊያስከትሉም ይችላሉ፡፡
- ለህይወታችሁ እና ለጤንነታችሁ ከፍተኛ ግምት በመስጠትና ከአደጋ በመጠንቀቅ አገራችሁን የምትጠቅሙ ዜጐች ለመሆን መጣር አለባችሁ፡፡
- የማታውቁትን እና አደጋ ሊያስከትል የሚችል ነገር ለመስራት ከመሞከር ይልቅ በቅድሚያ ለትላልቅ ሰዎች መንገሩ ይበልጥ ተመራጭ ነው ፡፡
- ሁሉም ነገር የራሱ የሆነ ደንብና ስርዓት እንዳለው መረዳት ይገባናል፡፡
- ከደንብና ስርዓት ውጭ ለመንቀሳቀስ ወይም ለማከናወን መሞከር በራስ ላይ አደጋ መጋበዝ ሊሆን ይችላል፡፡
- አቅጣጫዎች፤ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ሰሜንና ደቡብ ተብለው በአራት የተከፈሉ ናቸው፡፡
- በመንገድ ላይ በምንጓዝበት ወቅት አደጋ እንዳይደርስብን የሚያስችሉ እርምጃዎች የጥንቃቄ እርምጃዎች ይባላሉ፡፡
- ራሳችንን ከተለያዩ አደጋዎች መጠበቅ ያለብን እኛው እንጂ ሌላ ሰው እንዳማይሆን ማወቅ አለብን፡፡
- የእግረኛ መንገድ በሌለው የመኪና መንገድ ስንሄድ የመንገዱን ግራ ጠርዝ መያዝ እና መጓዝ አለብን፡፡
- መንገድ ለማቋረጥ ከመሞከራችን በፊት ወደግራ እና ወደቀኝ በማየት በድጋሚ ወደ ግራ አይተን መኪና ያልተቃረበ መሆኑንና በደህና ለማቋረጥ የምንችል መሆኑን ለይተን መሞከር ከአደጋ ሊያድን ይችላል፡፡
- የእግረኛ መንገድ ከመኪና መንገድ ዳርና ዳር የተስራ ከሆነ በዚያ መንገድ መጓዝ መልመድ አለብን፡፡
- የመኪና መንገድ ስናቋርጥ ማየት ያለብን በግራ አቅጣጫ መኪና አለመምጣቱን ብቻ ሳይሆን፣ መንገዱ መካከል ከደረስን በኋላ ወደ ቀኝ አቅጣጫ ዞረን መኪና አለመምጣቱን ሳናረጋግጥ ቀጣዩን ግማሽ መንገድ ለማቋረጥ መሞከር የለብንም፡፡
- የትራፊክ መብራት አረንጓዴው መኪናዎች እንዲንቀሳቀሱ መፍቀጃያ በመሆኑ እግረኞች መቆም አለባቸው፤ ቀዩ ሲበራ መኪናዎች እንዲቆሙ የሚያስገድድ በመሆኑ ለተሽከርካሪዎች ቀይ ሲበራ እግረኞች ተጠንቅቀው መንገዱን መሻገር ይችላሉ፡፡
- የትራፊክ መብራቶች እና የመንገድ ላይ ምልክቶች ከናንተ ቁመት ከፍ ያሉ በመሆናቸው ከማቋረጣችሁ በፊት ከአንገታችሁ ቀና ብላችሁ መመልከት ይኖርባችኋል፡፡
- መንገድ ከማቋረጣችሁ በፊት ሊገጥማችሁ የሚችል አደናቃፊ ነገር አለመኖሩን እርግጠኛ መሆን አለባችሁ፡፡
- መንገድ ከማቋረጣችሁ በፊት አሽከርካሪዎቹ እንዲያዩዋችሁ ወይም ሊያዩዋችሁ እንዲችሉ እርግጠኛ ሁኑ፡፡
- መኪና ላይ መንጠልጠል ከፍተኛ አደጋ ሊያደርስ እንደሚችል በማወቅ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባችኋል፡፡
- ጓደኞቻችሁ የሚመክሯችሁ ምክር ጥሩ ወይም መጥፎ መሆኑን ሳታመዛዝኑ መቀበል የለባችሁም፡፡
- ሳታመዛዛኑ የምታከናውኑት ነገር ሁሉ አሳዛኝ ፍፃሜ ሊኖረው እንደሚችል መገመት አለባችሁ፡፡
- መኪና ውስጥ በምትሆኑበት ጊዜ ሁልጊዜ ከኋለኛው ወንበር ላይ መቀመጥ ይኖርባችኋል፡፡
- መኪናው ውስጥ የጥንቃቄ ቀበቶ ካለ ቀበቶውን ማሰር የሚደርስባችሁን አደጋ በእጅጉ ሊቀንስ ይችላል፡፡

# መጽሐፍ፣ ክፍል ሁለት



ስዕል 19

*የትራፊክ ፖሊስ ከፊትና ከኃላ ሚመፁ ተሽከርካሪዎችን የሚጠቀመው ምልክት*

<u>መልዕክት</u>፡- *ጠንቃቃ ወጣት ራሱንም ሆነ ቤተሰቡን ያስደስታል*

## 1. በመኪና መንገድ ላይ የሚታዩ ነገሮች

በርካታ ነገሮች በመንገድ ላይ አሉ፡፡ በመንገድ ላይ የሚጓዙ ሰዎች፣ እንስሳት፣ በተለያየ ሀይል አማካኝነት የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች/መኪናዎች፣ ብስክሌቶች፣ ጋሪዎች…ወዘተ፣ በመንገድ ላይ ከሚታዩ ነገሮች ውስጥ ዋንኛዎቹ ናቸው፡፡

በመንገድ ዳር የተዘረጋ የኤሌክትሪክ መስመር እና የስልክ መስመር የሚታይባቸው መንገዶችም እንዳሉ እናውቃለን፡፡ ከመንገድ ዳር እና ዳር የተሰሩ የመኖሪያ ቤቶች፣ የንግድ ቤቶችና የተለያዩ መስሪያ ቤቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

በገጠር አካባቢዎች የተለያዩ ዛፎችና ቁጥቋጦዎች በመንገዶች ዳር እና ዳር በቅለው የሚታዩባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነዚህ እና ሌሎች በመንገድ አካባቢ ያሉ ነገሮች እግረኞች በሚጓዙበት ወቅት ትኩረታቸውን በመንገድ ላይ ብቻ እንዳያደርጉ ተጽዕኖ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

በመንገዶች ዳር ያሉ የተለያዩ ነገሮች ትኩረታችንን ሊስቡ የሚችሉበት ሁኔታ አለ፡፡ በመንገድ ዳር ባሉ ቤቶች ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን ሲፈጽሙ ያን ብቻ አትኩረን በማየት፤ በመንገዳችን ላይ መውሰድ ያሉብንን ጥንቃቄዎች እንዳናደርግ ሊያዘናጉን ይችላሉ፡፡ ዛፎችና ቁጥቋጦዎች ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ነገሮችን በማየት ትኩረታችንን ልንቀንስ የምንችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በመንገድ ዳር ያሉ የኤሌክተሪክና የስልክ ተሸካሚ ቋሚ እንጨቶች ትኩረት ካላደረግን ሊገጩንና አደጋ ሊያደርሱብን ይችላሉ፡፡

ተገቢውን ትኩረትና ጥንቃቄ ካላደረግን በመንገድ ላይ ከሚጓዙ ሰዎች ጋር ልንጋጭ እንችላለን፡፡ በመንገድ ላይ የሚጓዙ እንስሳት በመዋጋትና በመራገጥ አደጋ ሊያደርሱብን ይችለሉ፡፡ ጥንቃቄ ካልተወሰደ መኪናዎች እጅግ አስቃቂና ከፍተኛ አደጋ እንዲደርስብን ሊያደርጉ የሚችሉባቸው ሁኔታዎችም አሉ፡፡

ስለዚህ ከቤታችን ወጥተን በምንጓዝበት ወቅት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡ አደጋ በተለያዩ ነገሮች አማካኝነት ሊደርስ ስለሚችል በጉዞ ወቅት ሙሉ ትኩረታችንን በመንገድ ላይ በማድረግ መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ልጆች በመንገድ ላይ በምትጓዙበት ወቅት ጥንቃቄ መውሰድ እንደሚገባችሁ ተገነዘባችሁ? እስኪ ቀጥለን ይህን እውነተኛ ታሪክ እናንብብ፡፡

## 2. የመርካቶው አደጋ

ጊዜው ክረምት ነበር፡፡ ቦታው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ መርካቶ ተብሎ በሚጠራው ታዋቂዉ የገበያ ማእከል ነው፡፡ዝናብ እየዘነበ በመሆኑ ዝናቡን ለማምለጥ ሰዎች ሁሉ መጠለያ ወደ ሚያገኙበት አቅጣጫ ይሮጣሉ፡፡ዝናቡ ፊታቸውን እንዳይመታው አጐንብሰው ነበር የሚሮጡት፡፡ ሰዎች ከዝናቡ ለማምለጥ አጐንብሰው በየአቅጣጫው ሲሯሯጡ በተቃራኒ አቅጣጫ ከሚሮጡት ሰዎች ውስጥ ሁለቱ ግንባር ለግንባር ተጋጩና ወደቁ፡፡ ፍጥነት ስለነበራቸው እና ግጭቱም ከፍተኛ በመሆኑ ሁለቱም ሰዎች ከወደቁበት ተነስተው ሊሄዱ አልቻሉም ነበር፡፡ ሁኔታውን ያዩ ሰዎች ደረሱና አነሷቸው፡፡ ነገር ግን አደጋው ከፍተኛ በመሆኑ ሁለቱም ሰዎች ወደ ሐኪም ቤት ተወሰዱ፡፡ ህይወታቸውንም ለማትረፍ ከፍተኛ ሙከራ ተደረገ፡፡ ሆኖም አንደኛው ሰው በግጭቱ በጣም ተጎድቶስለነበረና ጭንቅላቱ ውስጥ ደም ፊሶት ስለነበር ህይወቱ አለፈች፡፡ ይህ ታሪክ የተፈፀመና እውነተኛ ታሪክ ነው፡፡ ከዚህ ታሪክ ምን ትገነዘባላችሁ?

አዎን አደጋ በተለያዩ ነገሮች አማካኝነት ሊደርስ እንደሚችል እንገነዘባለን፡፡ ዝናብ ቢያበስብሰን ልብሳችን ይደርቃል፡፡ ነገረ ግን ይህን ትንሽ ችግር ለማምለጥ ስንሞክር ከፍተኛ አደጋ ውስጥ

እንዳንወድቅ ማሰብ ይገባናል፡፡ ብዙ ልጆች ዝናብ ሲመጣ ከዝናቡ ለማምለጥ እንጂ የተለያዩ አደጋዎች ሊደርስባቸው እንደሚችል ባለማሰብ የመኪና መንገድን በሩጫ ለማቋረጥ ሲሞክሩ ይታያሉ፡፡

ጥንቃቄ እና ተገቢ ትኩረት ባለማድረግ የሚፈፀም እንቅስቃሴ ሁሉ ከተለያዩ ነገሮች ጋር እንድንጋጭ ሊያደርገን ይችላል፡፡ ስለዚህ በጉዞአችን ወቅት የጥንቃቄ እርምጃዎችን በተገቢው መልኩ መፈፀም ይገባናል፡፡

## <u>እነዚህን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው</u>

1. ከዚህ ታሪክ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሌላ የምታውቁት ታሪክ አለ? እናንተ የምታውቁት ታሪክ ከሌለ ከታላላቆቻችሁ ወይም ከወላጆቻችሁ በመጠየቅ በክፍል ውስጥ ተወያዩበት፡፡
2. በመኪና መንገድ ላይ እና በአካባቢው የሚታዩ ነገሮች በምን ሁኔታ ትኩረታችንን ሊሰቡ እንደሚችሉ እየገለፃችሁ ተወያዩ፡፡
3. በመንገድ ላይ ስንጓዝ አደጋ ሊደርስብን የሚችለው በመኪና ብቻ ነውን? ሌሎች አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ግለፁ?
4. በመንገድ ስንጓዝ አደጋ እንዳይደርስብን ምን ማድረግ ይገባናል?

## <u>መዝሙር</u>

ተማሪዎች - በሁለት ምድብ በመከፈል የመጀመሪያው ምድብ ውስጥ ያላችሁ ልጆች የኮከብ ምልክት (*) የተደረገበትን ሀረግ ሲዘምሩ፣ በሁለተኛው ምድብ ያላችሁ ልጆች በመደመር (+) ምልክት ስር የተፃፈውን የግጥም ሀረግ በመዘመር እየተቀባበላችሁ መዝሙሩን ዘምሩ፡፡ መዝሙሩን ክፍል ውስጥ ብቻ ሳይሆን ለወላጆቻችሁ እና ለታላላቆቻችሁ ጭምር ዘምራችሁ በማሰማት ጠንቃቃ ልጆች መሆናችሁን ግለፁላቸው፡፡

### <u>ከአደጋ እንጠበቅ</u>

* ተሽከርካሪ የሚጓዘው
\+ በጐማ ነው፣ በጐማ ነው፡፡
* የሰው ልጅ ሚጠቀመው፣
\+ በእግሩ ነው፣ በእግሩ ነው፡፡
* ፍጥነት አለው ተሽከርካሪ፣
\+ ካለው በላይ ነው በራሪ፡፡
* መጠንቀቅ ነው የሚያድነን፣
\+ በመንገድ ላይ ከአደጋ እንድንድን፡፡
* አዎን ልጆች
እንጠንቀቅ፣ እንጠንቀቅ
\+ ራሳችንን ከአደጋ
እንጠብቅ፣ እንጠብቅ፡፡
* ራሳችንን ከአደጋ፣
እንጠብቅ፣ እንጠብቅ፡፡

## <u>3. በተሽከርካሪ ነገሮች የሚደርሱ አደጋዎች</u>

ተሽከርካሪ ነገሮች የሚባሉት በተገጠመላቸው ጐማ አማካኝነት የሚሽከረከሩ ነገሮች ናቸው፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች የመሽከርከሩን ኃይል የሚያገኙት ከተለያዩ ነገሮች ነው፡፡ ለምሳሌ መኪናዎች በሞተር አማካኝነት የሚንቀሳቀሱ ሲሆን ሞተራቸው የሚሠራው በነዳጅ ኃይል ነው፡፡ ለመኪናዎች ማንቀሳቀሻ በአብዛኛው በአሁኑ ጊዜ የምንጠቀመው የነዳጅ ኃይል ሁለት ዓይነት ሲሆን እነዚህም ቤንዚን እና ናፍታ ተብለው ይጠራሉ፡፡

በነዳጅ ኃይል አማካኝነት የመኪናዎች ሞተር ሲንቀሳቀስ፤ በሞተሩ ኃይል ደግሞ በመኪናዎቹ ውስጣዊ አካላት ላይ በሚያሳርፈው ከፍተኛ ጉልበት የተገጠመላቸውን ጐማዎች እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋል፡፡

በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀሱ መኪናዎች የሰዎችን ስራ በማቃለል ከቦታ ወደ ቦታ ሰዎችንም ሆነ ዕቃዎችን በማጓጓዝ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሰጡ ሲሆን ጥንቃቄ ካልታከለባቸው በሰዎች ህይወትም ሆነ አካል እንዲሁም በንብረት ላይ የሚያደርሱት አደጋ ከፍተኛ ነው፡፡


## 4. መኪናዎች አደጋ የማያደርሱባቸው ምክንያቶች

በመኪናዎች አማካኝነት አደጋ የሚደርስው በተለያዩ ምክንያቶች ነው፡፡ ከነዚህም ምክንያቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ሊሆኑ የሚችሉት፡-

1ኛ. አሽከርካሪዎች ጥንቃቄ ባለማድርጋቸው የተነሳ በእግር ሆነው በመንገድ ላይ የሚጓዙ ሰዎችን በመግጨት አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ሰዎች በመኪና ሲገጩ ሁኔታው ከፍተኛ ከሆነ ህይወትን ማጣት ሊያስከትል ይችላል አደጋው ከህይወት መጥፋት በተጨማሪ ከባድና ቀላል የአካል ጉዳትንም ሊያስከትል የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

2ኛ. የመኪና አደጋ የሚደርሰው በአሽከርካሪዎቹ ጥንቃቄ አለማድረግ ብቻ ሳይሆን እግረኞችም ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረግ በመኪና መንገድ ውሰጥ ገብተው ሲጓዙ ወይም መንገድ ሲያቋርጡ አደጋ ሊደርስ ይችላል፡፡ የመኪና መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል፡፡

ተገቢ ጥንቃቄ ከሚባሉት ውስጥ መንገድ ከማቋረችን በፊት መውሰድ የሚገባንን ጥንቃቄ ማድረጋችን ህይወታችን በመኪና አደጋ እንዳይቀጭ ሊረዳን ይችላል፡፡ በመኪና መንገድ ላይ እግረኞች እንዲተላለፉበት ተለይቶ የተመለከተ አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ነጭ ቀለም የተቀባ የእግረኞች ማቋረጫ፣ በእንግሊዘኛው ቋንቋ "ዜብራ" የተቀባባቸው የመንገድ ማቋረጫ ምልክቶች ያሉት ከሆነ መኪና በቅርብ ርቀት አለመኖሩን ግራና ቀኙን ዞር ዞር ብለን በማየት በዚያ ማቋረጥ ይበልጥ ተመራጭ ነው፡፡



**ስዕል 20**
**የመኪና እንቅስቃሴ መፍቀጂያ የመብራት ምልክት**

ነገር ግን ልናቋርጥ ባሰብንበት አካባቢ ይህ ምልክት የተቀባበት መንገድ ከሌለ፤ቀድመን ወደ ግራ እና ቀኝ በማየት በድጋሚ በፍጥነት ወደ ግራ በማየት መንገዱ ከመኪና የፀዳ መሆኑን ወይም በፍጥነት ሊደርስብን የሚችል መኪና አለመኖረን ሳናረጋግጥ ለማቋረጥ መሞከር አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ አለብን፡፡

3ኛ. መኪናዎች ለሰው ልጅ በተሟላ መልኩ አገልገሎት የሚሰጡት ተገቢው ክትትልና እድሳት ሲደረግባቸው ነው፡፡ ብዙ ዘመን ያገለገሉ መኪናዎች መቆጣጠሪያዎቻቸው በተሟላ ሁኔታ ስለማይሰሩ አደጋ የሚያደረሱበት ሁኔታ ከፍተኛ ነው፡፡ ፍሬናቸው በተገቢው ሁኔታ ላይሰራ ይችላል፡፡ ፍሬቻቸው የተሟላ ላይሆን ይችላል፡፡ እነዚህንና ሌሎች የመኪናው አካላት በተገቢው ሁኔታ ካልሰሩ ለአደጋ መፈጠር ምክንያት ይሆናሉ፡፡

4ኛ. መኪናዎች የሚጠቀሙባቸው መንገዶች በራሳቸው ለመኪና አደጋ መፈጠር አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ በጥሩ ሁኔታ የተሰሩ መንገዶች አሽከርካሪዎች በፍጥነት እንዲነዱ ስለሚገፋፋቸው የጥቂት ሴኮንዶች መዘናጋት ከተከሰተ መኪናውን ተቆጣጥሮ አደጋ እንዳይደርስ ለማድረግ ከፍጥነታቸው የተነሳ ሙሉ በሙሉ አይቻልም፤ ከዚህም በላይ ከፍጥነቱ የተነሳ መኪናው ፍሬን ተይዞም ሊንሸራተትና ሊገለበጥ ወይም ሊጋጭ ስለሚችል ከፍተኛ የሆነ አደጋ ሊያደርስ ይችላል፡፡

በጥሩ ሁኔታ ያልተሰሩ መንገዶች፣ ጠመዝማዛ መንገዶች፣ ቁልቁለትና ዳገትማ የሆኑ መንገዶች፣ እይታን የሚጋርዱ ቤቶች፣ ተክሎች፣ ወይም ኮረብታ ካለ ሾፌሩ ጥንቃቄ ካላደረገ ለአደጋ ያጋልጣሉ፡፡ ዝናብ ካለ ተሽከርካሪው በፍጥነት ከተጓዘ ሊንሸራተት ይችላል፡፡ በጨለማም ወቅት እይታው ስለሚቀንስ በእግረኞችም ላይ አደጋ ሊያደርስ ይችላል፡፡ ሾፌሩ እነዚህ ሁኔታዎች የአደጋ መንስኤ መሆናቸውን ሳይገነዘብ በፍጥነት የሚያሽከረክር ከሆነ ወይም በመንገዱ ሁኔታ ላይ ጥንቃቄ አድርጎ ካላሽከረከረ ባልታሰበ ቅጽበት ወደ መኪና መንገድ የሚገባ ሰው ለአደጋ የተጋለጠ ሊሆን ይችላል፡፡

የእግረኛ መንገድ የተለየና ምቹ ባልሆነባቸው ቦታዎች ሰዎች የመኪና መንገድ ውስጥ ገብተው ሲጓዙ ይታያሉ፤ ይህ የመንገድ ሁኔታ የፈጠረው ችግር ለአደጋ መፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

ስለዚህ የመኪና መንገድ በምናቋርጥበትም ሆነ በመኪና መንገድ ተጠቅመን በምንጓዝበት ወቅት በተሽከርካሪዎች አማካኝነት አደጋ እንዳይደርስብን የበለጠ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል፡፡

## 5. መንገድ ስንጠቀም መውሰድ የሚገባን ጥንቃቄ

በመኪና መንገድ ጐን ለጐን የተሰራ የእግረኛ መንገድ ካለ ሁል ጊዜ ያን መንገድ መጠቀም አለበን፡፡ የእግረኛ መንገድ በሌለበት በመኪና መንገዱ ላይ መሄድ ከተገደድን የግራ ጠርዙን ይዘን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ምክንያቱም መኪናዎች የሚጓዙት የመንገዱን ቀኝ አቅጣጫ ይዘው በመሆኑ፣ እኛ የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዘን የምንጓዝ ከሆነ የሚመጡትን መኪናዎች ፊትለፊት በማየትና የአመጣጥ ሁኔታቸውን በማመዛዘን አደጋ እንዳያደርሱብን ተገቢውን ጥንቃቄ ለማድረግ ያመቸናል፡፡



ስዕል 21
**ትክክለኛ መንገድ አጠቃቀም**

በመንገድ ቀኝ ጠርዝ የምንጓዝ ከሆነ፣ መኪናዎችም የመንገድን ቀኝ አቅጣጫ ይዘው ስለሚጓዙ ከኋላችን የሚመጣውን መኪና ስለማናይ እና ተገቢውን ጥንቃቄ ልናደርግ ስለማንችል አደጋ ሊያደርስብን ይችላል።




ስዕል 22
**የተሳሳተ የእግረኛ መንገድ አጠቃቀም**

የመኪና መንገድ ማቋረጥ ካስፈለገን ከላይ በተገለፀው መሠረት ተገቢውን ጥንቃቄ በመውሰድ ግራና ቀኛችንን ዞር ዞር ብለን በማየት፣ መንገዱ ከመኪና እንቅስቃሴ የፀዳ መሆኑን ሳናረጋግጥ ሮጠን ማቋረጥ እንችላለን በሚል ግምት የመኪና መንገድ ለማቋረጥ መሞከር የሚያስከትለው አደጋ ከፍተኛ ይሆናል።

አደጋ ከሚያደርሱብን ተሽከርካሪዎች ውስጥ በሰው ኃይል የሚንቀሳቀሱ ብስክሌቶችም በተሽከርካሪ ክፍል የሚመደቡ ናቸው። በእንስሳት አማካኝነት እየተጐተቱ የሚሽከረከሩ ጋሪዎች በመኪና መንገድ ተጠቃሚ እግረኞች ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮች ናቸው።በመሆኑም መንገድ ላይ በምንጓዝበት ጊዜም ሆነ መንገድ ስናቋርጥ አሽከርካሪዎች ሁልጊዜ ጥንቃቄ ሊያደርጉልን ይችላሉ በሚል የተሳሳተ ግምት የምንቀሳቀስ ከሆነ አደጋ ሊደርስብን ይችላል።





ስዕል 23

ሰዎች ከተለያዩ አደጋዎች ራሳቸውን መጠበቅ ይገባቸዋል እንጂ ሌሎች ይጠነቀቁልኝ ይሆናል በሚል አስተሳሰብ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ከሆነ ምንም ጊዜ ራሳቸውን ከአደጋ ሊጠብቁ አይችሉም፡፡

አደጋ ከደረሰብን ህይወታችንን ልናጣ እንችላለን ወይም ከፍተኛ የሆነ የአካል መጉደል አደጋ ሊገጥመን ይችላል፡፡ ስለዚህ ወላጆቻችን ሀዘን ላይ እንዳይወድቁ፤ እኛም ጠንካራ እና ብርቱ ሆነን፣ ሙሉ አካል ይዘን ሀገራችንን ልንጠቅም የምንችለው ጠንቃቆች ሆነን ስንገኝ በመሆኑ ከአደጋ ራሳችንን ለመጠበቅ ተገቢውን የመንገድ አጠቃቀም ስርዓት መከተል ይኖርብናል፡፡

## አደጋ ከደረሰብን ህይወታችንን ልናጣ እንችላለን

ልጆች አደጋ እንዳይደርስባችሁ ንቁ፣ ጠንቃቃና ጉበዝ መሆን ይገባችኋል፡፡

## ተግባራት

**ተግባር አንድ**

**ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ ብቻ ምረጥ**

1. ተሽከርካሪዎች የሚንቀሳቀሱት በምን ሀይል ነው፡፡
   - ሀ. በሞተር ሀይል
   - ለ. በሰው ኃይል
   - ሐ. በእንስሳት ኃይል
   - መ. ሁሉም

2. አደጋ እንዳይደርስባቸው እግረኞች መወሰድ ያለባቸው ጥንቃቄ
   - ሀ. የመኪና መንገድ ውስጥ ገብቶ መጓዝ
   - ለ. የመንገዱን ቀኝ ጠርዝ ይዞ መሄድ
   - ሐ. የእግረኛ መንገድ ይዞ መጓዝ
   - መ. ተገቢውን ጥንቃቄ አለማድረግ

3. የመኪና አደጋ ሊደርስ የሚችለው
   - ሀ. አሽከርካሪዎች ጥንቃቄ ስለሚያደርጉ
   - ለ. ሳይጠነቀቁ እግረኞች በመኪና መንገድ ውስጥ ገብተው የሚጓዙ ከሆነ
   - ሐ. መኪና አለመኖሩን ሳያረጋግጡ የመኪና መንገድን ለማቋረጥ በሚደረግ ሙከራ
   - መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

4. አደጋ ምን ያስከትላል?
   ሀ. ህይወት ያሳጣል
   ለ. አካለ ጐደሎ እንድንሆን ሊያደርገን ይችላል
   ሐ. ወላጆቻችን እንዲያዝኑ ሊያደርግ ይችላል
   መ. ሁሉም መልስ ይሆናል

5. አደጋ እንዳይደርስብን መውሰድ ከሚገባን ጥንቃቄ ውስጥ ያልሆነው ሀሳብ የቱ ነው?
   ሀ. የመንገዱን ግራ አቅጣጫ በትኩረት ይዞ መጓዝ
   ለ. ዜብራ በተቀባበት መንገድ በኩል በጥንቃቄ ማቋረጥ
   ሐ. የመንገዱን ቀኝ ጠርዝ ይዞ መጓዝ
   መ. መንገድን በፍጥነት ላቋርጥ እችላለሁ ብሎ አለማሰብ

<u>ተግባር ሁለት</u>

<u>ትክክለኛ የሆነውን ሀሳብ እውነት፣ ትክክለኛ ያልሆነውን ስህተት ብላችሁ መልስ ስጡ፡፡</u>

1) የመኪና አደጋ የሚደርስው ተገቢውን የመንገድ አጠቃቀም ስርዓት ስንከተል ነው፡፡
2) አደጋ እንዳይደርስብን ከኛ ይልቅ አሽከርካሪዎች ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፡፡
3) በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ከፍተኛ አደጋ ሊያደርሱብን ይችላሉ፡፡
4) በእንስሳት የሚጐተቱ ጋሪዎች አደጋ ሊያደርሱ አይችሉም፡፡
5) መኪና እንዲንቀሳቀስ የሚያስችል ኃይል የሚገኘው ከተለያዩ ዓይነት ነዳጅ ነው፡፡

<u>ተግባር ሶስት</u>

<u>የተነሱትን ጥያቄዎች መሠረት በማድረግ ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ ግለፁ</u>

1. በተሽከርካሪዎች አማካኝነት የደረሰ አደጋ ስምታችሁ ታውቃላችሁ? አይታችሁ ወይም ስምታችሁ ከሆነ በምን ምክንያት እንደተከሰተ ለጓደኞቻችሁ ግለፁላቸው፡፡
2. ተሽከርካሪዎች አደጋ የሚያደርሱት በሰዎች ላይ ብቻ ነው ወይስ በእንስሳትና በሌሎች ነገሮችም ላይ አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ? በምን ላይ አደጋ እንደሚያደርሱ ብትገልፁ፡፡
3. በአካባቢያችሁ ባለ የመኪና መንገድ የእግረኛ ማቋረጫ ምልክት ተጠቅማችሁ መንገድ የምታቋርጡ ከሆነ መውስድ ያለባችሁ ጥንቃቄ ምንድነው?
4. በአካባቢያችሁ ያሉ የመኪና መንገዶች የእግረኛ መሄጃ የተለየ መንገድ አላቸው? ከሌላቸው በምን ሁኔታ ነው የምትጓዙት?
5. የተሽከርካሪ አደጋ የሚደርሰው በምን በምን ምክንያት እንደሆነ ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየትና መወሰድ ያለበት ጥንቃቄ ምን ሊሆን እንደሚገባው በመግለጽ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

ይህን መዝሙር ከጓዳኞቻችሁ ጋር በመሆን ዘምሩ፡፡ ለመዝሙሩ የሚሆን ዜማ የሙዚቃ መምህራችሁ እንዲያወጡላችሁ ጠይቋቸው፡፡

<u>ጥንቁቅ ነኝ ጉበዝ ልጅ</u>

እያየሁ እጓዛለሁ፣
ከአደጋ እጠበቃለሁ፡፡
የመንገዱ ግራ አቅጣጫ፣
ለኔ ጉዞ አለው ብልጫ፡፡
ጠንቃቃ ነኝ ትጉህ ወጣት፣
ተጠንቀቁ የምጫወት፡፡
መኖርን እፈልጋለሁ፣
ስለዚህ እጠነቀቃለሁ፡፡
አንተም ሁን ጠንቃቃ
በአደጋ እንዳትጠቃ፡፡

ከዚህ መዝሙር ምን ትምህርት እናገኛለን? ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

## 6. ድራማ፡- የመኪና መንገድ ላይ የእግር ኳስ ጫወታ

ይህን ድራማ ለመስራት ከጓደኞቻችሁ ጋር ተነጋገሩ እና በፍቃደኝነት ሊሰሩ የሚፈልጉትን ገፀባህርይ እንዲመርጡ አድርጉ፡፡ ሁኔታውን መምህራችሁ በማስተካከል እንዲረዷችሁ ትብብራቸውን ጠይቋቸው፡፡

**ተዋንያን**

1. ከበደ
2. ቶሎሳ
3. ሀጐስ
4. ዴንሰሞ
5. የሀጐስ እናትና አባት
6. የሰፈር ሽማግሌ
7. ሌሎች ሰዎች
8. እንደ መኪና የሚንቀሳቀሱ ልጆች

**ክንውን አንድ**

- ረፋድ ላይ ነው፡፡ ከበደ፣ ቶሎሳ፣ ዴንሰሞና ኃጐስ ቤታቸው ፊት ለፊት ካለው የመኪና መንገድ ላይ የእግር ኳስ ይጫወታሉ፡፡
- ዴንሰሞ የመኪናዎችን መብዛት አይቶ ጨዋታው ይቅርብን ሲል ከበደ እንጫወት በማለቱ ጫወታውን ቀጠሉ፡፡
- ሀጐስ ኳሷን ብቻ እያየ ሲሮጥ አንድ መኪና ሳያስበው አጠገቡ ደረሶበት፡፡ አሽከርካሪውም ፈጥኖ ፍሬን ቢይዝም ሊያድነው ባለመቻሉ ሀጐስን ገጨው፡፡
- ሀጐስ በመኪና በመገጨቱ ብዙ ሰዎች ተሰባሰቡ፡፡
- ሌሎች መኪናዎች በሁኔታው ድንገተኛነት የተነሳ ፍሬን ለመያዝ ቢሞክሩም እየተንሸራተቱ እርስ በርሳቸው ተጋጩ፡፡
- አንድ የቤት መኪና ውስጥ፣ ከፊት ተቀምጦ የነበረ ህፃን፣ መኪናዎቹ አርስ በርስ ሲገጫጩ ተሰፈንጥሮ ከመስታወቱ ጋር በሀይል በመላተሙ ወዲያውኑ ሞተ፡፡
- በርካታ አሽከረካሪዎችና ተሳፍሪዎች የጥንቃቄ ቀበቶ ባለማሰራቸው የመቁሰልና የመጐዳት አደጋ ደረሰባቸው፡፡

**ክንውን ሁለት**

ከበደ፣ ቶሎሳና ደንሰሞ በጣም ተጨነቁና አሁን ለሀጐስ ወላጆች ማን ይናገር እያሉ ተጨቃጨቁ፡፡ አንተ ሂድ፣ አንተ ሂድ፣ ያንተ ጥፋት ነበር እየተባባሉ ቢነጋገሩም ከሶስቱም ፈቃደኛ የሆነ አልነበረም፡፡ በዚህ መካከል ሰዎች አደጋውን ሰምተው ተሯሩጠው መጡ፡፡ ከሰዎቹ ውስጥ የሀጐስ እናትና አባትም ነበሩ፡፡ የሀጐስ እናት ልጃቸው እንደተገጨ ሲያውቁ “ልጄን ምን አደረጋችሁብኝ? እሱ እንዲህ ያለ አመል አልነበረውም፣ እናንተ ናችሁ ለአደጋ የዳረጋችሁኝ” በማለት ልጆቹ ላይ ጮሁ፡፡

ከተሰባሰቡት ሰዎች አንዱ አዛውንት ተነሱና “ከመጀመሪያውስ ቢሆን ልጆቻችሁ የት እንደሚጫወቱ ለምን ክትትል አታደርጉም ነበር” ብለው ተናገሩ፡፡ የተሰበሰቡትም ሰዎች በሁኔታው መከሰት በጣም አዘኑ ፡፡

**<u>የግንዛቤ ጥያቄዎች</u>**

**<u>አጭርና ግልፅ መልስ ለያንዳንዱ ጥያቄ ስጡ</u>**

1. ዴንሰሞ ጫዋታውን እናቁም ብሎት የነበረውን ሀሳብ ለምን ቀየረ?
2. ሃጎስ የመኪናዎቹን መምጣት ያልተመለከተው ለምን ይመስላችኋል?
3. አደጋው መከሰት ስህተት የፈፀመው አሽከርካሪው ነው ወይስ ልጁ? እንዴት አብራሩ
4. የሀጎስ ጎደኞች ለምንድን ነው የሀጎስ ወላጆች ጋር መሄድ የፈሩት?
5. እናንተስ ይህን ዓይነት አጋጣሚ እንዳይደርስባችሁ ምን ማድረግ አለባችሁ?
6. ተመሳሳይ አደጋ ሲደርስ ብታዩ ከወላጆቻችሁ ጋር በግልፅ ትነጋገራላችሁ?
7. እናንተ በዴንሰሞ ቦታ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?
8. ከአስፋልት ዳር ሆኖ ኳስ መጫወት የሚያስከትለው የመኪና አደጋ አይኖርም፡፡
9. አደጋ እንዳይደርስብን ወላጆቻችን ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል ብላችሁ ታስባላችሁ?
10. ከድራማው ያገኛችሁት ትምህርት ምንድን ነው?

## <u>7. መኪና ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ መውሰድ ያለብን ጥንቃቄ</u>

በተሳፋሪነት መኪና ውስጥ ሆነን ስንጓዝ መውሰድ የሚገባን የጥንቃቄ እርምጃዎች አሉ፡፡ ከነዚህ የጥንቃቄ እርምጃዎች ውስጥ የተወሰኑትን እንይ፡

-

- መኪና ውስጥ ለመግባት ወይም ከመኪና ውስጥ ለመውጣት ከመሞከራችን በፊት የተሳፈርንበትን መኪና ሙሉ በሙሉ መቆሙን እርግጠኛ መሆን አለብን፡፡
- ከመኪና ውስጥ ስንወርድም ሆነ ስንሳፈር አደጋ እንዳይደርስብን መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ መጠንቀቅ የሚገባን እኛ ላይ ብቻ አደጋ እንዳይደርስ ሳይሆን ሌሎች በመንገድ ላይ ተጠቃሚ ሰዎችም አደጋ እንዳይደርስባቸው ጭምር መሆን አለበት፡፡
- ከመኪና ውስጥ ለመውረድ መጠቀም ያለብን በመንገዱ ጠርዝ በኩል፣ ማለትም በመንገዱ ቀኝ ጠርዝ በኩል ያለውን የመኪና በር መሆን ይገባል፤ ምክንያቱም በመንገዱ ቀኝ ጠርዝ ተቃራኒ አቅጣጫ ያለውን በር በችኮላ እና አካባቢያችንን ሳንቃኝ ከፍተን ለመውረድ ስንሞክር ከኋላችን የሚመጣ መኪና ሊገጨንና አደጋ ሊያደርስብን ይችላል፡፡



ስእል 24

**በግራ በር በኩል መውረድ ከተፈለገ ስንከፍት ጥንቃቄ ማድረግ አለብን**

- ሁል ጊዜ፣ እንደልምድ በመያዝ፣ በተቻለ መጠን ከመንገዱ ቀኝ ጠርዝ በኩል ያለውን የመኪና በር ከፍቶ መውረድ የሚመረጥ ይሆናል፤ ይህ የማያመች ከሆነ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ በተቃራኒው በኩል ባለው በር መውረድ ይቻላል፡፡



ስእል 25
**በመንገዱ ቀኝ ጠርዝ በኩል በር ከፍቶ መውረድ**

- ከመንገዱ ቀኝ ጠርዝ ያለውን በር ከፍተን መውረድ የሚመረጥ ቢሆንም በዚህ ጠርዝ በኩል ያለውን የመኪና በር ስንከፍት የመንገዱን ጠርዝ ይዘው የሚጓዙ እግረኞችን በበሩ እንዳንመታ ወይም አደጋ እንዳናደርስ ትኩረት ማድረግ አለብን፡፡
- መኪና ውስጥ በምትቀመጡበት ወቅት ከፊት ለፊት ባለው ወንበር ላይ መቀመጡ፣ በአጋጣሚ አደጋ ቢደርስ የአደጋውን ሁኔታ ይበልጥ አስከፊ ሊያደርገው ይችላሉ፡፡ በእንቅስቃሴው የተነሳ ህፃናት ፊት ለፊት ካለው መስታወት ጋር ሊጋጩ እና ሊጎዱ ይችላሉ፤ በመሆኑም ህፃናት ከኋለኛው ወንበር በመሃል ባለው ቦታ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በብዙ የአውሮፖ አገሮች ዕድሜያቸው ከ10 ዓመት ያልበለጡ ህፃናትን ከፊት ወንበር አስቀምጠው በሚጓዙ አሽከርካሪዎች ላይ ተገቢውን ቅጣት ይቀጣሉ፡፡
- እኛ ሀገር ጥቅም ላይ ውሎ ባይታይም በሌሎች አንዳንድ ሀገሮች ህፃናት የሚቀመጡበት የተለየ መቀመጫ አለ፡፡ ይህ የህፃናት መቀመጫ በቤት መኪና ከሆነ ከሹፌሩ በኃላ ባለው ወንበር ላይ በማስቀመጥ በራሱ ማሰሪያ ከዋናው የመቀመጫው አካል ጋር እንዲታሰር ይደረጋል፡፡
- ይህ የተለየ መቀመጫ ህፃናትን እቅፍ እድርጐ ስለሚይዝ ተመራጭ ሲሆን በዚህ ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑም ህፃናቱ ጭምር የደህንነት ቀበቶ እንዲያስሩ ይደረጋል፡፡
- በአገራችን አንዳንድ ሰዎች የደህንነት ቀበቶ አስረው መኪና ሲያሽከረክሩ ይታያሉ፡፡ እስከሁን ያለው የአገራችን የትራፊክ ማስከበሪያ ህግ የደህንነት ቀበቆ አሽከርካሪ እና ተሳፍሪ ሁሉ እንዲያስር የሚያስገድድ ባይሆንም ወደፊት እንደማንኛውም የዳበሩ አገራት ሁሉ የደህንነት ቀበቶ ሳያስሩ መጓዝ የማይቻል መሆኑን የሚያስገድድ የትራፊክ ህግ ይወጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 8. የደህንነት ቀበቶ ማሰር የሚኖረው ጠቀሜታ

መኪና ውስጥ ሆነን በምንጓዝባቸው ጊዜያት ሁሉ የደህንነት/የጥንቃቄ/ ቀበቶ መታጠቅ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው፡፡ ጉዞው አጭር ቢሆንም እንኳን ቀበቶውን ማሰር አለብን፡፡ አደጋ በሚደርስበት ጊዜ ቀበቶ ያላሰሩ ሰዎች የሚደረስባቸው አደጋ ከፍተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ 50 ኪ.ሜትር በሰዓት የሚበር መኪና አደጋ በሚያጋጥመው ጊዜ አንድ ሰው ከክብደቱ 20 ጊዜ በበለጠ ክብዶ ወደፊት በመፈናጠር ይጋጫል፡

ይህንን ሃሳብ ሰፋ አድርገን በማየት ተሳፋሪው ክብደቱ 25 ኪሎ ግራም ቢሆን ከላይ በተገለፀው ፍጥነት የሚሽከረከር መኪና ተሳፍሮ ግጭት ቢደርስበት ተሳፋሪው የሚደርስበት የግጭት ሃይል የ5 ኩንታል ወይም 500 ኪሎ ግራም ያህል ክብደት ይኖረዋል፡፡ በዚህ ክብደት ወደ ፊት የተወረወረ ተሳፋሪ /ነገር/ ከፊት ካለው ነገር ጋር በሚፈጠረው መጋጨት አደጋው ከፍተኛ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ይህን በሌላ መልክ ስናየው፤ በሰዓት 50 ኪሎ ሜትር የሚጓዝ መኪና በግጭት ወቅት በተሳፋሪው ላይ የሚፈጥረው አደጋ ከ3ኛ ፎቅ ላይ ከመውደቅ ያልተናነሰ አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል በትራፊክ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

ተሳፋሪው የደህንነት ቀበቶ ያሰረ ከሆነ ከተቀመጠበት ቦታ ስለማይንቀሳቀስ ከመጋጨት ስለሚያተርፈው ከባድ የሆነ ጉዳት ላያስከትልበት ይችላል፡፡

የአዋቂዎች ህፃናትን በክንዳቸው አቅፈው ስለያዙ ብቻ በአደጋ ጊዜ ሊያድኗቸው አይችሉም፡፡ ምክንያቱም ከላይ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት በክንዳቸው የያዙት ህጻን 10 ኪሎ ቢመዝንና መኪናው በ50 ኪሎሜትር በሰዓት እየተጓዘ ግጭት ቢደርስ የህጻኑ ክብደት በግጭቱ ወቅት 200 ኪሎግራም ይሆናል ማለት ነው፡፡ እንዲሁም አዋቂዎች ራሳቸው ወደፊት ሊሽቀነጠሩ ስለሚችሉና የተፈጠረውን ሃይል ለመቆጣጠር ስለማይችሉ ከከጃቸው ተስፈንጥሮ ስሚጋጭ አደጋ ይደርስበታል፡፡ በዚህ ጊዜ ትልቅ ጠቀሜታ የሚሰጠው ከመኪናው አካል ጋር የተቆራኘውን የጥንቃቄ ቀበቶ በአግባቡ ስንታጠቅ ብቻ ነው፡፡ ለህጻናትም ከወንበሩ ጋር የሚታሰር ወንበር ስላለ ይህንኑ መጠቀሙ ከአደጋ ይጠብቃል፡፡ የደህንነት ቀበቶ በአግባቡ ከታጠቅን በመኪና ውስጥ ሆነን ስንጓዝ በአደጋ ጊዜ ጉዳት እንዳይደርስብን 96% (ዘጠና ስድስት በመቶ) ያህሉን ከጉዳት ሊታደገን ይችላል፡፡

### ተግባር

**ተግባር አንድ**

**እነዚህን ጥያቄዎች በማንበብ ተገቢውን መልስ በአጭሩ ስጡ**

1. መኪና ውስጥ ስተገቡ መቀመጥ የምትወዱት የትኛው ወንበር ላይ ነው?
2. የደህንነት ቀበቶ የሚኖረውን ጠቀሜታ ግለፁ?
3. ከመኪና ውስጥ ለመውረድ ስንፈልግ መውሰድ የሚገባንን ጥንቃቄ በዝርዝር ግለፁ?
4. የደህንነት ቀበቶ ማስር ጠቀሜታ ስላለው ህጋዊ አስገዳጅነት ሊደረግበት ይገባል ብላችሁ ታስባላችሁ? ምክንያቱን ዘርዘር አድርጉት፡፡
5. መኪና የሚያሽከረክሩ አንድ ሰው ፊልጉና ለምን የደህንነት ቀበቶ እንደማያስሩ ጠይቋቸው፤ መልሱን ከሰማችሁ በኂላ የደህንነት ቀበቶ ቢያስሩ ምን ጥቅም እንደሚያገኙ እንዴት ልታስረዱአቸው ትችላላችሁ?

**ተግባር ሁለት**

ድርፉጮ የዘጠኝ ዓመት ልጅ ነው፡፡ እነዚህን ተግባራት መፈፀሙ ትክክል አድርጓል ወይስ ስህተት ስርቷል ያስኘዋል፡፡ ተማሪዎች፣ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ እና በትክክል መመለስ አለመመለሳችሁን ለማረጋገጥ መምህራችሁን ጠይቋቸው፡፡

1. ከሹፌሩ ጀርባ ባለው ወንበር መቀመጥ ይወዳል፡፡
2. ከመኪና ሲወርድ በመንገዱ ቀኝ ጠርዝ በኩል ባለው በር ይወርዳል፡፡
3. ህፃናት የሚቀመጡበት የተለየ መቀመጫ ላይ መቀመጥ አለብኝ ይላል፡፡
4. ህፃናት አዋቂዎች የሚቀመጡበት መቀመጫ ላይ ቢቀመጡ የደህንነት ቀበቶው በአግባቡ ሊረዳቸው አይችልም ብሎ ስለሚያስብ ቀበቶውን አያስርም፡፡

**ተግባር ሶስት**

**ተገቢውን መልስ ስጡ**

ትክክለኛው መቀመጫ ላይ የተቀመጡ እና የጥንቃቄ ቀበቶውን በአግባቡ ያሰሩ ህፃናት አደጋ ቢደርስ የትኛው አካላቸው ሊጐዳ ይችላል?

- ጭንቅላታቸው
- አንገታቸው
- ጉሮሯቸው
- ሆዳቸው
- ክንዳቸው

መልስ፡- ቀበቶው በትክክል ከታሰረ የትኛውም የአካላቸው ክፍል ተለይቶ ሊጐዳ አይችልም፡፡

## 9. የእሽቅድምድም ጨወታ

ጨወታዎች ሁሉ የራሳቸው ህግ አላቸው፡፡ የእግር ኳስ በምትጫወቱበት ጊዜ ኳሷን በእጅ መንካት ክልክል ነው፡፡ ኳስ በጐሉ ውስጥ ካልገባች ነጥብ እንደማይቆጠር ህጉ ይደነግጋል፡፡ ከላይ የእግር ኳስ ጫወታ ህግ ምን እንደሚመስል በተወሰነ መልኩ አይተናል፡፡ አሁን የምናደርገው የአሽቅድምድም ጫወታም ህግ አለው፡፡

የዚህ ጫወታ ዓላማ፤ በመንገድ ላይ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎች መፈጸም ያለባቸውን የትራፊክ መብራት ህጐች በተግባር በጫወታ መልክ እንዲያውቁ ለማድረግ የታቀደ ነው፡፡

የተሽከርካሪ እንስቃሴን ለመቆጣጠር በአንዳንድ የአገራችን ከተሞች ውስጥ የተተከሉ የትሪፊክ መብራቶች አሉ፡፡ እነዚህ መብራቶች ሶስት ዓይነት ቀለማት ሲኖራቸው በተለያዩ መስቀለኛ መንገዶች ላይ ተተክለው ተራ በተራ በመብራት ተሽከርካሪዎች አደጋ በማያስከትል ሁኔታ እንዲተላለፉ ያደርጋሉ፡፡

አረንጓዴው መብራት መኪናዎች እንዲያልፉ ማድረጊያ ነው፡፡ ቢጫው መብራት ከአረንጋዴው ቀጥሎ የሚበራው ቀዩ ሊበራ መሆኑን በማስገንዘብ ወደማቋረጫው አልፈው የገቡት ፈጥነው እንዲያልፉና ያልገቡት ደግሞ እንዲቆሙ የሚያስጠነቅቅ መብራት ነው፡፡ ምክንያቱም ከፊትለፊቱ ቀይ መብራት ሲበራ ማንኛውም ተሽከርካሪ መቆም ግዴታው በመሆኑ ነው፡፡

ቀዩ በርቶ ተሽከርካሪዎች በዚያ የተነሳ ከቆሙ፣ ቢጫው ሲበራ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ የሚፈቅደው አረንጋዴው መብራት ቀጥሎ እንደሚበራ ስለሚታወቅ አሽከርካሪዎች ለእንቅስቃሴ እንዲዘጋጅ መጠቆሚያ መሆኑን ካለፈው ክፈለ ትምህርት ተገንዘባችኋል፡፡

**ክንውን**
ሶስቱን ቀለማት በተለያየ ወረቀት ላይ በክቡ በመቀባት እንደ ትራፊክ መብራት አድርጎ ማዘጋጀት፡፡ እነዚህን ሶስት ቀለማት የሚያሳዩ ወረቀቶችን በእንጨት ላይ በመምታት ምልክቶቹን ተራ በተራ የሚያሳዩ ሶስት ልጆች ከውስጣችሁ ትመርጣላችሁ፡፡

ሳይጠጋጉና ሳይጋፉ ስድስት ልጆች ወደፊት በሶምሶማ ሩጫ እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ፡፡ መብራቱ አካባቢ ከመድረሳቸው በፊት አረንጋዴ ቀለም የተቀባበትን ወረቀት የያዘው ልጅ ምልክቱን ዝቅ ያድርግና ብጫ ቀለም የተቀባውን ወረቀት የያዘው ልጅ ምልክቱን አሳይቶ፣ ከዚያ ብዙም ሳይቆይ ዝቅ ሲያደርግ፣ ቀዩን ወረቀት የያዘው ልጅ ከፍ አድርጐ ምልክቱን ያሳያል፡፡ በዚህ ጊዜ ልጆቹ መቆም ይገባቸዋል፤ ነገር ግን ፍጥነት ስላላቸው ቀዩን ምልክት ሳያስተውሉ የሚያልፉ ልጆች ካሉ ህጉን የተላለፉ በመሆኑ ከጫወታው ውጭ ይሆናሉ፡፡

ልጆች፣ ጫወታው አላስደሰታችሁም? አዎን ያስደስታል፡፡ እየተደሰታችሁ የትራፊክ መብራት ጠቀሜታን ትረዱበታላችሁና ይህን ጫወታ በመደጋገም ተጫወቱ እንደ ተሽከርካሪ የሚንቀሳቀሱ ልጆችን ቁጥር መጨመር ይቻላል፡፡

**ተግባር አንድ**
**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ**

1. የትራፊክ መብራት ጠቀሜታው ምንድነው? ለመምህራችሁ እና ለመላጆቻችሁ ጠቀሜታውን በመንገር ምን ያህል እንደተገነዘባችሁ አሳውቋቸው፡፡
2. በእሽቅድድም ጫወታው ጊዜ የተገፋፉ ልጆች አይታችኋል? የተገፋፉት መኪናዎች ቢሆኑ ኑሮ ምን ዓይነት አደጋ ሊያስከትሉ ይችሉ ነበር?
3. የተለያዩ ጫወታዎችን ስንጫወት ህግ እንዲኖረው የሚያስፈልገው ለምንድነው?
4. የትራፊክ ማስተላለፊያ መብራቶች በሁሉም የመኪና መንገድ ላይ የሌሉት ለምን ይመስላችኋል?
5. የቢጫው የትራፊክ መብራት ጠቀሜታ ምን እንደሆነና መቼ፣ መቼ እንደሚበራ ለጓደኞቻችሁ በመግለጽ ተወያዩበት፡፡

ልጆች፣ ይህ ስለትራፊክ ማስተላለፊያ መብራት ጠቀሜታ የቀረበ መዝሙር ነው፡፡ ለዚህ መዝሙር የሚሆን ዜማ የሙዚቃ መምህራችሁ ወይም ከመምህራን ውስጥ አንዱ እንዲያወጡላችሁ በመጠየቅ በሚሰጧችሁ ዜማ መሰረት ዘምሩ፡፡

**መብራቱ ሲጠቅመኝ**

ቀዩ መብራት መኪና አቁም ነው
ብጫ ሲሆን ማስጠንቀቂያ ነው
አረንጓዴው መፍቀጂያ ነው
መንገድ ሳቋርጥ አዘውትሬ አያቸዋለሁ
መኪኖቹ በቀይ ሲቆሙ አቋርጣለሁ
አረንጓዴ ሲሆን እቆማለሁ
የእግረኛ ማቋረጫ እጠቀማለሁ፡፡
እኔ ብልህ ወጣት ነኝ
ወላጆቼን የማላሳዝን
ራሴን ለአደጋ የማላጋልጥ
እናንተም ተጠንቀቁ፣
በመኪና አደጋ እንዳታልቁ፡፡

- ከዚህ መዝሙር ምን ትምህርት አገኛችሁ? በክፍል ውስጥ ተወያዩበት፡፡

## 10. የጠንቃቃ ልጅ ተግባር

በመንደሩ ነዋሪዎች የተመሰገነው ጠንቃቃው ልጅ ድርፉጮ በአካባቢው የሚሰጠውን ትምህርት በጥሩ ውጤት አጠናቀቀ፡፡ በአካባቢው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ባለመኖሩ የድርፉጮ ወላጆች ልጃቸውን ራቅ ወዳለ ከተማ በመውሰድ ት/ቤት አስገቡት፡፡

ይህ ወጣት ከቤተሰቦቹ ቢርቅም ከጓደኞቹ ጋር በመኖር ትምህርቱን በትጋት ቀጠለ፡፡ ከተማዋ ውስጥ ጭነት ለመጫን የሚመጡ በርካታ የጭነት መኪናዎች፣ ጋሪዎችና ብስክሌቶች በመኖራቸው ጥንቃቄ በማያደርጉ ልጆች ላይ አደጋ ያደርሱ ነበር፡፡

የእግረኛና የተሽከረካሪ መንገድ የተለየ ባለመሆኑ ጋሪ የሚጐትቱ ፈረሶች በመደንበር ተሳፋሪዎች እና መንገደኞች ላይ አደጋ እንደሚያደርሱ ያየው ድርፉጮ ጓደኞቹን፣ “ጥንቃቄ ማድረግ ካልቻልን አደጋ ሊደርስብን ይችላል፡፡” እያለ ብዙ ጊዜ ይመክር ነበር፡፡

በዚያች ከተማ ብዙ የህዝብ ማመላለሻ መኪናዎች ባለመኖራቸው አብዛኛው ሰው የሚጓዘው የጭነት መኪናዎችን በመጠቀም ነው፡፡ ሆኖም “በጭነት መኪና ላይ ተሳፍሮ መሄድ አደጋ ሊያስከትል ይችላል” እያሉ መምህሩ የሚናገሩትን እያስታወሰ እና የሚያየው የአደጋ ሁኔታ ድርፉጮን ስለሚያሳስበው ወደ ዘመዶቹ ሲሄድ የሚጠቀመው የህዝብ ማመላለሻ መኪናዎችን ነበር፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ተማሪዎች ለጉዞ ስለሚቸኩሉና የጭነት መኪና የትራንስፖርት ክፍያ ከህዝብ ማመላለሻ መኪና የትራንስፖርት ክፍያ ያነሰ በመሆኑ ገንዘብ ለመቆጠብ ሲሉ የመምህራቸውንም ሆነ የሱን ምክር ባለመስማት ከጭነት ላይ በመቀመጥ ወደ መንደራቸው ይሄዱ ነበር፡፡

ጊዜው ክረምት ላይ ነበር፡፡ ት/ቤት በመዘጋቱ ድርፉጮና ጓደኞቹ ወደ ወላጆቻቸው ዘንድ ለመሄድ ተዘጋጁ፡፡ ቀኑ ዝናባማ በመሆኑ ወደዚያ የሚሄድ የህዝብ ማመላለሻ መኪና በመጥፋቱ የጭነት መኪና ላይ ተሳፍረን እንሂድ የሚል ሃሳብ አንዱ ጓደኛቸው አቀረበ፡፡

ድርፉጮ ግን ጭነት ላይ ተቀምጦ መሄድ አደጋ ስለሚያስከትል መንገዱ ደረቅ ሲል የህዝብ ማመላለሻ መኪና ፈልገው ቢሄዱ እንደሚሻለ ሀሳብ አቀረበ፡፡

ነገር ግን ወላጆቻቸውን የናፈቁት አብዛኛዎቹ ልጆች የድርፉጮን ሀሳብ በመቃወም በጭነት መኪናም ቢሆን ተሳፍረው እንደሚሄዱ ነገሩት፡፡ ቢለምናቸውና ቢመክራቸውም እምቢ አሉት፡፡

ወደ እነሱ መንደር የሚሄድ የጭነት መኪና በማግኘታቸው አብዛኞዎቹ ልጆች መኪናው ላይ እየወጡ ጭነቱ ላይ ተቀመጡ፡፡ ጉዞ ተጀመረ፡፡ ድረፍጮና ጥቂት ልጆች ከጓደኞቻቸው በመለየታቸው እያዘኑ ወደ ማደሪያ ቤታቸው ገቡ፡፡

የጭነት መኪናው የአንድ ሰዓት ያህል ጉዞ ካደረገ በኋላ የጨቀየና በጐረፍ የተቦረቦረ አካባቢ ደረሰ፡፡ ሾፌሩ ነዳጅ ሰጥቶ ጭቃውን ሊያልፍ ሲሞክር የጫነው ከባድ ጭነት ወደ አንድ ጐን በማጋደሉ መኪናው ተገለበጠ፡፡ በዚህን ጊዜ ነበር፤ ከላይ የተቀመጡት ተሳፋሪዎች ሁሉ የሚይዙት ነገር ባለመኖሩ ግማሾቹ እየወደቁ አደጋ ሲደርስባቸው የተቀሩት ጭነቱ እላያቸው ላይ በመውደቁ ከፍተኛ አደጋ ደረሰባቸው፡፡

የበርካታ ተሳፋሪዎች ህይወት ወዲያውኑ ሲያልፍ፣ ጥቂቶቹ ከባድና ቀላል የአካል ጉዳት አደጋ ደረሰባቸው፡፡ አደጋ መድረሱን ደርፉጮና ሌሎች ጓደኞቹ ስሙ፡፡ ጓደኞቹ በድርፉጮ ጠንቃቃነት ከአደጋው በመተረፋቸው እያመሰገኑ በሌሎች ጓደኞቻቸው ላይ በደረሰው አደጋ በጣም አዘኑ፡፡ መምህራቸው ይነግሯቸው የነበረው ነገር ፍፁም ትክክለ እንደ ነበር በመገንዘብ ወደ ፊት ራሳቸውን ከልዩ ልዩ አደጋዎች ለመጠበቅ ለራሳቸው ቃል ገቡ፡፡

**<u>የተግባር ጥያቄ አንድ</u>**

**<u>ትክክል የሆነውን ሀሳብ እውነት፣ ትክክል ያልሆነውን ሀሳብ ሀሰት በማለት መልስ ሰጡ</u>**


1. ድርፉጮ በጭነት መኪናው ያልተሳፈረው ወላጆቹን ስለማይናፍቃቸው ነው?
2. ድርፉጮ በጭነት መኪና አንሂድ ያለው ምቾት ስለሌለው ነው?
3. በጭነት መኪና መጓዝ ገንዘብ ለመቆጠብ ስለሚረዳ መሳፈሩ ጉዳት አያመጣም?
4. ድርፉጮ የፈፀመው ተግባር ጠንቃቃ ልጅ ነው ሊያሰኘው ይችላል?
5. መኪናው የተገለበጠው የተሳፋሪው ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ነበር?

**<u>የተግባር ጥያቄ ሁለት</u>**

**<u>ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢውን መልስ ሰጡ፡፡</u>**

1. የጭነት መኪና ከህዝብ ማመላለሻ መኪና የሚለየው እንዴት ነው?
2. ድርፉጮ እና ጓደኞቹ እያዘኑ ወደ ማደሪያ ቤታቸው የሄዱበት ለምን ነበር?
3. ጓደኞቻችን ከሚያቀርቡልን ምክሮች ውስጥ መከተል የሚገባን ምን ዓይነቶቹን እንደሆነ ዘርዝራችሁ ግለፁ?
4. አደጋ እንዳይደርስብን ምን ዓይነት ጥንቃቄ መውሰድ አለብን?
5. በአካባቢያችሁ የመኪና አደጋ ደርሶ ያውቃል? ያያችሁትን ወይም የሰማችሁትን ነገር እየጠቀሳችሁ ተነጋገሩበት፡፡
6. እናንተስ ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

# መጽኃፍ፡- ክፍል ሶስት



**ስእል 26**
**በመስቀለኛ መንገድ ላይ የሚገኝ የመንገድ አደባባይ**

**መልእክት-** ***መጠንቀቅ ህይወትን ከአደጋ ያተርፋል***

## 1. እግረኞች በመንገድ አጠቃቀም ላይ ማወቅ የሚገባቸው ነገሮች

እግረኞች በመንገድ ላይ ሲጓዙ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በአገራችን በጥናት እንደተረጋገጠው በመኪና ግጭት ከሚደርሰው የሰው ሞት አደጋ ውስጥ 68% (ስድሳ ስምንት ከመቶ) ማለትም ከመቶ የሞት አደጋ ውስጥ 68 ያህሉ በእግረኛ ተጓዦች ላይ የሚደርስ አደጋ መሆኑ ታይቷል፡፡

ለዚህ አደጋ መከሰት አብዛኛው ስህተት የአሽከርካሪዎች መሆኑም ይታወቃል፡፡ ስለዚህ እገረኞች አሽከርካሪው ይጠነቀቅልኛል የሚል ግምት መያዝ አይኖርባቸውም፡፡ ዋነኛውን ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባቸው ራሳቸው እግረኞች መሆን አለባቸው፡፡

ስለዚህ አንድ ተጓዥ እግረኛ መኪና በሚንቀሳቀስባቸው መንገዶች በሚጠቀምበት ጊዜ እነዚህን የጥንቃቄ እርምጃዎች መፈፀም ይኖርበታል፡፡

1. በመኪና መንገድ ዳርና ዳር የእግረኛ መሄጃ መንገድ ካለ በእግረኛ መሄጃ መንገድ ላይ ብቻ መሄድ አለበት፣
2. የእግረኛ መንገድ ከሌለ ከፊት ለፊት የሚመጣን ተሽከርካሪ ለማየትና ለመጠንቀቅ እንዲረዳ የመኪና መንገዱን ግራ ጠርዝ ይዞ መጓዝ፣
3. በመኪና መንገድ ውስጥ አለመሄድ፣ አለመቆም፣ አለመቀመጥ ወይም አለመጫወት፣
4. በመስቀለኛ መንገድ ወይም በአደባባይ ላይ በሰያፍ አለማቋረጥ፡፡
5. የመኪና መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ የእግረኛ ማቋረጫ ነጭ ቀለም /ዜብራ/ የተቀባበት መንገድ ምልክት ባለበት ቦታ ከሌለ በአጭሩና በቀጥተኛው አቅጣጫ የተሽከርካሪዎችን ሁኔታ በጥንቃቄ በማየት በፍጥነት ማቋረጥ ይገባናል፡፡
6. መንገድ ስናቋርጥ መጀመሪያ ወደ ግራና ቀኝ ከዚያም በፍጥነት ወደግራ በድጋሚ በማየት በቅርብ ርቀት መኪና አለመኖሩን አረጋግጠን ይበልጥ ጥንቃቄ በማድረግ ማቋረጥ፡፡



**ስዕል 27**
**የቆመ መኪና ተከልሎ ለማለፍ አለመሞከር**

7. ተሽከርካሪን ተከልሎ ወይም ከፊትና ከኋላ ለሚመጣ ተሽከርካሪ በማይታይ ሁኔታ መንገድ ለማቋረጥ መሞከር እጅግ አደገኛ መሆኑን መገንዘብ ይገባናል፡፡

8. ተሽከርካሪ እየተንቀሳቀሰ ለመሳፈር ወይም ለመውረድ መሞከር ለአደጋ ያጋልጣል፡፡

በመንገድ አጠቃቀም ጊዜ ማወቅና ማድረግ የሚገባን በርካታ ነገሮች ቢኖሩም በዋናነት እነዚህን ወደ ተግባር ለመቀየር ብንሞክር የእግረኛ ግጭት አደጋን ለመቀነስ እንችላለን፡፡

## 2. አደጋን ለመቀነስ ምን ማድረግ ይኖረብናል

በአገራችን የሚታየውን የመኪና አደጋ ለመቀነስ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ የሚጠበቅበት ተግባር ነው፡፡ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ከተፈቀደው ሰው በላይ ሲያሳፍሩ በምናይበት ጊዜ ሁኔታውን ለተቆጣጣሪ አካላት በማሳወቅ የትራፊክ ህግ እንዲከበር የበኩላችንን እገዛ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ እጅግ አስገዳጅ ሁኔታ ካልገጠመን በስተቀር ለዕቃ መጫኛ አገልግሎት በሚውሉ የጭነት መኪና ላይ መሳፈር የለብንም፡፡ ሁኔታው አስገዳጅ በመሆኑ የጭነት መኪና የምንጠቀም ከሆነም ፍጥነቱን ቀንሶና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መጓዝ ይኖርብናል፡፡ መኪናዎቹ በፍጥነት ሊንቀሳቀሱ ከሆነም ተገቢውን አስተያየት በመስጠት ፍጥነቱን እንዲቀንስ ማድረግ፡፡ በአደገኛ ሁኔታ የሚያሽከረክር ከሆነ በሌሎች ላይ አደጋ እንዳያደርስ ሁኔታውን ለሚመለከተው አካል አስተያየት መስጠት፡፡

በጭነት መኪና ላይ ምንም መያዣ መጨበጫ በሌለው አደገኛ በሆነ አኳኋን ከዕቃ በላይ ተሳፍሮ መጓዝ ለአደጋ የሚያጋልጥ በመሆኑ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተሳፍሮ ራስን ለአደጋ ላለማጋለጥ መጠንቀቅ፡፡ ሌሎችንም መምከር፡፡

ሁሉንም ዓይነት ህገወጥ የመኪና እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የትራፊ ፖሊሶች እጥረት ስለሚኖር፣ እያንዳንዱ ዜጋ አደጋን ለመቀነስ የበኩሉን የዜግነት ድርሻ በመወጣት ለህጉ ተግባራዊ መሆን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## 3. ተሽከርካሪዎች እና ዓይነታቸው

ተሽከርካሪዎች ባለሞተር እና ያለሞተር የሚንቀሳቀሱ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ ይህን ክፍፍል በዚህ መልኩ ማየት እንችላለን፤

1. ባለሞተር ተሽከርካሪ፡- የመንቀሳቀሻ ሃይሉን የሚያገኘው ከሞተሩ ሆኖ ሞተሩ በነዳጅ ሃይል የሚሰራ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ በየብስ (መሬት) ላይ የሚሽከረከሩ ልዩ ልዩ ዓይነት መኪናዎች፣ በዓየር ላይ የሚበሩ አውሮፕላኖችና ሄሊኮፕተሮች፣ በውሃ ላይ እየተንሳፈፉ የሚጓዙ መርከቦችና ጀልባዎች በሞተር ኃይል የሚሰሩ በመሆናቸው ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ተብለው ሊመደቡ ይችላሉ፡፡
2. ያለሞተር የሚሽከረከሩ የሚባሉት የመንቀሳቀሻ ሃይላቸውን የማያገኙት ከተገጠመላቸው ሞተር ሳይሆን ከሰው ወይም ከእንስሳት ጉልበት ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ሊጠቀሱ የሚችሉት ብስክሌቶች፣ በፈረስ፣ በአህያ ወይም በበቅሎ የሚጐተቱ ጋሪዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 4. የመንገድ ላይ ተጠቃሚዎች

መንገድ የሚለው ቃል የሚገልፀው በተለያየ የጥራትና የስፋት ደረጃ እንዲሁም የቁሳቁስ ዓይነት የተሰራ ሆኖ እግረኞች፣ እንስሳትና ተሽከርካሪዎች እንዲመላለሱበት አገልግሎት የሚሰጥ ከአነስተኛ ጥርጊያ መንገድ እስከ አውራ ጐዳና ያለውን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ብዙ ዓይነት መንገዶች ያሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የእግረኛ መንገድ እና የመኪና መንገድ በሚሉ ሁለት

ክፍሎች መድበን ማየት እንችላለን፡፡ ትመህርቱ ትኩረት ያደርገው የመንገድ ላይ አደጋ እንዳይደርስብን ለማስተማር በመሆኑ በዚህ ርዕስ ስር የምንማረው ስለመኪና መንገድ ተጠቃሚዎች ይሆናል፡፡

በመኪና መንገድ የሚጠቀሙ ወገኖች በአራት ተከፍለው ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ እነዚህም፡-

1. አሽከርካሪዎች፡- ማለትም በሞተር ሀይል የሚሰሩ የተለያዩ ዓይነት ተሽከርካሪ ነገሮችን የሚያሽከረክሩ
2. ብስክሌተኞችና ጋሪ ነጂዎች፡- ያለሞተር ሀይል በሰው ወይም በእንስሳት ጉልበት በመታገዝ የሚሽከረከሩ ነገሮችን የሚጠቀሙ፣
3. እግረኞች፡- መኪና መንገዱን በመጠቀም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ፣
4. እንስሳት፡- ከቤት ወደ ግጦሽ ወይም ከግጦሽ መልስ ወደቤት ወይም ወደ ገበያ ለሽያጭም ሲነዱ ሆነ ለማጓጓዣነት ሲያገለግሉ የመኪና መንገዱን ሊጠቀሙ ይችላሉ

እነዚህ ከላይ ያየናቸው ነገሮች ለመኪና ተብለው በተሰሩ መንገዶች ላይ ነው የሚጠቀሙት፡፡

<u>የተግባር ጥያቄዎች አንድ</u>
<u>ትክክለኛውን ሀሳብ እውነት፣ ትክክል ያልሆነውን ሀሳብ ስህተት ብላችሁ መልሱ፡፡</u>

1. በመንገድ አጠቃቀም ጊዝ አሽከርካሪዎች መሉ ጥንቃቄ ስለሚያደርጉ እግረኞች ብዙም መጨነቅ የለባቸውም፡፡
2. የጥንቀቄ እርምጃዎች ተብለው የተማርናቸው ራሳችንን ከበሽታ ለመጠበቅ የሚረዱን ጥንቃቄዎች ናቸው፡፡
3. መኪና የሚበዛበት እንደ አደባባይ ያለ አካባቢ ቢሆንም በሰያፍና በአጭሩ ማቋረጥ ከቻልን ያን ማቋረጫ መጠቀሙ ተመራጭ ነው፡፡
4. መንገድ ለማቋረጥ ስንፈልግ ግራና ቀኛችንን ዞር ዞር ብለን በማየት በቅርብ ርቀት መኪና የሌለ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡
5. አደጋን ለመቀነስ ሁሉም የዜግነት ግዴታውን ለመወጣት ከትራፊክ ስርዓት ውጭ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ለተቆጣጣሪ አካላት አስተያየት መስጠት ይችላል፡፡

<u>የተግባር ጥያቄዎች ሁለት</u>
<u>እነዚህን ጥቃቄዎች አብራሩ</u>

1. የመንገድ ተጠቃሚዎች የሚባሉትን ዘርዝሩ?
2. ባለሞተር ተሽከርካሪ የመንቀሳቀሻ ሀይሉን የሚያገኘው ከምንድን ነው?
3. የጭነት መኪናዎች ለሰው መጓጓዣነት መዋል የለባቸውም የሚባለው ለምንድን ነው?
4. የመኪና መንገድን ስንጠቀም ማወቅ የሚገባን የጥንቃቄ እርምጃዎች ምንድን ናቸው?
5. በእግረኞች ላይ ነው በተሳፋሪዎች ላይ ብዛት ያለው የመኪና አደጋ ሲደርስ የሚስተዋለው?

ልጆች፣ ወደ ቀጣዩ ትምህርት ከማለፋችሁ በፊት “ጠንቃቆች” የሚለውን መዝመር ለመዘመር እንዲረዳችሁ መምህራኖቻችሁን በመጠየቅ ችሎታው ወይም ዝንባሌው ያላቸው መምህር ለግጥሙ የሚስማማ ዜማ ያውጡላችሁ፡፡

አዎ መዝሙሩን እየዘመራችሁ በግጥሙ ውስጥ የተገለፀውን ሀሳብ ይበልጥ ለመረዳት መጣር ይኖርባችኋል፡፡

ጠንቃቆች

መንገድ መንገድ
ብዙነገር ሚያስተናግድ፡፡
መኪና አለ በመንገድ ላይ
ብስክሌትም ሲሄድ የሚታይ
ብዙ ሰዎች ይሄዳሉ
እንሰሳትም ይጓዛሉ
መኪኖችም ይበራሉ
አህዮችም ይጋፋሉ፡፡
እኛ እንሁን ጠንቃቃ
ለሀገራችን የምንበቃ፡፡
የምንረዳት ይህችን አገር
ስናድግ ነው በህይወት ስንኖር፡፡
ስሙ ልጆች ተጠንቀቁ
ህይወታችሁን ጠብቁ፡፡
አዎ እንጠብቅ ህይወትን
ጠንቃቆችም እንሁን፡፡
አዎ እንጠብቅ ህይወትን
ጠንቃቆችም እንሁን፡፡

## 5. የመንገድ ላይ ትራፊክ ማለት ምን ማለት ነው?

ለመኪና በተሰራ መንገድ ላይም ሆነ ለየትኛውም አገልግሎት በተሰራ መንገድ ላይ የሚጓዙ ሰዎች የመንገድ ላይ ትራፊክ የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ ትራፊክ የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ያለው ፍቺ እንቅስቃሴ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ማንኛውም እንቅስቃሴ የሚያደርግ ነገር ሁሉ ትራፊክ ተብሎ ይታወቃል፡፡

የመንገድ ላይ የትራፊክ እንቅስቃሴ ስርዓት እንዲይዝ፣ አደጋዎች በእንቅስቃሴው ምክንያት እንዳይፈጠሩ የሚያደርገው አካል የትራፊክ ፖሊስ ተብሎ ይታወቃል፡፡

ልጆች፡- ትራፊክ ማለት እንቅስቃሴ ማለት በመሆኑ እንቅስቃሴውን የሚገልፀው የእንግሊዝኛ ቃል፣ ትራፊክ የሚለውን እንቅስቃሴውን ለሚቆጣጠረው አካል መጠሪያ ከሆነው የትራፊክ ፖሊስ የተለየ መሆኑን ማወቅ አለባችሁ፡፡

በአሁን ጊዜ በከተሞች አካባቢ ከትራፊክ ፖሊሶች በተጨማሪ የት/ቤት መግቢያና መውጫ ሰዓት የትራፊኩ ሁኔታ በአግባቡ እንዲከናወን የሚያስተባብሩ የተማሪ ትራፊክ ተቆጣጣሪዎች በየት/ቤቱ በራፍ የሚሰሩ በመሆናቸው የሚያከናውኑት ተግባር አደጋን ለመቀነስ ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግ በመሆኑ ለጥረታቸው መሳካት እገዛ ልናደርግላቸው ይገባል፡፡

በእናንተ ት/ቤት በመግቢያና በመውጭያ ሰዓት የመኪና አደጋ ተማሪዎች ላይ እንዳይደርስ የትራፊኩን እንቅስቃሴ የሚቆጣጠሩ የተማሪ ትራፊክ ተቆጣጣሪዎች አሉ? ካሉ ተግባራቸው ምን ያህል ጠቃሚ መሆኑን ተነጋገሩበት፡፡

በትምህርት ቤታችሁ የመንገድ የትራፊክ ደህንነት ክበባት ተቋቁመዋል? የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ክበባት ተቋቁመው ከሆነ በመኪና የሚደርሱ አደጋዎችን ለመቀነስ እናንተም እገዛ ማድረግ እንድትችሉ የክለቡ አባላት በመሆን ተመዝገቡ፡፡ ህጻናትም ብትሆኑ ትራፊክ አትቆጣጠሩም እንጂ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ክበብ አባላት መሆን ትችላላችሁ፡፡

በት/ቤታችሁ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ክበብ ካልተቋቋመ ከመምህራችሁ ጋር በመንጋገር የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ክበብ በማቋቋም በአካባቢያችሁ የሚገኙ የትራፊክ ፖሊሶች ተገቢውን የመንገድ አጠቃቀምና የቁጥጥር ስርዓት እንዲያስተምሯችሁ ትብብር መጠየቅ ትችላላችሁ፡፡

## 6. ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ለራሳችን ብቻ ነውን?

በየት/ቤቱ የሚገኙ ጠንቃቃ ተማሪዎች የመኪና አደጋ እንዳይደርስባቸው ጥረት የሚያደርጉት ለራሳቸው ብቻ አይደለም፡፡ ወላጆቻቸው፣ ዘመዶቻቸው ወይም የአካባቢቸው ሰዎች ከአደጋ እንዲጠበቁ በየትምህርት ቤታቸው የሚማሩትን የትራፊክ ደንቦች በማስረዳት ግንዛቤ የማስፋት ስራ ሲሰሩ ይታያሉ፡፡

በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ የከተማውና የአካባቢው ህዝብ ተገቢውን የመንገድ አጠቃቀም ስርዓት እንዲያውቅ ያደረጉት የአምቦ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መሆናቸው ይነገራል፡፡

የአምቦ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት በሚወጡበትም ሆነ ወደ ት/ቤት በሚሄዱበት ጊዜ የሚጠቀሙት የመንገዱን ግራ ጠርዝ ነው፡፡ የመንገዱን ግራ ጠርዝ በመያዝ የሚጓዙት ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ ህብረተሰቡም እንዲጠቀም በተደጋጋሚ በሰጡት ትምህርት፣ በአሁኑ ጊዜ ይህ ልምድ ሆኖ የአምቦ ህዝብ በመኪና መንገድ ላይም ሆነ በእግረኛ መንገድ በእግሩ ሲጓዝ የሚጠቀመው የመንገዱን ግራ ጠርዝ በመያዝ ነው፡፡

የመንገዱን ግራ ጠርዝ ሳይዝ የሚጓዝ ሰው ከታየ ለከተማው እንግዳ መሆኑ ከመታወቁ በተጨማሪ "እባክዎትን" ተብሎ ትክክለኛውን የእግረኞች መንቀሳቀሻ አቅጣጫ እንዲጠቀም ትብብሩ ይጠየቃል፡፡

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት አንድ ዞን በሆነችው፣ ከአዲስ አበባ ወደ ምዕራብ 125 ኪ. ሜትር ርቀት ላይ ባለችው ከተማ የተጀመረው መልካም ተግባር በአምቦ አቅራቢያ ባሉ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አማካኝነት በየአካባቢያቸው እንዲለመድ በመደረጉ በግንጪ፣ በጉደር እና በአንዳንድ የአካባቢው ከተሞች እየተለመደ መምጣቱ ይደርስ የነበረውን የመኪና አደጋ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ እገዛ እድርጓል ተብሎ ይታመናል፡፡

እናንተስ ይህን መልካም ተግባር በመፈፀም ለአካባቢያችሁ ምሳሌ በመሆን ራሳችሁን እና ህብረሰተቡን ከመኪና አደጋ ለመጠበቅ ዝግጁ ናችሁ?

አዎን ዝግጁ እንደሆናችሁ ለመምህራኖቻችሁ ግለፁላቸው፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ይህን መልካም ተግባር ለመፈፀም ቅድሚያውን በመውሰድ እና ለሌሎችም ለማስተማር ከተንቀሳቀሳችሁ እግረኞች ላይ የሚደርሰውን የመኪና አደጋ በከፍተኛ ሁኔታ ልትቀንሱ ትችላላችሁ፡፡

ስለዚህ ሃሳባችሁን እውን ለማድረግ ከታላላቆቻችሁ፣ ከመምህራን እና ከወላጆቻችሁ ጋር በመመካከር ትምህርት የምትሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ከናንተ የሚጠበቅ የዜግነት ድርሻ መሆኑን መገንዘብ ይገባችኋል፡፡

## 7. የመጓጓዣ ዓይነቶች እና ጠቀሜታቸው

የሰው ልጅ ከብዙ ዓመታት በፊት ጀምሮ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚያደርገውን ጉዞ አድካሚነት ለመቀነስና ፍጥነት ለመጨመር የተለያዩ የትራንስፖርት መገልገያዎችን ሲጠቀም ኖሯል፣ አሁንም እየተጠቀመ ይገኛል፡፡

ጥንታዊ መጓጓዣዎች ተደርገው የሚወሰዱት የጋማ ከብቶችን ማለትም ፈረስን፣ በቅሎን፣ አህያን ወዘተ፣ በመጠቀም ሰዎች ራሳቸውንም ሆነ ያመረቱትን ምርት ወደ ገበያና ወደ ተለያዩ ቦታዎች፣ ለማድረስ ሲጠቀሙ ኑረዋል። አሁንም ቢሆን በአገራችን የገጠር አካባቢዎች በርካታ ህዝብ የጋማ ከብቶችን ለመጓጓዣነት ሲጠቀም ይስተዋላል።

የጋማ ከብቶችን ለትራንስፖርት መገልገያነት መጠቀሙ ስራን የሚያቃልል፣ ድካምን የሚቀንስ መሆኑ የታመነበት ቢሆንም በነዚህ እንስሳት የሚጠቀሙ ሰዎችም ሆኑ ሌሎች እግረኞች አደጋ እንዳይደርስባቸው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ለማጓጓዣ የሚያገለግሉ እንስሳት ጠቀሜታቸው ከፍተኛ መሆኑ ቢታወቅም ተገቢ ባለሆነ ሁኔት የምንጠቀምባቸው ከሆነ አደጋ ሊያስከትሉብ ይችላሉ። እንስሳቱን ለመጓጓዣነት ስንጠቀም ተስተካክለን መቀመጥ እንደንችል ኮርቻ ልንጠቀም ይገባል። ስንጋልብ እንስሳቱን ለመቆጣጠር አፋቸው ውስጥ በመግባት የሚያገለግለው ልጓም የሚባለው፣ ከብረትና ከጠፍር የተሰራ ነገር የምንጠቀም ቢሆን የበለጠ ይመረጣል። ይህ ባልተሟላበት ሁኔታ የጋማ ከብቶችን ለመጓጓዣ እንዲረዱን ብቻ አስበን ብንጠቀምባቸው አደጋ ሊያስከትሉ እንደሚችሉ መረዳት ያስፈልጋል። ለጭነት ማጓጓዣነት ስንጠቀምባቸው ጀርባቸውን ጭነቱ እንዳይጎዳቸው አስፈላጊ መከላከያ ልናደርግላቸው ይገባል።

ስለዚህ ጠንቃቃ ወጣቶች ጥንቃቄን የሚጀምሩት በአካባቢያቸው ከሚጠቀሙት ነገር በመሆኑ እናንተም ይህንኑ በመፈፀም ጠንቃቆች መሆን ይገባችኋል።

ከእንጨት የተሰራ መሽከርከሪያ የተገጠመለት በጋማ ከብቶች በመጎተት ሰውና እቃ ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝ የምንጠቀምበት ነገር ጋሪ ይባላል። ጋሪ የሚሠራው፤ ከእንጨት፣ ከብረትና ከመኪና ጐማ ወይም የብረት ተሽከርካሪ ነው። ከነዚህ ነገሮች ገጣጥሞ በመስራት በፈረስ፣ በበቅሎ በአህያ በማስጐተት ሰዎችና እቃዎች ይጓጓዙበታል።

በአገራችን በበርካታ ትናንሽ ከተሞች ውሰጥ ጋሪዎች በተለይም የፈረስ ጋሪዎች ለሰዎች መጓጓዣነት በስፋት ሲሰጡ ይታያሉ። ከአገራችን ትላልቅ ከተሞች በአሁኑ ጊዜ ጋሪ የሌለበት አደስ አበባ ከተማ ብቻ ነው። ነገር ግን በብዙ አነስተኛ ከተሞች እንደ ዋና የትራንስፖርት መገልገያ ሆነው ሲያገለግሉ ይታያል። በገጠሩም ለጭነት ማጓጓዣነት በአህያ የሚጎተቱ ጋሪዎችን በብዛት እየተጠቀሙ ይታያል።

ልጆች፣ እናንተ በምትኖሩበት አካባቢ ጋሪዎች አሉ? በጋሪዎች ምክንያት አደጋ ሲደርስ አስተውላችኋል? እስቲ ከመምህራችሁ ወይም ከወላጆቻችሁ ጋር ተወያዩበት።

በጋሪዎች የተነሳ የሚደርሱ በርካታ አደጋዎች አሉ። ለምሳሌ ጋሪውን የሚጐትተው ፈረስ ወይም አህያ ከደነበረ በሰዎች ላይ አደጋ ሊያደርስ ይችላል።

ጋሪዎች በሰፈር የውስጥ ለውስጥ መንገዶች በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ሞተር ስለሌላቸው ድምፃቸው አይሰማም። አንዳንድ ስዎች እንሰሳት አደጋ አያደርሱም በሚል አስተሳሰብ የተነሳ ጥንቃቄ ስለማያደርጉ በጋሪ ጐታች እንስሳት ሊገጩ ይችላሉ። ጋሪ የተሰራበት እንጨት ሲወጋቸውና አደጋ ሲያደርስባቸው የሚታይበት ጊዜ ብዙ ነው።

በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታዩት የዕቃ መጫኛ ጋሪዎች በሁለት ወይም ሶስት አህያ ወይም በቅሎ የሚሳቡ በመሆናቸው በርካታ እቃዎች ሲጫኑባቸው ይታያሉ። የሚጫነው ዕቃ በክብደቱ ቀላል ከሆነ፣ ለምሳሌ የበቆሎ አገዳ የመሳሰሉት ተከምሮ ስለሚጫን ከኋላ የሚመጣን ነገር በማየት ጥንቃቄ ለማድረግ አመቺ ባለመሆኑ ወይም ከኋላ ያለ መኪና ከፊቱ የሚመጣውን ተሽከርካሪ እንዳያይ ስለሚጋርደው ጋሪውን በሚቀድምበት ጊዜ የተለያዩ የመንገድ ላይ አደጋዎች እንዲደርሱ ምክንያት ሲሆን ይታያል።

ስለዚህ የምንጠቀምባቸው ነገሮች ጥሩ ጠቀሜታ የሚሰጡ ቢሆኑም አደጋም ሊያስከትሉ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች መኖራቸውን አውቀን በጋሪ ስንሳፈርም ሆነ በጋሪ የተሳፈሩ ሰዎች በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ አደጋ እንዳይደርስብን ተገቢ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል።




ስእል 28
ከጋሪ ዓይነቶች አንዱ

በበርካታ የአገራችን ከተሞች ጋሪዎችና መኪናዎች የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣሉ። የተለያዩ ዓይነት መኪናዎች የሰውን ልጅ የትራንስፖርት ችግር ለማቃለል ጥቅም ላይ ውለዋል። ከነዚህ ውስጥ ብዙ ሰዎችን በማሳፈር ሩቅ ቦታ የሚያደርስ አውቶቡስ ተብሎ ሲታወቅ፣ ከአውቶቡስ አነስ ያሉና ከ4 ሰወች እስከ 11 ሰዎች ሊያሳፍሩ የሚችሉት ታክሲ ተብለው ይታወቃሉ። ከዚህ በተጨማሪ ሰዎች ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው መጓጓዣናት የሚጠቀሙባቸው አነስተኛ መኪናዎች የቤት መኪናዎች ተብለው ይጠራሉ።

በሞተር ሀይል ባይሰራም በሰው ጉልበት አማካኝነት የሚንቀሳቀሰውና በብዙ ከተሞች ውስጥ የሚገኘው እየሰጠ ያለው የፔዳል ነው። እነዚህ መጓጓዣዎች ከሚሰጡት ጥቅም ጎን አደጋዎችንም የሚያደርሱባቸው ሁኔታዎች አሉ።

<u>የተግባር ጥያቄዎች</u>
<u>ለነዚህ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ</u>

1. ጠንቃቆች ከሚለው መዝሙር ምን ትማራላችሁ?
2. ትራፊክ ማለት ምን ማለት ነው?
3. የተማሪ ትራፊክ ተቆጣጣሪዎችና የትራፊክ ፖሊስ አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?
4. የመኪና አደጋ እንዳይደርስብን ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ለራሳችን ብቻ ነው ትላላችሁ?
5. በተማሪዎች ንቁ ጥረት፣ የመኪና መንገድን ግራ ጠርዝ ብቻ በመያዝ፣ ሰዎች በመንገድ ላይ ሲጓዙ የሚታይባቸው አካባቢወች የት የት ናቸው?
6. ስለጋሪ አሰራር አገልግሎት የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ ግለፁ?
7. በጋሪ አማካኝነት የደረሱ አደጋዎች ካሉ ትላልቅ ሰዎችን በመጠየቅ ተወያዩበት?
8. የተማሪ ትራፊክ ተቆጣጣሪዎች ምን ጠቀሜታ ይሰጣሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?
9. በመኪና አማካኝነት የሚደርሰውን አደጋ ለመቀነስ ተማሪዎች ምን ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል?
10. ከአንቦ ተማሪዎች የምንማረው ምንድን ነው?

## 8. የመኪና አደጋ የሚደርስባቸው ዋነኛ ምክንያቶች

- በአሽከርካሪዎች ጥንቃቄ የጐደለው የአነዳድ ሁኔታ፣
- በጭነት ተሽከርካሪ ደህንነቱ ባልተጠበቀ ሁኔታ ሰውን በማጓጓዝ
- በእግረኞች ጥንቃቄ የጐደለው እንቅስቃሴ፣
- እንስሳትና ጋሪዎች በዋና መንገድ ላይ ያለጥንቃቄ መጓዝ
- የተሽከርካሪው መቆጣጠሪያ አካላት በትክክል አለመስራት፣
- የመንገዱ ሁኔታ ለተሽከርካሪውም ሆነ ለእግረኛው ምቹ አለመሆን የተነሳ የሚፈጠር እንደሆነ ይታወቃል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ አንድ ተሽከርካሪ በአደጉ ሀገሮች ብዙ ተሽከርካሪዎች የሚያደርሱትን አደጋ በሰው ላይ ያደርሳል፡፡ በአሽከርካሪዎች ስህተት በሚፈጠረው አደጋ አብዛኛው ተጎጂዎች ደግሞ እግረኞች ናቸው፡፡ ይህን አደጋ ለማስወገድ እግረኞች ምን ተግባር መፈጸም ይገባቸዋል ብላችሁ ታስባላችሁ? እግረኞች የመንገድ አጠቃቀም ስርዓትን በትክክል ማወቅ ይኖርባቸዋል፣ በመንገድ ላይ ሲጓዙ መውሰድ ያለባቸውን ጥንቃቄ ችላ ብለው የሚጓዙ ከሆነ ለመኪና አደጋ ይጋለጣሉ፡፡

ስለዚህ እግረኞች በመኪና መንገድ በሚጠቀሙበት ጊዜ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ በመውሰድ ራሳቸውን ከአደጋ ለመጠበቅ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

አሽከርካሪዎች በራሳቸውም ሆነ በሌላው መንገደኛ ላይ አደጋ እንዳይደርስ ጠንቃቆች እና አሳቢዎች መሆን አለባቸው፡፡ የመንገድ አጠቃቀም ስርዓትን ማክበር ይገባቸዋል፡፡ የራሳቸውን መቸኮል ብቻ ሳይመለከቱ ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት በሚገባቸው ጊዜ ቅድሚያ መስጠት፣ ለያዙት ንብረትም ሆነ የሰው ህይወት ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ሀላፊነት አለባቸው፡፡

አሽከርካሪዎች በጫት፣ በመጠጥ ወይም ይህን በመሳሰሉ አደንዛዥ እጾች አማካኝነት የተለወጠ የማመዛዘን ስሜት በመያዝ መኪና መንዳት የለባቸውም፡፡ በትክክል በሚያመዛዝን አዕምሮ፣ በራሳቸውም ላይ ሆነ በሌሎች ላይ አደጋ ሳያደርሱ እንዲንቀሳቀሱ ራሳቸውን ከተለያዩ ሱሶች ማራቅ አለባቸው፡፡ መኪና በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ሙሉ ሀሳባቸውን በመንገዱ እና በሚያሽከረክሩት መኪና ላይ በማድረግ መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡ ይህን ማድረግ ካልቻሉ የመኪና አደጋ ሊያጋጥማቸው እንደሚችል እርግጠኛ መሆን አለባቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመንገድ አጠቃቀም ስርዓትን ማወቅና መተግበር፣ የፍጥነት ወሰንን ማክበር፣ በከተሞችና ሰው በሚበዛባቸው አካባቢዎች ፍጥነታቸውን ቀንሰው በጥንቃቄ ማሽከርከር፣ በጭነት ተሽከርካሪ ደህንነቱ ባልተጠበቀ ሁኔታ ሰውን አለማጓጓዝ የመሳሰሉትን ጥንቃቄዎች መፈጸም ይኖርባቸዋል፡፡

ተሽከርካሪዎች አደጋ እንዳያደርሱ ወይም የአደጋ መንስኤ እንዳይሆኑ የተሽከርካሪ መቆጣጠሪያ አካላቶቻቸው የተሟሉ መሆን ይገባዋል፡፡ አንድ መኪና ለማቆም የሚያስችለው ፍሬን፣ የሚዞርበትን አቅጣጫ አጠገቡ ላሉት ተሽከርካሪዎች ለመግለጽ የሚያስችለው በግራ እና በቀኝ የተገጠመ የፍሬቻ መብራት፣ ከኂላና ከጐን በኩል የሚመጣ መኪና መመልከቻ የጐን መስታወት፣ ወደተፈለገው አቅጣጫ ለማዞር የሚያስችለው መሪ፣ ጎማዎቹ ከነመጠባበቂያው፣ ማስጠንቀቂያ ጥሩንባ፣ ወዘተ የመሳሰሉት የተሽከርካሪ መቆጣጠሪያ አካላት በጥሩ ሁኔታ መሆናቸውንና በትክክል መስራታቸውን በየጊዜው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ለመኪናም ሆነ ለእግረኛ መጓጓዣነት መንገድ አስፈላጊ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የእግረኛ መንገድ ከመኪና መንገድ ተለይቶ ጐን ለጐን የተሰራ መሆን ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም እግረኛና መኪና በአንድ መንገድ የሚጠቀሙ ከሆነ ለአደጋ መከሰት ምክንያት ይሆናሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የእግረኛው መንገድ ሁኔታ ምቹ ካልሆነ እግረኞቹ ወደ መኪና መንገዱ እንዲገቡ ስለሚገደዱ ለአደጋ መፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

በአገራችን የተሰሩት አብዛኛዎቹ መንገዶች የእግረኛና የተሽከርካሪ ተብለው የተለዩ አይደሉም፡፡ ይህ መሻሻልና መለወጥ የሚገባው እንደሆነ ይታመናል፡፡ በከተማም ሆነ በገጠር አብዛኛው ተጓዥ እግረኛ እንደመሆኑ መንገዶች ሲሰሩ የእግረኛውንም ፍላጎት ያሟሉ እንዲሆኑ መደረግ አለበት፡፡ ለመሻሻሉ መነሻ የሚሆነው ወጣት ዜጐች ተምረውና ጠንክረው የአገራችንን ኢኮኖሚ ለማሳደግ በሚያደርጉት ጥረት ነው፡፡

ስለዚህ ተማሪዎች የመኪና አደጋ በተለያዩ ምክንያት ሊደርስ እንደሚችል በማወቅ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድርግ የሞትና የአካል ጉዳት አደጋ በናንተም ላይ ሆነ በሌሎች ሰዎች ላይ እንዳይደርስ በማስተማርና እናንተም በመጠንቀቅ ተገቢውን የደህንነት እርምጃ መውሰድ ይገባችኋል፡፡

**<u>የተግባር ጥያቄዎች</u>**

**<u>ለነዚህ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ</u>**

1. የመኪና አደጋ እንዳይደርስ ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች ምንድን ናቸው?
2. በአሽከርካሪዎች ጥንቃቄ ጉድለት አደጋ እንዴት ሊደርስ ይችላል?
3. የተሽከርካሪ መቆጣጠሪያ አካላት አለመሟላት እንዴት አደጋ ሊያስከትል ይችላል?
4. የፍሬቻ መብራት ጠቀሜታ ምንድን ነው?
5. የእግረኛና የተሽከርካሪ መንገዶች የተለያዩ መሆኑ ምን ጠቀሜታ አለው?

## <u>9. ትራንስፖርት ለንግድ መስፋፋት የሚኖረው እገዛ</u>

የትራንስፖርት አውታሮች መኖርና ንግድ ሁለት ተያያዥነት ያላቸው ነገሮች ናቸው በገጠሪቱ የአገራችን ክፍልም ሆነ በከተሞች ውስጥ ስዎች ያመረቷቸውን ወይም የሰሯቸውን ነገሮች ለገበያ የሚያቀርቡት የትራንስፖርት አውታሮችን በመጠቀም ነው፡፡

በአገራችን የተለያዩ የትራንስፖርት አውታሮች ያሉ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ ለበረካታ ህዝብ ለመጓጓዣም ሆነ ለዕቃ መጫኛ አገልግሎት የሚሰጡት የጋማ ከብቶች ናቸው፡፡ ገበሬዎች የጋማ ከበቶችን በመጠቀም ያመረቷቸውን ምርቶች ገበያ አውጥተው በመሸጥ ባገኙት ገንዘብ በፍብሪካ የተመረቱ ምርቶችን በመግዛት የሚጠቀሙበት የትራንስፖርት አውታር በመኖሩ ነው፡፡ የትራንስፖርት አውታሮች ባይኖሩ ኑሮ አገሮች ያመረቷቸውን ምርቶች ሊሻሻጡ የሚችሉበት አመቺ ሁኔታ ባልኖረ ነበር፡፡

ከትራንስፖርት አገልግሎቶች ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያለውና በርካታ አገልግሎት ከፍጥነት ጋር የሚሰጠው መኪና ነው፡፡ ለመኪናዎች መመላለሻ የሚሆኑ የተለያዩ መጠንና ጥራት ያላቸው መንገዶች ባሉባቸው የአገራችን ክልሎች የመኪና ትራንስፖርት ለንግድ መስፋፋት ከፍተኛ ጠቀሜታ ሲሰጥ ይታያል፡፡

ባቡርም የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ የተዘረጋው የባቡር ሀዲድ አገራችን ከውጭ አገሮች ጋር የምታደርገውን የንግድ ልውውጥ እንዲጠናከር አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል፡፡



ስእል 29
የምድር ባቡር

በአገራችን የተመረቱ ምርቶችን ወደ ውጭ አገር በመላክ፣ ከውጭ ተገዝተው የሚመጡ ምርቶችን ወደ አገር ውስጥ በማስገባት ንግድን ማስፋፋት የሚቻለው የትራንስፖርት መገልገያ አውታሮችን በመጠቀም ነው፡፡

<u>ወጣት ተማሪዎች (ህፃናት) ምን የተሳሳቱ ተግባራትን ይፈጽማሉ</u>

ህፃናት ስለ አካባቢያቸው ያላቸው ግንዛቤ አናሳ በመሆኑ ለአደጋ ሊያጋልጧቸው የሚችሉ ተግባራትን ሲፈጽሙ ይታያሉ፡፡ በተሳሳተ መልኩ ከሚፈጽሟቸው ተግባራት ውስጥ ጐልተው የሚታዩትን እንጥቀስ፡-

ከሁሉም በላይ ህፃናት ፍላጐታቸውን ማሳካት ብቻ ነው የሚፈልጉት (መጫወት፣ ወዲያ ወዲህ መሮጥ፣ ወላጆቻቸውን ከሩቅ ሲያዩ ሮጦ ለመቀበል፣ መቸኮል፣ ወዘተ የመሳሰሉ ድርጊቶችን ይፈጽማሉ፡፡ እነዚህን ድርጊቶች ሲፈጽሙ ሊገጥማቸው የሚችለውን አደጋ ፈጽሞ አያገናዝቡም፡፡

ህፃናት ዕድሜያቸው በግምት 7 ዓመት እስኪሆናቸው ድረስ ስለአደጋ ያላቸው ግንዛቤ ጠንካራ አይደለም፡፡ ህይወታቸው በአደጋ ውስጥ መሆኑን አስበው አይጨነቁም፡፡ በጫወታ ጊዜ ቦታ ሳይመርጡ ይጫወታሉ፡፡ የማመዛዘን ችሎታቸው ስላልዳበረ አነስተኛ ነው፡፡ በአንድ ጊዜ ከአንድ ለበለጡ ነገሮች ትኩረት አይኖራቸውም፡፡ ይህ ሁኔታ ለአደጋ እንዲጋለጡ ሲያደርጋቸው ይታያል፡፡

ህፃናት ቤታቸው አካባቢ ሲደርሱ የሚያደርጉትን ጥንቃቄ ትተው መዝናናት ይጀምራሉ፡፡ ት/ቤት የመሄጃ ስዓት ከረፈደባቸው ስለመርፈዱ ከማሰብ ውጭ አደጋ እንዳይደርስባቸው አይጠነቀቁም፡፡ ወደ ጓደኞቻቸው ለመሄድ ሲያስቡም ከጓደኞቻቸው ጋር ስለሚያደርጉት የጫወታ ዓይነት ያስባሉ እንጂ ሊደርስባቸው ስለሚችለው የመንገድ ላይ አደጋ በማስብ ጥንቃቄ አያደርጉም፡፡

አንዳንድ ህፃናት የመኪና መንገዶችን ጥሩ የመጫወቻ ቦታ አድርገው የሚመለከቱበት ሁኔታ አለ። ምክንያቱም መንገድ ላይ የስልክና የኤሌክትሪክ ምሶሶዎች ስለሚኖሩ እዚያ ላይ ኳስ አስሮ ለመጫወት፣ ለመንጠላጠል፣ ወዘተ ስለሚያመች መንገድ ላይ መጫወት ይመርጣሉ።

ከመንገዱ ዳር ኳስ ሲጫወቱ ኳሷ ወደ መኪና መንገዱ ብትገባ አደጋ ይደርስብኛል ብለው ሳያስቡ ኳሷን ለመመለስ ሲሮጡ ይታያሉ። ጓደኞቸው ወይም ሌላ ሰው ከመንገዱ ሌላ አቅጣጫ ቢጠራቸው ያለማስተዋልና ያለጥንቃቄ መንገዱን በማቋረጥ ወደዚያ መሄዱን ብቻ ያስባሉ። ህፃናት ጨወታቸውን ከፍ አድርገው ስለሚመለከቱ ለሌሎች ጉዳዮች የሚሰጡት ግምት አነስተኛ ነው።

አንድ ነገር እንዲፈጽሙ በተነገራቸው ቅጽበት ስለዚያ ጉዳይ በመደጋገም ያስባሉ፣ ይጠነቀቃሉ። ነገር ግን አየቆዩ ሲሄዱ ስለዚያ ነገር እየረሱ ስለሚሄዱ የሚሰጡት ትኩረትም አነስተኛ ይሆናል።

መንገድ ሲያቋርጡ ወይም የመኪና መንገድ ሲጠቀሙ አስደንጋጭ ሁኔታ ቢገጥማቸው ሮጠው ለማምለጥ ወይም ደንግጠው ለመቆም ይሞክራሉ እንጂ ተረጋግተው ሁኔታውን በማየት ተገቢውን እርምጃ ሲወስዱ አይታዩም።

ከላይ ያየናቸውን ነገሮች ተማሪዎች በተሳሳተ መልኩ ተግባር ላይ ሲያውሉ ይታያሉ። እነዚህ ድርጊቶች በሙሉ ለአደጋ መፈጠር መነሻ ሊሆኑ ስለሚችሉ መምህራንና ወላጆች ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ህጻናት ራሳቸውን ከአደጋ መጠበቅ እንዲችሉ ማሳየትና ማስተማር ይገባቸዋል።

## 10. በትምህርት ቤቶች አካባቢ ሊወሰድ የሚገባ ጥንቃቄ

አብዛኛዎቹ ትምህርት ቤቶች፣ በተለይም በከተሞች የሚገኙ ትምህርት ቤቶች፣ በመኪና መንገድ ዳር የተሰሩ በመሆናቸው፣ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ሲወጡ ወይም ወደ ትምህርት ቤት ሲገቡ፣ አደጋ ሲደርስባቸው ይስተዋላል።

ይህ ችግር ተገቢውን ትኩረት አግኝቶ የትምህርት ቤቶች የተማሪ መግቢያና መውጫ በሮች ከመኪና መንገድ ተቃራኒ አቅጣጫ ሊዞሩ የሚችሉበት ሁኔታ ሊታሰብ የሚገባው ሲሆን ወደፊትም በሁሉም ቦታ የሚሰሩ ትምህርት ቤቶች በሮቻቸው ይህን ችግር በሚያስቀር መልኩ ቢሰሩ የተሻለ እንደሚሆን ይመከራል።

ከላይ የቀረበውን ሀሳብ በአንድ እውነተኛ ገጠመኝ ማጠናከር ይቻላል። ቦታው በአ ዲስ አበባ ከተማ፣ በመድሐኒዓለም 1ኛ ደረጀ ት/ቤት በራፍ ላይ፣ በ1985 ዓ.ም፣ ከቀኑ 11 ሰዓት፤ ተማሪዎች የዕለቱን ትምህርት ጨርሰው ተለቀዋል። በት/ቤቱ በር የሚያልፍ የመኪና መንገድ በመኖሩ በርካታ ተማሪዎች መንገዱ ላይ በመቆም ከጓደኞቻቸው ጋር እየተሰነባበቱ ሌሎችም አብሮ ሂያጅ ጓደኞቻቸውን በመጠበቅ ጫወታ ላይ ነበሩ።

አንድ ታክሲ ከላይ ወደ ተማሪዎቹ አቅጣጫ እየተምዘገዘገ ይመጣል። ተማሪዎቹ አስተውለው ባያዩትም ታክሲው በዚያ ፍጥነት የሚበረው ፍሬኑ ስለተበላሸበት ነበር። ያ ታክሲ እየበረረ እንደመጣ ከትምህርት ቤቱ ተለቀው መንገድ ሞልተው የቆሙ ተማሪዎች ጋር ደረሰ። ጥቂቶቹ ሮጠው አመለጡ። ሌሎች በአደጋው ተጐዱ። በዚያን ቀን ዘጠኝ ህፃናት በአደጋው ሲሞቱ 34 ተማሪዎች ከባድና ቀላል አደጋ ደረሰባቸው። አካባቢው በሀዘንና በእሪታ ተሞላ።

ልጆች፣ ይህ አሳዛኝ ክስተት የደረሰው የት/ቤቱ በሮች ከመንገዱ ትይዩ በመስራታቸው ብቻም አይደለም። ተማሪዎች መጫወትና ማውራት ያለባቸውን ቦታ ለይተው ስላልተጠቀሙና

አሽከርካሪውም ቁልቁለት ሲወርድ ጥንቃቄ ባለማድረጉና ተሽከርካሪውም ፍሬኑ የማይሰራ በመሆኑ ጭምር ነው፡፡ ተማሪዎች አሽከርካሪው ይጠነቀቅልኛል ሳይሉ ራሳቸው ይበልጥ በመጠንቀቅ እንደወጡ የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዘው ወደየቤታቸው ቢሄዱ ይህን መሰል አሰቃቂ አደጋ ሊደርሰ አይችልም ነበር፡፡

በውጭ አገር በተሰራ ጥናት መሰረት ከመቶ ዘጠኝ ያህል አደጋ የሚደርስው በት/ቤት በሮች አካባቢ ሲሆን፣ ከመቶ ስልሳ አምስት አደጋዎች የሚደርሱት ተማሪዎች ቤታቸው አካበቢ ሲደርሱ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰፈራቸው በመድረሳቸው ምንም ዓይነት ችግር ሊገጥመን አይችልም ብለው ስለሚያሰቡ ነው፡፡

ስለዚህ ህፃናት ሰፈሬ ደርሻለሁ፣ ትምህርት ቤቴ በርላይ ነኝ ብለው ማድረግ የሚገባቸውን ጥንቃቄ መቀነስ የለባቸውም፡፡ ወላጆችና መምህራን ይህን ደጋግመው በማሳሰብ፣ ተማሪዎችም የተማሩትን መሰረት በማድርግ ህይወታቸውን ከአደጋ ለመጠበቅ ንቁና ጠንቃቃ መሆን ይገባቸዋል፡፡

<u>ተግባር አንድ</u>

<u>ትክክል ለሆነው ሀሳብ እውነት፣ ትክክል ላልሆነው ሀሳብ ስህተት በማለት መልስ ስጡ፡፡</u>

1. በት/ቤቶች አካባቢ አደጋ ሊደርስ ስለማይችል ጥንቃቄ ማድረግ አያስፈልግም፡፡
2. ለንግድ መስፋፋት የትራንስፖርት መኖር አጋዥ ነው፡፡
3. ህፃናት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡት ለሚያደርጉት ጨወታ ሳይሆን አደጋ እንዳይገጥማቸው ነው፡፡
4. ህፃናት የተነገራቸውን ምክር ወዲያውኑ ቢያስታውሱትም እየቆዩ ሲሄድ ግን ሊረሱት ይችላሉ፡፡
5. ህፃናት ስለአደጋ መፈጠሪያ ምክንያቶች ያላቸው ግንዛቤ ከአዋቂዎች ያነሰ ነው፡፡

<u>ተግባር ሁለት</u>

<u>አጭርና ግልጽ መልስ ስጡ፡፡</u>

1. በአገራችን ያለው የባቡር መስመር ከየት እስከ የት የተዘረጋ ነው?
2. ህፃናት ከሁሉም ነገር በላይ ትኩረት የሚሰጡት ለምን እንደሆነ አብራሩ?
3. ተማሪዎች ቤታቸው አካባቢ የሚደርስባቸው አደጋ ለምን ከፍ ያለ ይሆናል?
4. የትምህርት ቤት በሮች በምን አቅጣጫ ቢሰሩ ተመራጭ ነው? ለምን? አብራሩ
5. ካነበባችሁት ሌላ፣ በት/ቤት በር አካባቢ የደረሰ የመኪና አደጋ መኖሩን ከመምህራችሁ በመጠየቅ ስለሁኔታው ተወያዩበት፡፡

<u>ተግባር ሦስት</u>

የክፍል ውስጥ ተማሪዎች በትናንሽ ቡድን መከፋፈል፡፡ በምን ጊዜ ወይም በምን ሁኔታ የመኪና መንገድ ሮጠው እንደሚያቋርጡ እንደሚገፋፉ በቡድን እንዲወያዩ ማድርግ፤ እያንዳንዱ ቡድን የደረሰበትን ሀሳብ እየጠየቁ በመፃፍ፤ ተማሪዎች ይህን መሰሉ ድርጊት ምን ዓይነት አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ተወያዩበት፡፡

<u>ተግባር አራት</u>

የረፈደባቸው ተማሪዎች እንዴት ወደ ት/ቤት እየተቻኮሉ እንደሚሄዱ አንድ ተማሪ እዚያው በቆመበት ቦታ ድምፅና እንቅስቃሴ ሳያደርግ በአካልና በፊቱ ሁኔታ እንዲገልጽ ማድረግ፣ ተማሪዎች ሲረፍድባቸው ምን እንደሚያደርጉ ማወያየት፣ ከዚያ እደተቻኮሉ ወደ ት/ቤት ከመሄድ ይልቅ ቀደም ብለው በመነሳት ወደ ት/ቤት ለመሄድ መሞከር የተሻለ እንደሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው መርዳት፡፡

ተግባር አምስት

አንድ ተማሪን ምሳሌ በማድርግ ፊቱን ለመታጠብ፣ ቁርሱን ለመብላት፣ ከቤት ወደ ት/ቤት ለመድረስ ስንት ሰዓት እንደሚፈጅበት በዝርዝር እየመዘገቡ በመወያየት፣ ሌሎች ተማሪዎችም ከወላጆቻቸው ጋር እየተነጋገሩ እንዲመዘግቡ በማድረግ ሳይቸኩሉ በስንት ሰዓት መነሳት እንዳለባቸው እንዲወስኑ ስሜታቸውን ማነሳሳት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## 11 ከቤና ጓደኞቹ

ከቤ፣ ተሰማና ቤለም የሚኖሩት አንድ ሰፈር ውስጥ ነው፡፡ የአንድ ት/ቤት ተማሪዎች በመሆናቸው ወደ ት/ቤት ለመሄድ ሁልጊዜ ይጠራራሉ፡፡ ተሰማ በነቤለሞ ቀሰቃሽነት ካልሆነ በጠዋት ተነስቶ ስለማይጠብቃቸው ሁል ጊዜ ወደ ት/ቤት የሚደርሱት አርፍደው ነው ፡፡ በዚህ ምክንያት መምህራቸው ወ/ሮ አስቴር በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ስጥተዋቸው ነበር፡፡

ማስጠንቀቂያው በተሰጣቸው በማግስቱ፣ በማርፈዳቸው የተደናገጡት ልጆች ት/ቤት ለመድረስ በችኮላ መሮጥ ጀመሩ፡፡ በት/ቤቱ መዳረሻ አጠገብ የመኪና መንገድ አለ፡፡ ከቤ ወላጆቹ በነገሩት መሠረት የእግረኛ ማቋረጫ መነገድ ከላገኘ በሰተቀር የመኪና መንገድ ለማቋረጥ ዝም ብሎ መግባት አይወድም፡፡ ተሰማና ቤለሞ በማርፈዳቸው ስለተደናገጡና ስለቸኮሉ የእግረኛ ማቋረጫ በሌለበት አቅጣጫ ሲያቋርጡ ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው ይተላለፍ የነበረ በስክሌት ቤለሞን ገጨውና ወደቀ፡፡ ጉልበቶቹ ተላጡ፡፡ ተሰማ እሸሻለሁ ሲል መንገድ ላይ በሲሚንቶ የተሰራው ጠርዝ አደናቅፎት በመውደቁ እጆቹን ድንጋይ ወጋው፣ እግሮቹም ቆሰሉ፡፡ ከቤ የእግረኛ ማቋረጫ መንገዱን በመጠቀም አቋርጦ ወደ ት/ቤቱ ሲደርስ ክፍል ውስጥ ጓደኞቹን በማጣቱ ምን ሆነው ይሆን ብሎ ደነገጠ፡፡

እናንተስ እንደ ከቤ ጠንቃቆች ናችሁ ወይስ እንደነ ቤለሞ ዝንጉዎች?

የተግባር ጫወታ

መጫወቻ ሜዳ ላይ አስር ህፃናትን በመስመር በማስቀመጥ ከ1 እስከ 3 ያሉ ቁጥሮችን መስጠት፡፡ ቁጥሮቹን ሌሎች ተማሪዎች እንዲመለከቷቸው ማድረግ፣ ከዚያ ቁጥር ሶስት ብሎ ኳስ መወርወር በዚያን ወቅት ሶስት ቁጥር የያዙ ልጆች ብቻ ለመቅለብ እንዲሞክሩ ማድረግ፡፡ ታዛቢ ሆነው የቆሙት ልጆች እንዲመለከቱ በማድርግ አንድ ቁጥርንና ሁለት ቁጥርን የያዙ ልጆች ሳይጠሩ በፊት መንቀሳቀስ ወይም አለመንቀሳቀሳቸውን እንዲናገሩ ማድርግ፡፡

ሳይጠሩ የተንቀሳቀሱ ልጆች ከጫወታው ይወጣሉ፡፡ በመጨረሻም አሸናፊዎቹ ልጆች ተለይተው ይጨብጨብላቸው፡፡

ይህ ጫወታ ስለአንድ ነገር ያለንን ግንዛቤ እና እውቀት፣ ቶሎ እና ፈጥኖ ውሳኔ የመስጠት ችሎታን ሊያዳብር ስለሚችል ደጋግሞ መስራት ጠቃሚ ነው፡፡

ተግባር አንድ
ለእነዚህ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ

1. ከትምህርት ቤት ውጭ ህፃናት ምን ዓይነት አደጋ የሚያስከትሉ ቦታዎች ላይ እንደሚጫወቱ መዝግበው እንዲመጡ ማድረግ፣
2. ህፃናት ቢጫወቱ አደጋ ሊደርስባቸው የማይችልባቸውን ቦታዎች በመነጋገር መዝግቡ፣
3. ወጣት ተማሪዎች ካላችሁበት ሰፈር ልዩ ልዩ ጫወታዎችን ስትጫወቱ አደጋ ሊደረስባችሁ የማይችለው ጫወታውን በምን ሁኔታ ስታከናውኑ ነው?

## 12. በመኪና ለመጓዝ ቀድመን ማሟላት የሚገባን ነገሮች

በመኪና በመንጓዝበት ጊዜ ማሟላት የሚገባንን ነገሮች መፈጸም ጉዞአችንን ያልተሰላቸ እና አስደሳች ሊያደርገው ይችላል፡፡ በተለይም ህፃናት ወደ ተለያዩ ቦታዎች በመኪና የሚጓዙ ከሆነ ጉዞው አሰለቺ እንዳይሆንባቸው መጽሐፍ ወይም ሌላውን ሳይረብሹ ሊያጫወቱባቸው የሚስችሉ ነገሮችን መያዝ ያስፈልጋል፡፡

አሽከርካሪው ከፊት ለፊቱ ያለውንና የሚመጣውን ነገር በአግባቡ መመልከት እንዲችል እይታውን ሊጋርዱ የሚችሉ ነገሮችን መስታወቱ አካባቢ አለማስቀመጥ፡፡

ህፃናት የሚቀመጡበት ወንበር ከመኪናው ጋር በደንብ የተያያዘ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ወንበሩ እንዲያያዝ መደረግ ያለበት ከፊተኛው ወንበር ጀርባ ባለው ቦታ እንጂ ነጂው አጠገብ መሆን የለበትም፡፡

ህፃናት በጉዞ ወቅት ከወንበራቸው ላይ እንዳይወድቁ የሚያደርጉ ነገሮችን ማለትም የደህንነት ቀበቶ በትክክል የታጠቁ መሆናቸውን ማረጋገጠ ይኖርብናል፡፡

## 13. በመኪና በምንጓዝበት ወቅት መውስድ የሚገባን ቅድመ ጥንቃቄ

ከእናታቸው እቅፍ የወጡ ዕድሜያቸው ከ3-10 ዓመት የሚሆናቸው ህፃናት መኪና ውስጥ በሚቀመጡበት ጊዜ ለህፃናት በተለይ በተዘጋጁ መቀመጫዎች ላይ መቀምጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ በመኪናው ወንበር ላይ በተደራቢነት የሚታሰር የህፃናት መቀመጫ ወንበር በእኛ አገር አገልግሎት ሲሰጥ አይታይም፡፡ ስለዚህ ይህ እስኪለመድ ድረስ ህፃናትን ከሾፌሩ ጀርባ ባለው ወንበር መካከለ ማስቀመጡ ተመራጭነት ይኖረዋል፡፡

ህፃናት መኪና ውሰጥ ሲቀመጡ ቀጥ ብለው መቀመጥ እንጂ የመኪናውን አካል መደገፍ የለባቸውም፡፡ መኪናው በሚያደርገው መንገጫገጭ ጊዜ ከመኪናው አካል ጋር በመጋጨት አደጋ ሊደርስባቸው ስለሚችል የመኪናውን የውስጥ አካል ሳይደገፉ ቢቀመጡ ይመረጣል፡፡

በመኪና ተሳፍረን በምንጓዝበት ጊዜ የአሽከርካሪውን ትኩረት የሚቀንሱ ነገሮችን ከማድርግ መቆጠብ ይገባናል፡፡ አሽከርካሪው ለራሱ እና ለሌሎች ተሳፋሪዎች ህይወት ሃላፊነት ያለበት መሆኑን አውቆ ሙሉ ትኩረቱን በመንገዱ እና በመኪናው እንቅስቃሴ ላይ በማድረግ ማሽከርከር ስላለበት ይህን የሚጠበቅበትን ትኩረት ማበላሽት አይኖርብንም፡፡

ህፃናት በመኪና ተሳፍረው ሲጓዙ የበሩን መክፈቻ በመነካካት መጫወት የለባቸውም፡፡ የበሩን መክፈቻ በመነካካት የሚጫወቱ ከሆነ ባልታሰበ ቅጽበት በሩ ሊከፈትና አደጋ ሊደርስባቸው ይችላል፡፡

እጅን በመኪናው መስኮት ማውጣት አደገኛ መሆኑ መታወቅ ይገባዋል፡፡ በመንገዱ ግራ ጠርዝ በሚተላለፍ መኪና ወይም ከመኪናው ቀኝ አቅጣጫ በሚተላለፍ እግረኛ ምክንያት አደጋ ሊፈጠር ስለሚችል ተሳፋሪው እጁን ከመስኮቱ ውጭ እንዳያወጣ ይመከራል፡፡

በመኪና እየተጓዙ አንዳንድ ነገሮችን፣ ማለትም የሙዝ፣ የቡርቱካን ልጣጭ፣ ዕቃ የታሸገባቸውን መረቀቶች የመሳሰሉትን በመስኮት ወደ ውጭ መጣል መንገድ ከማቆሸሹም በላይ ከኋላችን በሚመጣ መኪና መስታወት ላይ ባልታሰበ ሁኔታ በማረፍ አሽከርካሪውን አስደንግጦ አደጋ እንዲደርስ ሊያደርግ ስለሚችል፣ ልጣጩም እግረኛን በማዳለጥ ለጉዳት ሊዳርግ ስለሚችል፣ ከዚህ መሰል ድርጊት በመቆጠብ አመቺ ቦታ እና ሁኔታ እስኪገኝ ድርስ ቆሻሻውን በመኪናችን ውስጥ ማቆየት ይመረጣል፡፡

አሽከርካሪው ሙሉ ትኩረቱን መንገዱ ላይ እንዲያደርግ ሌሎች ተሳፋሪዎች ስልክ በመደወል፣ የመንገድ አቅጣጫ አመልካች በማንበብ እና ሌሎች የአሽከርካሪውን ተደራራቢ ስራ ማገዝ ሊደርስ የሚችል አደጋን ለማስቀረት ከሚደርግ ጥረት ተለይቶ አይታይም፡፡

## 14. አሽከርካሪዎች መከተል ያለባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች

በተሽከርካሪዎች በምንጠቀምበት ጊዜ መፈፀም የሚገባን በርካታ የጥንቃቄ እርምጃዎች አሉ፡፡ አሽከርካሪው ወደ መኪናው እንደገባ ሁል ጊዜ የጥንቃቄ ቀበቶውን ማሰር ይኖርበታል፡፡ የደህንነት ቀበቶ ማሠር ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በከፍተኛ መጠን ሊቀንስ እንደሚችል በጥናት ተረጋግጧል፡፡

በእኛ አገር ይህ ሁኔታ የተለመደ ባለመሆኑ በአሽከርካሪዎችም ሆነ በተሳፋሪዎች ላይ የሚደርሱት አደጋዎች አሰቃቂ እና ዘግናኝ ሲሆኑ ይታያሉ፡፡

በመኪናዎች የሚደርሰው አደጋ እንደፍጥነታቸው ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡ አደጋ እንዳይደርስ ለመቆጣጠር የሚያግዘን ፍሬን የተባለው ክፍል ውጤታማ በሆነ ሁኔታ መኪናው ቀጥ ብሎ እንዲቆም ማድረግ የሚችለው መኪናው ፍጥነቱ ከፍተኛ ካልሆነ ነው፡፡ ነገር ግን መኪናው ከፍተኛ ፍጥነት ያለው ከሆነ ፍሬን ተይዞ እንኳን ወደፊት ሊንሸራተት ስለሚችል ወዲያው ቀጥ አድርጐ ለማቆም አይቻልም፡፡ ስለዚህ አሽከርካሪዎች ለመንገዱ ከተፈቀደው ፍጥነት በላይ መንዝ አለመንዛቸውን ለማወቅ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ የፍጥነት መቆጣጠሪያውን ማየት ይኖርባቸዋል፡፡

በእርጥበት፣ ወቅት ማለትም ዝናባማ እና ጭቃማ በሆነ፣ ጊዜና በደረቃማ ወቅት በተመሳሳይ ፍጥነት ልንንዝ አንችልም፡፡ መንገዱ ጭቃማ ወይም እርጥብ ከሆነ በቀላሉ ሊያንሸራትት ስለሚችል ፍጥነት ቀንሰን ተገቢውን ጥንቃቄ በማድርግ መንዝ ያስፈልጋል፡፡

በምሽት ወይም በጭጋጋማ ጊዜ ከፊት ለፊታችን የሚመጣን ነገር ከሩቁ በግልጽ ማየት ስለማይቻል በዝግታ መንዝ የመረጣል፡፡

መጠጥ የአዕምሮን የማመዛዘን አቅም የሚያሳጣ በመሆኑ፣ ጠጥቶ ማሽከርከር አደጋ እንዲደረስ ሁኔታዎችን በገዛ ፍቃድ ከማመቻቸት ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡

አንድ ሰው መኪና የማሽከርከር ሀሳብ ካለው መጠጥ መጠጣት የለበትም "ከጠጡ አይንዱ፣ ከነዱ አይጠጡ" የሚባለው መጠጥ ሊያስከትል የሚችለው የአጉል ድፍረት እና ጀብደኝነት ስሜት ለአደጋ መፈጠር ምክንያት ሊሆን የሚችል መሆኑን በይበልጥ መገንዘብ ይገባናል፡፡

መሪ የመኪናው እንቅስቃሴ ተገቢውን አቅጣጫ እንዲይዝ መቆጣጠርያ አካል ነው፡፡ ይህንን መቆጣጠሪያ አካል በአንድ እጅ ብቻ በመያዝ በሌላው እጃችን ሌላ ስራ ለመስራት መሞከር ሙሉ ሃሳባችንን በማሽከርከሩ ላይ እንዳናደርግ ያደርገናል፡፡

በአንዳንድ አገሮች በአንድ እጅ የመኪና መሪ ይዘው በሌላው እጃቸው የሙባይል ስልኮችን እንዳይጠቀሙ የሚከለክል ህግ አላቸው፡፡ በሞባይል ስልክ እያወሩ ማሽከርከር ሊፈጠር የሚችለውን አደጋ ከፍ ሊያደርግ ስለሚችል ማንኛውም አሽከርካሪ ሙባይል ስልክ መጠቀም ከፈለገ መኪናውን ዳር አስይዞ አቁሞ መጠቀም ይገባዋል፡፡ አሽከርካሪው ሁለቱንም እጆቹን መሪው ላይ በማድረግ ለማሽከርከር ተግባር ብቻ ማዋል እንዳለበት ይመከራል፡፡

የመኪና መቆጣጠሪያ አካላት ለተሽከርካሪው ስርዓታዊ እንቅስቃሴ ከመርዳታቸውም በላይ ሌሎች አሽከርካሪዎች ከዚህኛው መኪና በሚያገኙት ትክክለኛ መልእክት አደጋ እንዳያደርሱ

እግዛ ያደርጋል፡፡ መኪናው ወደ ቀኝ ሊዞር ከፈለገ በቀኝ በኩል ያለውን ፍሬቻ ማብራት አለበት፡፡ ይህ ባለተሟላ ሁኔታ ቢዞር ከኋላ በሚመጣ ተሽከርካሪ ሊገጭ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

አሽከርካሪዎች በወንበራቸው ላይ ተመቻችተው መቀምጥ አለባቸው፡፡ ባልተስተካከለ ሁኔታ ወይም ተጣበው ወይም በጐናቸው ቢቀመጡ ሙሉ ሀይላቸውን ተጠቅመው የመኪናውን አካላት እየተቆጣጠሩ ሊያሽከረክሩ አይችሉም፡፡

ከላይ ያየናቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች በአሽከርካሪዎች ተሟልተው መፈጸም አለባቸው፡፡ ልጆች እናንተም ጉበዝ ተማሪ ሆናችሁ፣ ትልቅ ሰው ስትሆኑ የራሳችሁን መኪና ገዝታችሁ ስታስከረክሩ እነዚህን የጥንቃቄ እርምጃዎች መውሰድ ይኖርባችኋል፡፡ እስከዚያው ይህን የተማራችሁትን ለምታውቋቸው አሽከርካሪዎችና ለወላጆቻችሁ በመግለጽ የመኪና አደጋ እንዳይፈጠር የበኩላችሁን እገዛ ማድረግ ትችላላችሁ፡፡

<u>የክፍል ውስጥ ተግባራት</u>
<u>ተግባር አንድ</u>

አሽከርካሪዎች አደጋ ሳያደርሱ እንዲያሽከረክሩ የሚያሳስቡ መፈክሮችን ጽፋችሁ ኑ ተብላችሁ በመምህራችሁ ብትጠየቁ ምን ዓይነት መፈክር ልትጽፉ እንደምትፈልጉ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

<u>ተግባር ሁለት</u>
ደህንነትን አስመልክቶ ምን የምታውቁት ታሪክ አለ? ለምሳሌ የደህንነት ቀበቶ ባለመታጠቅ ፍሬን በድንገት ሲያዝ ፊት ለፊት ካለ የመኪና መስታወት ወይም የመኪና አካል ጋር መጋጨት፤ የመሳሰሉ ታሪኮችን ሰምታችሁ ወይም አይታችሁ ከሆነ ወይም ወላጆቻችሁንና መምህራኖቻችሁን በመጠየቅ ተወያዩበት፡፡

<u>ተግባር ሶስት</u>

1. ህፃናት ረጅም ጉዞ በሚጓዙበት ጊዜ የአሽከርካሪውን ትኩረት ሳይረብሹ እንዴት ራሳቸውን እያዝናናኑ ሉጓዙ ይችላሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? የአሽከርካሪውን ትኩረት ሊረብሹ የሚችሉ ተግባራት ምንድናቸው? እነዚህን ከጓደኞቻችሁ ጋር ተነጋገሩ፡፡
2. አሽከርካሪዎች መከተል ካለባቸው የጥንቃቄ እርመጃዎች ውስጥ በዋነኛነት መተኮር ያለበት የትኛው ነው ትላላችሁ? ለምን?

## <u>15. እግረኞች መከተል ያለባቸው ልዩ የጥንቃቄ ደንቦች</u>

አንዳንድ ሰዎች የእግረኛ መንገዱ በእግር ለመሄድ ምቾት የማይሰጥ በሚሆንበት ጊዜ የመኪና መንገዱን በመጠቀም ሲጓዙ ይታያሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት የመንገድ አጠቃቀም አደጋ ያስከትላል፡፡

ሀ. በመንገዱ ላይ ከሚተላለፉ መኪናዎች አንዱ ባልጠበቅነው እና ባላሰብነው ሁኔታ አደጋ ሊያደርስብን ይችላል፡፡
ለ. የሆነ ነገር አደናቅፎን ወይም ከመኪና አደጋ ለመሸሽ ስንሞክር የአስፍልቱ (የመንገዱ) ጠርዝ ሊጐዳን ይችላል፡፡
ሐ. የመንገዱን ዳር ይዘን በቆሙ መኪናዎች አጠገብ ስናልፍ በድንገት የመኪናው በር ከውስጥ ሊከፈት ስለሚችል በዚህ ልንመታና ልንጐዳ እንችላለን፡፡

ስለዚህ እግረኞች በተቻለ መጠን የእግረኛን መንገድ ይዘው መጓዝ ይኖርባቸዋል እንጂ የመንገዱን መስተካከል በማየት የመኪና መንገድ ውስጥ ገብቶ ለመጓዝ መሞከር ራስን ለአደጋ ማጋለጥ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

በአደባባዮችና ተሽከርካሪዎች በሚበዙባቸው ይበልጥ ለአደጋ የተጋለጠ የከተማ መንገዶች የእግረኞችን መሄጃ ከመኪና መንገድ ለመለየት የብረት አጥሮች ተሰርተው ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም እግረኞች ለነሱ ከተፈቀደው መጓዣ መንገድ ውጭ አጥሩን አልፎ በመግባት ለመጓዝ ወይም መንገዱን ለማቋረጥ መሞከር ለአደጋ መጋለጥ ይሆናል፡፡

ጐን ለጐን በሚሄዱ ሰዎች የእግረኛ መንገዱ በመያዙ የተነሳ ወደ መኪና መንገድ ገብቶ ለመጓዝ መሞከሩ አደጋ ሊያስከትል ስለሚችል፡፡

ሀ. የምትጓዙት በሰወቹ አቅጣጫ ተቃራኒ ከሆነ ቆማችሁ ብታሳልፉ
ለ. የምትጓዙት ሰዎቹ በሚሄዱበት አቅጣጫ ከሆነ እንዲያሳልፏችሁ ይቅርታ መጠየቁ የበለጠ ተመራጭነት አለው፡፡

በምሽት ጊዜ በመኪና መንገድ ላይ የምተጓዙ ከሆነ አንጸባራቂ ያላቸው ወይም ነጣ ያሉ ልብሶችን መልበሱ ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም ጠቆር ካሉ ልብሶች ይልቅ ነጣ ያሉ ልብሶች በቀላሉ ስለሚታዩ አሽከርካሪዎች በርቀት በማየት ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ስለረዳቸው ነው፡፡ ነገር ግን ነጣ ያሉ ልብሶችን ብትለብሱም ጥንቃቄ ማድረጉን መርሳት የለባችሁም፡፡

የግድ የመኪና መንገድ ተጠቅማችሁ መጓዝ የሚኖርባችሁ ከሆነ የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዛችሁ መጓዝ ይኖርባችኋል፡፡ የግራ ጠርዙን ይዛችሁ ስትጓዙ የሚያጋጥማችሁ ከፊት ለፊት የሚመጣ መኪና በመሆኑ የመኪናውን አመጣጥ በማየት ጥንቃቄ ልታደርጉ ተችላላችሁ፡፡

የመኪና መንገዱን ቀኝ ጠርዝ ይዞ መሄድ ለአደጋ ያጋልጣል የሚባለው መኪናው ከበስተኋላችሁ ስለሚመጣ እናንተም አመጣጡን ስለማታዩ ልትጠነቀቁ ስለማትችሉ ለአደጋ የመጋለጡ ሁኔታ በግራ በኩል ከሚጓዙት እግረኞች የበለጠ ነው፡፡

የመኪና መንገድ ውስጥ ገብቶ መጓዙ አደገኛ ሲሆን፣ በተለይም የመኪናውን መንገድ ከእግረኛው መንገድ የሚለይ በድንጋይ ወይም በሲሚንቶ የተሰራ ከፍ ያለ ጠርዝ ያለው ከሆነ፣ በፍጥነት ለማምለጥ ስንል ጠርዙ አደናቅፎን ለከፋ አደጋ ልንጋለጥ እንችላለን፡፡

ልጆች፣ መንገድ በምታቋርጡበት ጊዜ በተቻለ መጠን እግረኞች እንዲያቋርጡባቸው ነጭ ቀለም በተቀባባቸው ቦታዎች ላይ ብቻ ማቋረጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በገጠር አካባቢ ያላችሁ ከሆነ መንገዱን ከማቋረጣችሁ በፊት በግራ እና በቀኝ የመንገዱን አቅጣጫዎች በመመልከት መኪና በቅርብ ርቀት ያልደረሰ መሆኑን በማረጋገጥ ማቋረጥ ይኖርባችኋል፡፡

## 16. በሁለት አቅጣጫ መኪናዎች የሚሄዱበትን መንገድ ስንጠቀም ማድረግ ያለብን ጥንቃቄ



**ስእል 30**
**በመንገድ አካፋይ ደሴት ላይ ቆሞ ወደቀኝ መመልከት**

በሁለት አቅጣጫ መኪናዎች የሚሄዱበትን መንገድ ስናቋርጥ፣ ምንም እንኳን የምናቋርጠው በእግረኛ ማቋረጫ ቢሆንም፣ ከማቋረጣችን በፊት ግራና ቀኛችንን በማየት መንገዱ ከተሽከርካሪ የፀዳ መሆኑን አረጋግጠን ቢሆንም ከመንገዱ መካከል ስንደርስ ወደ ቀኝ በማየት ከሌላኛው አቅጣጫ የሚመጣ መኪና መኖር አለመኖሩን ሳናረጋግጥ ቀሪውን የመንገዱን ግማሽ ለማቋረጥ መሞከር የለብንም።

የትራፊክ መብራት ስለበራ ወይም የእግረኛ ማቋረጫ በመሆኑ ብቻ ፈጥናችሁ ወደ ማቋረጫው ከመግባታችሁ በፊት፤ ለጥቂት ሰኮንዶች ያህል ቆም ብላችሁ መንገዱ ከመኪና የፀዳ መሆኑን ወይም ከማቋረጣችን በፊት ሊደደርስ የሚችል መኪና አለመኖሩን ወይም አሽከርካሪው ልታቋርጡ መንገድ መጀመራችሁን ማየቱንና መኪናውን ማቆሙን እርግጠኛ ልትሆኑ ይገባል።


በእናንተ ዕድሜ የሚገኙ ልጆች ቁመታቸው አጭር ስለሚሆን አንዳንድ ጊዜ ከአሽከርካሪው እይታ ውጭ ስለሚሆኑ አሽከርካሪው በእግረኛ ማቋረጫ ሰው የለም በሚል ግምት በፍጥነት ሊያልፍ ሲሞክር አደጋ ሊያደርስ ስለሚችል ከማቋረጣችሁ በፊት አሽከርካሪው እንደተመለከታችሁ እርግጠኛ ለመሆን መሞከር አለባበችሁ።

መኪና ተከልሎ ለማለፍ መሞከር እጅግ አደገኛ ነው። ምክንያቱም እናንተ ከፊት የሚመጣ መኪና መኖር አለመኖሩን ለማየት በማያስችል ሁኔታ ውስጥ ስለምትሆኑ፣ አሽከርካሪውም ስለማያያችሁ፣ ለከፋ አደጋ ሊዳርጋችሁ ይችላል።



ስእል 31
የቆመ መኪና ተከልሎ ለማለፍ መሞከር

መንገድ የምታቋርጡት የትራፊክ መብራት ባለበት አካባቢ ከሆነ መብራቱ ቀይ በርቶ መኪናዎች መቆማቸውን በማረጋገጥ ወይም የተንዣ ሰው ስዕል ያለበት ከሆነ ደግሞ የተንዥ ስእሉ አረንጓዴ ያበራ መሆኑን ስናረጋግጥ ብቻ መሆን አለበት። በአገራችን ያሉ የትራፊክ መብራቶች እነዚህን ሁለት ምልክቶች አቀናጅተው የያዙበት ሁኔታ የለም። ይህ ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው ሲሆን በኛ አገር የቀዩ መብራት መታየት ለመኪና መቆም፣ ለእግረኛ ጉዞ መንቀሳቀስ መፍቀጃያ ተደርጉ ይወሰዳል። ሆኖም ግን መብራትም ቢኖር ሁል ጊዜ መኪናዎች መቆማቸውን ሳታረጋግጡ ለማቋረጥ አትሞክሩ።



ስእል 32
የህጻናት ምልክት ያለው መብራት አረንጓዴ ሲበራ አይቶ ማቋረጥ

መንገድ በሩጫ ማቋረጥ የሚመከር አይደለም፡፡ ሲያቋርጡ በጣም ዝግማለትም ወይም መቆም ለአደጋ ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ ስለዚህ ፈጠን ብሎ በመራመድ ማቋረጥ ተመራጭ ነው፡፡ በምንም ዓይነት መንገድ ላይ መንገድ ስታቋርጡ በቀጥታ እንጂ በአግድሞሽ/በሰያፍ መሆን የለበትም፡፡

የመኪናን መምጣት በሚያሰማው ድምጽ ልናውቅ እንችላለን፡፡ ብስክሌቶች ግን ድምፃቸው ስለማይሰማ አደጋ ሊያደርሱብን ስለሚችሉ መንገድ ስንጠቀም ወይም ስናቋርጥ እነዚህ ድምፀ ጉልህ ያልሆኑ ተሽከርካሪዎች አደጋ እንዳያደርስቡን መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡





ትክክል ያልሆነ መንገድ ማቋረጥ | ትክክል የሆነ መንገድ ማቋረጥ

ስእል 33
ትክክል የሆነና ያልሆነ መንገድ ማቋረጥ

መኪናዎች በተለየ ሁኔታ የሚጠቀሙበት በፍጥነት የሚጓዙበት መንገድ ወደፊት በብዛት የሚስራበት ሁኔታ እንደሚኖር የሚታሰብ ቢሆንም በአገራችን በአሁኑ ጊዜ በብዛት የለም፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ የቀለበት መንገድ በሚል ስያሜ የተሠራ መንገድ አለ፡፡ ይህን የቀለበት መንገድ ለማቋረጥ ስንፈልግ ነጭ ቀለም የተቀባበት የእግረኛ ማቋረጫ ልናገኝ አንችልም፡፡ በዚህ ፋንታ መንገዱን ለማቋረጥ የተሠሩ ድልድዮች ናቸው ያሉት፡፡ እነዚያን ድልድዩች በመጠቀም መሻገር ይኖርብናል፡፡ ፈጥነን ማለፍ እንችላለን በሚል ግምት እግረኛ እንዳይገባ ለማገድ የተሠሩ የብረት ወይም የድንጋይ አጥሮችን በመዝለል ለማለፍ መሞከር ራስን አደጋ ውስጥ ከመጣል ያነሰ ድርጊት አይሆንም፡፡



ስእል 34
እግረኛ እንዳይገባ የተሰሩ የብረት አጥሮች

የእግረኛ ማቋረጫ የቅብ ምልክት (ዜብራ ቅብ) ተጠቅመን መንገድ የምናቋርጥ ቢሆንም በጉናችን ካለው መንገድ እኛ እያቋረጥንበት ወዳለው መንገድ መኪና ሊመጣ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ በማወቅ መጠንቀቅ አለብን፡፡

አንድ አቅጣጫ ብቻ ይዘው መኪኖች የሚጠቀሙበትን መንገድ ከማቋረጣችሁ በፊት መኪና ወደየትኛው አቅጣጫ ብቻ እንደሚጓዝ በጥንቃቄ በማየት ማረጋገጥ አለባችሁ፡፡

የመኪና ጋራዥ ባለበት አካባቢ ስትሄዱ ወይም የመኪና ማቆሚያ አካባቢዎች ላይ ስትጓዙ የሚንቀሳቀሱ መኪናዎች አደጋ እንዳያደርሱባችሁ ጥንቃቄ ልታደርጉ ይገባል፡፡

<u>ተግባር አንድ</u>
<u>ለነዚህ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡</u>

1. እግረኞች ደህንነታቸውን ጠብቀው እንዲጓዙ የሚረዷቸውና መፈፀም ያለባቸው ዋናዋና ተግባራት ምን ምን ናቸው?
2. የመኪና መንገድ ስናቋርጥ ማድረግ የሚገባን ጥንቃቄዎች ምንድናቸው?
3. በሁለት አቅጣጫ መኪና የሚጠቀምበትን መንገድ ከማቋረጣችን በፊት ምን ማድረግ ይገባናል?
4. የእግረኛ መንገድ ሲባል ምን ማለት ነው?
5. ስለትራፊክ እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ መብራቶች አገልግሎትና ጥቅም በዝርዝር ግለፁ?
6. በአንድ አቅጣጫ ብቻ መኪናዎች የሚጓዙበትን መንገድ ስናቋርጥ ምን ጥንቃቄ ማድረግ አለብን?
7. የእግረኛ ማቋረጫ ምልክት /ዚብራ ምልክት / በሌለባቸው ቦታዎች መንገድ ስታቋርጡ ማድረግ ያለባችሁ ጥንቃቄ ምንድ ነው?

## ተግባር ሁለት

## ትክክለኛ የሆነውን ሀሳብ እውነት፣ ትክክል ያልሆነውን ስህተት ብላችሁ መልሱ።

1. የመኪና መንገድ በሩጫ ለማቋረጥ መሞከር አደጋ ላያስከትል ይችላል።
2. መንገድ ስናቋርጥ አደጋ ሊያደርሱብን ከማይችሉ ነገሮች ውስጥ አንዱ ብስክሌት ነው።
3. የቆመ መኪና ተከልሎ ለማለፍ መሞከር የሚያስከትለው ምንም ዓይነት አደጋ የለም።
4. በእግረኛ ማቋረጫ መንገድ በዝግታ ብታቋርጡ ወይም ቆም እያላችሁ ብትጓዙ የሚደርስባችሁ አደጋ የለም።
5. ቀለበት መንገድ ላይ ያሉ የእግረኛ ማቋረጫ ድልድዮች ለእንስሳት መተላለፊያ እንጂ ለሰው መተላለፊያ የተሰሩ ባለመሆናቸው ማቋረጫ ድልድዩን ባንጠቀምም አደጋ ሊደርስብን አይችልም።
6. አረንጓዴ የትራፊክ መብራት ሲበራ ማቋረጭ የተፈቀደ በመሆኑ የሚደርስባችሁ የመኪና አደጋ አይኖርም።

## ተግባር ሶስት

## ከዚህ በታች በምታነቡት ሁኔታ ከቤ መንገዱን ቢያቋርጥ ጠንቃቃ ነው ማለት እንችላለን?

1. ቀኝ እና ግራ ካየ በኋላ ደግሞ ወደ ቀኝ በማየት መንገዱን ቢያቋርጥ ትክክል ነው?
2. ከቤ በእግሩ ሲጓዝ የመንገዱን ቀኝ ጠርዝ በመያዝ ነው።
3. ከቤ የእግረኛ ማቋረጫ በመጠቀም የትራፊክ መብራቱ አረንጓዴ ሰው የተሳለበት ቀይ ቀለም ሲበራ ሲበራ ያቋርጣል።

ልጆች፡- የከቤን የመኪና መንገድ አጠቃቀም ስናይ ጠንቃቃ አለመሆኑን እንገነዘባለን ። ምክንያቱም

1ኛ- የመኪና መንገድ ስናቋርጥ ቀድመን ማየት ያለብን የመንገዱን ግራ አቅጣጫ ሲሆን ከዚያ ወደ ቀኝ ዞረን በማየት መኪና አለመኖሩን ማረጋገጥ ይኖርብናል። መኪና አለመኖሩን እርግጠኛ ሳንሆን ወይም ከማቋረጣችን በፊት እየመጣ ያለው መኪና እንደማይደርስብን ደግመን ወደ ግራ በማየት አረጋግጠን ለማቋረጥ መንቀሳቀስ ይኖርብናል፤ ከቤ ግን ይህን ባለማድረጉ ጠንቃቃ ነው ልንለው አንችልም።

2ኛ- በገጠርም ሆነ በከተማ ከዋናው የመኪና መንገድ ዳር እና ዳር የእግረኛ መንገድ በማይኖርበት ጊዜ የግድ የመኪና መንገድ ውስጥ ገብተን ለመንጓዝ የምንገደድ ከሆነ መጠቀም የሚገባን የመንገዱን ግራ ጠርዝ ብቻ ነው። ነገር ግን ከቤ የተጠቀመው የመንገዱን ቀኝ ጠርዝ በመሆኑ ጠንቃቃ ልጅ ነው አያሰኘውም።

3ኛ- የእግረኛ ማቋረጫ ምልክት ባለበት መንገድ አጠገብ የትራፊክ መብራት ካለ፣ ቀይ መብራቱን በማየት፣ የሰው ምልክት ያለበት ከሆነ አረንጓዴ መብራት ሲበራ በማስተዋል መኪናዎቹ መቆማቸውን እርግጠኛ ስንሆን ብቻ ማቋረጥ ይገባናል። ከቤ ይህን ባለማድረጉ ጠንቃቃ ልጅ ነው አያሰኘውም።

## ተጨማሪ መልመጃዎች

1. የመኪና መንገዱ ጠርዝ በድንጋይ ወይም በሲሚንቶ ኮንክሪት ትንሽ ከፍ ተደርጐ በተሰራበት ቦታ ውስጥ ገብታችሁ፣ የመንገዱን ግራ አቅጣጫ ይዛችሁ ብትሄዱ ምን የሚገጥማችሁ ችግር አለ?
2. የመንገዱን ማንኛውንም ጠርዝ ይዘን ስንጓዝ በቆመ መኪና አጠገብ ለማለፍ ስንሞክር ምን አደጋ ሊያጋጥመን ይችላል?
3. በየትኛው ሁኔታ ነው እግረኛ ሲያቋርጥ አደጋ ሊያጋጥመው የሚችለው?

1. ተሽከርካሪ ተከልሎ ሲያቋርጥ?
2. የሰው ምስል ያለው አረንጓዴ መብራት ሲበራ?
3. ለእግረኛ ማቋረጫ በተቀባ ስፍራ ተጠንቅቆ ሲያቋርጥ? ወይስ
4. ባለሁለት አቅጣጫ መንገድ ላይ በመጀመሪያ ወደግራ ማህል ደሴቱ ላይ ሲደርስ ደግሞ ወደቀኝ አየቶ ተጠንቅቆ ሲያቋርጥ?

**ከላይ ለተነሱት ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች**

1. የእግረኛ መንገድ ባለበት ቦታ የመኪና መንገድ ውስጥ ገብተን ብንጓዝ የመንገድ ጠርዝ ተጠግቶ በአደገኛ ሁኔታ የሚመጣ መኪና ካለ ያን በማየት ልንሸሽ ስንሞክር አደናቅፎን በመውደቅ የመቁሰል ወይም በመደናቀፍ የመኪና አደጋ ሊደርስብን ይችላል፡፡
2. መኪና ውስጥ ያለው ሰው በድንገት የመኪናውን በር የሚከፍተው ከሆነ በበሩ ልንመታ እና ልንጐዳ እንችላለን፡፡
3. የቆመ ተሽከርካሪን ተከልሎ ለማለፍ መሞከር ለአደጋ ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ ምክንያቱም ከፊት ያለው መኪና የልጁን እንቅስቃሴ በማየት ሊቆም የሚችል ቢሆንም ከኋላ ያለው መኪና የልጁን ወደ እግረኛ ማቋረጫ ውስጥ መግባቱን ላያይ ስለሚችል አና በመጣበት ፍጥነት ሲጓዝ ልጁን ሊገጨው ይችላል፡፡

ስለዚህ መኪናዎች በዚህ ሁኔታ እየመጣ ባለበት ሁኔታ የእግረኛ ማቋረጫ ቢኖርም ሁኔታው አመቺ እስኪሆን ድረስ ቆም ብሎ ማሳለፍ ያስፈልጋል፡፡

**ተጨማሪ ተግባር**
**የተፃፉትን ቃላት በመጠቀም ከስር የቀረበውን ታሪክ አሟሉ**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ሲያቋርጥ<br>2. ቀና | 3. ጠንቃቃ<br>4. ትንሽ | 5. ማየት<br>6. በእግሩ | 7. መጠን<br>9. ሊያዩት | 9. አጭር |

1. መገርሳ የ9 ዓመት ልጅ ነው፡፡ ሁልጊዜ ወደ ት/ቤት የሚሄደው ___________ነው፡፡
2. _________ ልጅ በመሆኑ አሽከርካሪዎች ከሩቅ ______ አይችሉም፡፡
3. የእሱ__________ መሆን ከፊት ለፊቱ የሚመጡትን መኪናዎች በሙሉ ለማየት አያመቸውም፡፡
4. በመሆኑም መንገድ ___________በጣም______ መሆን ይገባዋል፡፡
5. ምክንያቱም የትራፊክ መብራቶች እና ምልክቶች ቢኖሩም ከቁመቱ ______ ከፍ ያሉ በመሆናቸው ሊያያቸው አይችልም፡፡
6. ስለዚህ ከአንገቱ_________በማለት የተሽከርካሪዎቹን እንንቅስቃሴ በ_____________ መንገዱን ማቋረጥ ይገባዋል፡፡

## 17. የአስተዋይነት ጠቀሜታ

ትጉሁ፣ ብልሁና ጠንቃቃው ድርፉጮ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በማጠናቀቅ ጥሩ ውጤት በማምጣቱ ለከፍተኛ ትምህርት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተመደበ፡፡

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ከተሞች ሁሉ እጅግ ሰፊ ከተማ ነው፡፡ በርካታ መኪናዎች በከተማው ውሰጥ ይገኛሉ፡፡ ከገጠር ወደ ከተማ ለመጣ ሰው አዲስ አበባ ውስጥ የሚታየው የመኪናዎች እንቅስቃሴ እጅግ የሚያስፈራበት ሁኔታ አለ፡፡

ብዙዎቹ የከተማው ውስጥ መንገዶች አስፋልት የለበሱ ቢሆንም በበርካታ ቦታዎች የእግረኛ መንገድ ያልተሰራላቸው በመሆኑ የመኪና አደጋ በብዛት ያጋጥማል ፡፡

በየቀኑ አደጋች በእግረኞች ላይ ስለሚደርስ ድርፉጮ ከሚማርበት የዩነቨርስቲው ግቢ በሚወጣበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋል፡፡

መንገድ ሲያቋርጥ በእግረኛ ማቋረጫ ይጠቀማል፡፡ ሁል ጊዜ ሲጓዝ የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዞ ነው፡፡ የመንገድ ላይ የትራፊክ መብራቶችን በጥንቃቄ በማስተዋል ቀይ መብራት ካልበራ በፍፁም መንገድ ማቋረጥ አይሞክርም፡፡

አንዳንድ ጓደኞቹ፣ የገጠር ልጅ በመሆኑ ነው መኪና የሚፈራው እያሉ ያሾፉበታል፡፡ "ሞኙ ድርፉጮ የእግረኛ ማቋርጫ መንገድ ካላገኘ መንገድ ማቋረጥ አይደፍርም" እያሉ ይቀልዱበት ነበር፡፡ ብዙ ቀን "ና እጅህን ይዘን መንገዱን እናሻግርህ፣ መኪና ቢመጣ እንኳን ሮጠን ማለፍ እንችላለን" ይሉታል፡፡ እሱ ግን በቀልዳቸው ሳይናደድ ረጋ ብሎ "ለምን ለኛ ደህንነት ሌላ ሰው እንዲያስብልን ትፈልጋላችሁ? የተማረ ሰው የደህንነት ደንቦችን በማወቅ ለሌላው ህዝብ ምሳሌ መሆን ይገባዋል እንጂ ደንቡን ለማፍረስ አርአያ መሆን አይገባውም" እያለ ይመክራቸዋል፡፡

ከጠጠር መንገድ የበለጠ አደጋ የሚደርሰው በጥሩ አስፋልት መንገድ ላይ መሆኑን ማወቅ እንደሚገባቸውና በዚህም የተነሳ በአዲስ አበባ ከተማ በአማካኝ በቀን አንድ ሰው እንደሚሞት፣ ከዚህም ከሚጎዳውም ውስጥ 80 ከመቶው እግረኛው መሆኑን በማወቅ መጠንቀቅ እንደሚገባቸው ያሳስባቸው ነበር፡፡

ጥቂት ጓደኞቹ የሱ ሀሳብ ከፍርሃት የመነጨ አድርገው ቆጠሩት፡፡ የድርፉጮ ጓደኞች አንድ ቀን ከዩንቨርስቲ ግቢ ወጥተው ወደ ከተማ ሲሄዱ በመኪና መንገዱ ላይ ያለውን እንቅስቃሴ አትኩረው ሳያገናዝቡ፣ ስለፈተና መድረስ እያወሩ፣ መንገድ በማቋረጥ ላይ ነበሩ፡፡ አዎን በዚያን ጊዜ ነበር በጣም እየፈጠኑ የሚመጡ መኪናዎች አጠገባቸው እንደደረሱ ያዩት፡፡ አንድ ጓደኛቸው ሮጦ ለመሻገር ሞከረ፡፡ ነገር ግን መኪናው በፍጥነት ይጓዝ ስለነበር ሾፌሩ ፍሬን ቢይዝም በመንሸራተቱ ልጁ በሚያሳዝን ሁኔታ በመኪናው ተገጭቶ ወደቀ፡፡

ሌሎቹ ግን ከአደጋው ቢተርፉም በጓደኛቸው መሞት በጣም አዘኑ፡፡ ትምህርቱን ሊጨርስ ሁለት ወራት የቀረው ጓደኛቸው በዚህ ሁኔታ ህይወቱ በማለፉ በራሳቸው ድርጊት ተበሳጩ፡፡ "ለራሳችን ደህንነት ማሰብ ያለብን እኛ ነን" እያለ ድርፉጮ የሚያቀርበው ሀሳብ ትክክል እንደነበር አምነው፤ የመኪና አደጋ እንዳይደርስ እግረኞች ለራሳቸው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ምሳሌ ለመሆን ጥረት ለመጀመር ቃል ገቡ፡፡

## ተግባር አንድ

## ጥያቄዎቹን በማንበብ ትክክል ለሆነው እውነት፣ ትክክል ላልሆነው ስህተት ብላችሁ መልሱ

1. በአስፋልት የተሠሩ መንገዶች ምቹ በመሆናቸው የመኪና አደጋ ሊያጋጥም አይችልም፡፡
2. አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ለእግረኛ መሄጃነት የተሰሩ መንገዶች አሏቸው፡፡
3. ድርፋጮ የዩንቨርስቲ ተማሪ በመሆኑ የመኪና አደጋ ይደርስብኛል ብሎ አይጠነቀቅም
4. የድርፋጮ ጓደኞች የሚያሾፉበት የሚለብሰው ልብስ ንፁህ ባለመሆኑ ነው፡፡
5. አዲስ አበባ ውስጥ የመኪና አደጋ የሚበዛው ትክክለኛ የመቆጣጠሪያ መሳሪያዎች የሌሏቸው መኪናዎች ስለሚበዙ ነው፡፡

## ተግባር ሁለት

## እያንዳንዱን ጥያቄ በማንበብ አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. በከተሞች ውስጥ የመኪና አደጋ የሚደርስባቸው ዋነኛ ምክንያቶች ምንድ ናቸው?
2. የተማረ ሰው ለሌሎች ሰዎች ምሳሌ የሚሆነው ምን በማድረግ ነው?
3. የድርፋጮ ጓደኞች ምክሩን ያልሰሙት ለምን ይመስላችኋል?
4. ወሬ እያወሩ መንገድ ማቋረጥ የመኪና አደጋ የሚያስከትለው እንዴት ነው?
5. የከተማ ልጅ መሆናችን መኪና እንዳይገጨን ሊረዳን ይችላል?
6. እናንተስ ከዚህ ታሪክ ምን ትማራላችሁ?



በመኪና መንገድ ላይ በቀን የሚታይ እንቅስቃሴ



በመኪና መንገድ ላይ በማታ የሚታይ እንቅስቃሴ

መልዕክት፡- አስተውሎ መንዳት ዓላማን ለማሳካት ያስችላል፡፡

## 1. የተሽከርካሪ አጀማመር አጭር ታሪክ።

ኑሮ ትግል ነው። የሰው ልጅ የኑሮ ጫናውን ለማቃለል የተለያዩ ጥረቶችን በማድረግ ላይ ይገኛል። ካደረጋቸው እና እያደረጋቸው ካሉ ጥረቶች ውሰጥ ተሽከርካሪዎችን ለሰውና ለዕቃ መጓጓዣነት መጠቀም መቻል ነው።

ጥንታዊ ተሽከርካሪዎች በእንሰሳት የሚጐተቱ፣ በእንፋሎት ሀይል የሚሰሩ ነበሩ። ከዚያ ዕድገቱ እየቀጠለ በጋዞሊን የሚሰሩ መኪናዎች እየተፈላለፉ አሁን ያለንበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ተችሏል።

አንድ ወይም ሁለት ሰዎችን ከሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎች ተነስተን አሁን ባለንበት ወቅት አንድ መርከብ ከ3,000 በላይ ሰዎችን ሊያጓጉዝ የሚችልበት፣ አንድ አውሮፕላን ከ500 ሰዎች በላይ የሚያሳፍርበት ጊዜ ላይ ተደርሷል።

ተሽከርካሪዎች በመንገድ ላይ በሚመላለሱበት ወቅት ያለ አደጋ በስርዓት እንዲጓጓዙ የሚያገለግል የትራፊክ ደንብ ሁሉም አገሮች ይጠቀማሉ። በዓለማችን ላይ በብዙ ሚሊዩን የሚቆጠሩ ተሽከርካሪዎች ሲኖሩ ሁሉም ተሽከርካሪዎች በዘፈቀደ የሚጓዙ ቢሆን ኖሮ ይደርስ የነበረው አደጋ ከፍተኛ ይሆን ነበር።

## 2. ተስከርካሪዎች ወደ ኢትዮጵያ መግባት የጀመሩት መቼ ነው?

ባለሞተር ተሽከርካሪ ወደ ኢትዮጵያ መግባት ከጀመረ ከአንድ መቶ አመት አይበልጥም። የመጀመሪያው የሞተር ተሽከርካሪ ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ የገባው የምድር ባቡር መሆኑ ይታወቃል። በ1904 ዓ.ም. ከጅቡቲ እስከ ድሬደዋ የተሰራው ሃዲድ በመጠናቀቁ ባቡር የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ጀመረ።

ከባቡር ቀጥሎ ወደ አገራችን የገባው ተሽከርካሪ ዳምጠው ተብሎ የሚጠራው የመንገድ መደምደሚያ ከባድ የብረት መሽከርከሪያዎች ያሉት ይህ መሳሪያ የገባው በ1906ዓ.ም ተርኪስ በሚባል የአርመን ተወላጅ አማካይነት ነው። ከድሬደዋ አዲስ አበባ ነድቶ የሚያመጣው ሰው ባለመኖሩ፣ በማወላለቅ ሶስት ሺህ ያህል ሰዎች በሸክም አዲስ አበባ ድረስ እንዳመጡት ይነገራል። በሸክም የመጣው መኪና ከተገጣጠመ በኋላ ለትንሽ ጊዜያት በውጭ ዜጐችና በአጼ ሚኒልክ ከተንቀሳቀሰ በኋላ በሞተር ማቀዝቀዣው ውስጥ ውሃ ባለመጨመሩ ሞተሩ ተበላሽቶ እንደቆመ ቀርቷል። ሰባራ ባቡር እየተባለ የሚጠራውም ቦታ ስሙን ያገኘው ይህ ዳምጠው ተበላሽቶ የቆመበት ቦታ ስለሆነ ነው።

ከዚያን ጊዜ በኋላ በተለያዩ ሰዎች በርካታ ተሽከርካሪዎች ወደ አገራችን ሊገቡ ችለዋል። መኪናዎች በዓይነትና በብዛት እየጨመሩ ሲመጡ እንቅስቃሴውን ሰርዓት ለማስያዝ አለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸው የመንገድ አጠቃቀም ደንቦችን አገራችን ተግባራዊ ማድረግ ጀምረች።

## 3. የመንገድ ላይ ምልክቶች ጠቀሜታ

የትራፊክ ምልክቶች አለም አቀፍ ይዘትና እውቅና ያላቸው አሽከርካሪውን የሚያስጠነቅቁ፣ የሚቆጣጠሩና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶች ናቸው። ጥቅማቸውም አሽከርካሪዎች የመንገዱን ሁኔታ በተመለከተ አስቀድመው እንዲያውቁትና እንዲጠነቀቁ በመከልከልና በማስገደድ የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ የሚያስችሉ የመቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ናቸው።
ምልክቶች አሽከርካሪዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ወይም ምን ማድረግ እንደሌለባቸው ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን በነዚህ ምልክቶች አማካኝነት የትራፊክ ደንቦችን በሚተላለፉ አሽከርካሪዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ያስችላሉ።

የመንገድ ላይ ምልክቶች እና ስርዓቶች ባይኖሩ ኑሮ እያንዳንዱ ሰው በፈለገው አቅጣጫ እና ሁኔታ በመንዳት የሚደርስው አደጋና መጨናነቅ አሁን ካለው ሁኔታ እጅግ የተበራከተ በሆነ ነበር።

## 4. የትራፊክ ምልክቶች ምን ያስገነዝቡናል?

የትራፊክ ምልክቶች የተለያዩ ዓይነት መግለጫዎችን ለአሽከርካሪዎች ይሰጣሉ። እነዚህ ምልክቶች፡-

1. የሚያስጠነቅቁ፣
2. የሚቆጣጠሩና
3. መረጃ የሚሰጡ

ተብለው የሚታወቁ ናቸው።

**የሚያስጠነቅቁ የመንገድ ዳር ምልክቶች፡-** ቅርጻቸው ሶስት ማእዘን የሆነ በቀስት፣ በስእልና በቁጥር በመሳል/በመጻፍ የመንገዱን የወደፊት ሁኔታ በማሳወቅ አሽከርካሪዎች እንዲጠነቀቁ የሚረዱ ናቸው።

**የሚቆጣጠሩ የመንገድ ዳር ምልክቶች፡-** ቅርጻቸው ክብ ሆኖ በውስጡ በክብ ወይም በቀስት በመሳል/በመጻፍ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱና ቅድሚያ የሚያሰጡ ምልክቶች ናቸው።

**መረጃ ሰጪ የመንገድ ዳር ምልክቶች፡-** ቅርጻቸው አራት ማእዘን ሆኖ ራሳቸው መረጃ ሰጪ ወይም አቅጣጫ አመልካች ምልክቶች ናቸው።

- ሶስት ማዕዘን ሆኖ ዳርዳሩ ቀይ የተቀባ ምልክት የአደጋ ማስጠንቀቂያ ምልክት ሆኖ ይተርጎማል። ለምሳሌ፡-



ስእል 35

ይህ የሚያመለክተው ሰዎች መንገድ እየሰሩ በመሆኑ አሽከርካሪዎች ተጠንቅቀው ማለፍ እንዳለባቸው ሲሆን ከዚህ በታች ያለው ምልክት ደግሞ የሚያስጠነቅቀው ተማሪዎች የሚተላለፉበት ስለሆነ ፍጥነትህን ቀንሰህ ተጠንቅቀህ አሽከርክር የሚል ሲሆን ይህም በቅርብ ርቀት ት/ቤት መኖሩን ያመለክታል።



ስእል 36


- ክብ ሆኖ ዙሪያዉ ቀይ የተቀባ ከሆነ የተከለከለ መንገድ መሆኑን ያመለክታል፡፡
  ለምሳሌ



ስእል 37

ከላይ የተሳለው ምልክት ለእግረኛ ማለፍ  የማይፈቀድ እና የተከለከለ መሆኑን ያመለክታል፡፡

- ክብ ሆኖ ሰማያዊ ውስጡ ከተቀባ የሚያስገድድ ምልክት ነው፡፡
  ለምሳሌ



ስእል 38

ይህን ምልክት ለእግረኞች ብቻ የተፈቀደ መንገድ መሆኑን አመልካች ሲሆን የታችኛው ደግሞ ለብስክሌት ብቻ መሄድ እንደሚቻል ያመለክታል፡፡



ስእል 39

- አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው እና ውስጡ አረንጓዴ የተቀባ ከሆነ ምን ነገር ልናገኝ እንደምንችል ጥቆማ የሚሰጠን ምልክት ነው ፡፡
  ለምሳሌ፡-ከታች የምናየው ምልክት ከፊት ለፊት የእግረኛ ማቋረጫ መኖሩን የሚያሳየን፡፡




ስእል 40

## 5. የመንገድ ላይ የቅብ ምልክቶች

ቋሚ ነገሮች ላይ ከሚሰቀሉ ምልክቶች በተጨማሪ መንገድ ላይ በነጭ ወይም በቢጫ ቀለም የተቀቡ የመንገድ ላይ የመስመር ምልክቶች አሉ፡፡

ባለፉት ክፍለ ትምህርቶች እንደተማርነው አግድም የመንገድ መሃል መስመሮች፣ (ዜብራ) ቅብ ምልክት ያለባቸው፣ ለእግረኞች ማቋረጫ የተፈቀደ እንደሆነ ተምረናል፡፡

በሁለት አቅጣጫ ለሚያገለግል መንገድ በአስፋልቱ መሃል የተቆራረጠ መስመር ያሉበት መንገድ የሚያመለክተው መንገዱ በረጂም ርቀት ግልጽ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ተከታትለው ከሚሽከረከሩ መኪናዎች ውስጥ አንዱ ከፊቱ ያለውን መኪና ለመቅደም ቢፈልግ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግና ከፊት ለፊት የሚመጣ መኪና አለኖሩን በመመልከት የተቆራርውን የመንገድ ላይ ቅብ በማቋረጥ መቅደም ወይም ወደ ግራ በመታጠፍ ዞሮ ወደመጣበት መመለስ እንደሚችል ያመለክታል፡፡



ስእል 41

መንገዱ አጋማሽ ላይ የተቆራረጠ መስመር

መሰመሩ ያልተቆራረጠ ከሆነ የሚያመለክተው መንገዱ በረጂም ርቀት ግልጽ አለመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ከፊቱ ያለውን መኪና ለመቅደም ወይም ዞሮ ወደመጣበት ለመመለስ መስመሩን ማቋረጥ እንደማይችል የሚገልጽ ነው፡፡ መቅደም የሚችለው የተቆራረጠ መስመር ላይ ሲደርስ ብቻ ነው፡፡ እስከዚያ መታገስ እንደሚገባው ማወቅ ይኖርበታል፡፡



ስእል 42

*መንገዱ አጋማሽ ላይ ሙሉ መስመር*

*ተማሪዎች! ሌሎች የመንገድ ላይ ምልክቶች ያሉ ሲሆን እነዚህን ምልክቶችና ጥቅማቸውን ወደፊት እስክትማሩ ድረስ ምንምን ዓይነት ሊሆኑ እንደሚችሉ ያውቃሉ ብላችሁ የምታስቧቸውን ሰዎች ጠይቁ፡፡*

***መሰራት ያለባቸው ተግባራት***

***ተግባር አንድ***

*ተለያዩ የመንገድ ላይ እና የትራፊክ ምልክቶችን ስላችሁ ለመምህራችሁ በማሳየት ትክክል መሆናችሁን ወይም አለመሆናችሁን አረጋግጡ፡፡*

***ተግባር ሁለት***


*ተማሪዎች! አደጋን ለመቀነስ ይረዳሉ የምትሏቸውን አዳዲስ የትራፊክ ምልክቶች ስላችሁ ለመምህራችሁ በማሳየት፣ ለምን ምልክቶቹን መሳል እንደፈለጋችሁ ግለፁ፡፡*

***ተግባር ሶስት***

- የተከለከለ
- ማስጠንቀቂያ
- መግለጫ

እነዚህን ቃላት በትክክለኛው ምልክት ስር ፃፉ፡፡







ስእል 43

ልታውቋቸው የሚገቡ ነገሮች

1. የማታውቁት የመንገድ ላይ ምልክት ወይም የትራፊክ ምልክት ሲያጋጥማችሁ መምህራኖቻችሁ ወይም የሚያውቁ ሌሎች ሰዎች እንዲነግሯችሁ መጠየቅ አለባችሁ፡፡
2. የመንገድ ላይ የትራፊክ ምልክቶች ተጓዦች ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲጓዙ የሚረዱ በመሆናቸው በእግራችሁ ወይም በብስክሌት በምትጓዙበት ጊዜ እነዚህን ምልክቶች ማክበር አለባችሁ፡፡ ይህን በማድረጋችሁ በናንተም ሆነ በሌሎችም ላይ አደጋ እንዳይደርስ አስተዋጽኦ አደረጋችሁ ማለት ነው፡፡

## 6. የመንገድ እና የትሪፊክ ምልክቶችን አክብሮ መጠቀም፡፡

አሽከርካሪዎች ማክበር የሚገባቸው በርካታ የትራፊክ ህጎች አሉ፡፡ እግረኞችም መፈፀም ያለባቸው ተግባሮች አሉ፡፡ በብዙ አገሮች የወጣውን የትራፊክ ህግ እንዲያከብሩ የሚገደዱት አሽከርካሪዎች ብቻ ሳይሆኑ እግረኞችም ጭምር ናቸው፡፡

የትራፊክ ህግን የሚጥሱ አሽከርካሪዎች በኛም አገር ተገቢው ቁጥጥር እና ክትትል እየተደረገ ለህግ የሚቀረቡበት ሁኔታ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ነገረ ገን እግረኞች ለሚፈጽሙት የትራፊክ ህግ መጣስ አስገዳጅ ደንብ ወይም የሚጣል ቅጣት እስካሁን ቅርብ ድረስ አልነበረም፡፡ አሁን ግን ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ህግ ወጥቷል፡፡ በዚህ ህግ መሰረት እግረኞችም ሊቀጡ ይችላሉ፡፡

ሌላውን ሰው ለአደጋ በማጋለጣችን እንዳንቀጣ ወይም ለአደጋ የተጋለጥን እንዳንሆን፣ የመንገድ ላይ እና የትራፊክ ምልክቶችን በሚገባ በማወቅ ተገቢውን አክብሮትና ጥንቃቄ በማድረግ እኛንም ሆነ ሌሎችን ከአደጋ መጠበቅ ይገባናል፡፡

ተግባር አንድ
ተገቢውን መልስ ስጡ

1. እግረኞች የትራፊክ ህግጋትን ማወቃቸው ምን ጥቅም ይሰጣቸዋል?
2. እግረኞች ህጉን ሲጥሱ ለምን እርምጃ አይወሰድባቸውም?
3. የመንገድ ምልክቶችን ያላከበረ እግረኛ መቀጣት ቢችል የትራፊክ አደጋ ይቀንስ ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ? ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡
4. አሽከርካሪዎች ማክበር ያለባቸው የትራፊክ ህጐች ምን ምን ዐይነት እንደሆኑ እየጠቀሳችሁ ተወያዩ
5. አደጋ እንዳይደርስብን ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ አለብን?

## 7. የመመልከት እና የማደመጥ ችሎታን ማዳበር

የሰው ልጅ ካሉት የተለያዩ የስሜት ህዋሳት ውስጥ ጆሮ እና አይን በመንገድ አጠቃቀም ወቅት የሚኖራቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመጡ ተሽከርካሪዎችን በድምፃቸው አዳምጦና በአይን አይቶ ለመለየት እነዚህ አካላት ያስችሉናል፡፡ ተገቢውን ጥንቃቄ ለማድረግ እነዚህ የስሜት ህዋሶቻችን የዳበሩ መሆን ይገባቸዋል፡፡

## 8. የህፃናት የማየት እና የመስማት ችሎታ የዳበረበት መጠን

ህጻናት እንደ አዋቂዎች ሁሉ ማየት የሚችሉ ቢሆንም ቁመታቸው አጭር በመሆኑ ሰፋ ባለ ሁኔታ አካባቢያቸውን ማየት አይችሉም፡፡ ህጻናት አካባቢያቸውን በሚያዩበት ጊዜ የሚመለከቱት

ፊትለፊታቸው ያለውንና ማየት የፈለጉትን ነገር ብቻ እንጂ ባሉበት አካባቢ የሚታዩ ነገሮችን ሁሉ አይደለም፡፡

አዋቂዎች በትንሽ ሰኮንድ ውስጥ አካባቢያቸውን በማየት ያሉትን ሁኔታዎች ፈጥነው ሊያገናዝቡ የሚችሉ ሲሆን ህጻናት ግን ተመሳሳይ እይታ አድርገው አካባቢያቸውን ለመገንዘብ ረዘም ያለ ጊዜ ይፈጅባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቆሙ ወይም የሚንቀሳቀሱ መኪናዎችን ለማየት፣ ፍጥነታቸውን ወይም የመኪናዎቹን መጠን ለመገንዘብ፣ ርቀታቸውን በአግባቡ ለመገመትአእምሯቸው ከአዋቂ እኩል የዳበረ አይደለም፡፡ የጭነት ወይም የቤት መኪና በእኩል ርቀትላይ ቢኖሩ የትኛው ፈጥኖ አጠገባቸው እንደሚደርስ የማመዛዘን ችሎታቸው አነስተኛ ነው፡፡

ጭጋጋማ በሆነ የአየር ሁኔታ ወይም በጨለማ ጊዜ እይታ ስለሚቀንስ ፊትለፊት ያለውን ነገር ማየት በመቻላቸው ብቻ እነሱም አሽከርካሪዎች ያዩናል የሚል ግምት ሊይዙ ይችላሉ፡፡ እነሱ ትልቅ ነገር ማየት ቢችሉም ቁመታቸው አጭር በመሆኑ ለሌላው ላንታይ እንችል ይሆናል ብለው አይገምቱም፡፡

የህጻናት የማዳመጥ ችሎታ ከአዋቂዎች የበለጠ እንደሆነ ሳይንስ ይነግረናል፡፡ ነገር ግን የሰሙት ድምጽ በየት አቅጣጫ እንደመጣ የመለየት ችሎታቸው አነስተኛ ነው፡፡ በተደረጉ ጥናቶች እንደተደረሰበት 40% ያህሉ ህጻናት ድምጹን ቢሰሙም የሰሙት ድምጽ ከፊት ይሁን ከኋላቸው መለየት አይችሉም፡፡ 80% ከነሱ ቀኝ ወይም ግራ አቅጣጫ፣ ከፊት ወይም ከኋላ እንደመጣ ለይተው ሊናገሩ አይችሉም፡፡

ድምጽ ወደሰሙበት አቅጣጫ አይናቸውን ቢያዞሩም በአካባቢያቸው ያለው ጫወታ ወይም ግርግር በትክክል ድምጹ ከየት አቅጣጫ እንደመጣ ለይተው እንዳያውቁ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ከበርካት አደናጋሪ ድምጾች ውስጥ አደጋ ሊያስከትልባቸው የሚችል መኪና መምጣቱን የሚጠቁመውን ድምጽ የመለየት አቅማቸው ዝቅተኛ ነው፡፡

በተገቢው ሁኔታ ድምጽን ሳይለዩ የሚደርስባቸው መኪና ቢኖር ምን ማድረግ እንዳለባቸው ፈጥነው በማመዛዘን የመወሰን ችሎታቸው አነስተኛ ስለሆነ በሚያደርጉት መደናበር አደጋ ላይ የሚጥላቸውን ድርጊት ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡

## 9. ህፃናት የማየት እና የመስማት ችሎታቸውን ለማዳበር ማድረግ ያለባቸው ነገሮች

ፊት ለፊት ካለው ሁኔታ (ነገር) ራቅ አድርገው የማየት ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያስችል ልምምድ ማድረግ አለባቸው፡፡

ከፊት ለፊታቸው ወይም በየትኛውም አቅጣጫ በመምጣት ላይ ያለ ተሽከርካሪ፣ አሽከርካሪ እንደተመለከታቸው እርግጠኛ ከመሆናቸው በፊተ መንገድ ለማቋረጥ ወይም ለመንቀሳቀስ መሞከር የለባቸውም፡፡

መንገድ ከማቋረጣቸው በፊት፣ ማለትም መንገዱ በሁለት አቅጣጫ የሚያገለግል ከሆነ፣ ቀድመው ወደ ግራ አቅጣጫ ያለውን መንገድ በመመልከት ወዲያውኑ የቀኙን አቀጣጫ ማየት፡፡ ከዚያ የግራ አቀጣጫውን በድጋሚ በመመልከት መኪና አለመኖሩን ወይም ከማቋረጣቸው በፊት ሊደርስባቸው እንደማይችል አረጋግጠው ማቀረጥ አለባቸው፡፡

የመኪና ድምፅ ሲሰሙ ድምጹ ከምን ያህል ርቀት እንደተሰማ በተደጋጋሚ በሚደረግ ልምምድ ለመገመት መጣር ይኖርባቸዋል፡፡ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮች ያላቸው ድምፅ ምን ምን ዓይነት እንደሆነ ማወቁ ጥንቃቄ ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ስላለው ተገቢውን ልምምድ ማድረግ ጥቅሙ ከፍተኛ ነው፡፡

**ይህን ታውቁ ነበር?**

- በአህጉራችን ከፍተኛው የሰው ጉዳት የሚያስከትለው የመኪና አደጋ ዓይነት የእግረኞች ግጭት ነው፡፡
- የቆሙ መኪናዎችን ተከልሎ ለማቋረጥ የሚደርግ ሙከራ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡

**መከናወን ያለባቸው ተግባራት**
**ተግባር አንድ**

በመካከላችሁ ከተቀመጡት ተማሪዎች የአንዱን ዓይን እንዳያይ በጨርቅ ማሰር፡፡ ከዚያ ተማሪዎች ቦታቸውን እንዲለዋወጡ ማድረግ፡፡ ከኋላ በኩል የተቀመጡት ተማሪዎች የማጉተምተም ድምፅ እያሰሙ ባሉበት ወቅት አንድ ተማሪ የታሰረውን ልጅ ስም እንዲጣራ በማድረግ የታሰረው ተማሪ የተጣራውን ድምጽ ከፊቱ ወይም ከኋላው በኩል እንደሰማ እንዲናገር በማድረግ የድምፁን አቅጣጫ በትክክል መጠቆም እንደቻለ ማየት፡፡ ይህን ድርጊት ሌሎቹም ተማሪዎች ደጋግመው እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

**ተግባር ሁለት**

- የመኪና መንገድ ወይም አውራ ጐዳና ላይ የሚታዩ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በዝርዝር ተናገሩ፡፡
- በጨለማ ጊዜ (በምሽት ጊዜ) መኪና መንገድ ላይ በቀላሉ ተለይተው ሊታዩ የሚችሉ እና የማይችሉ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በዝርዝር ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩቸው፡፡

**ተግባር ሶስት**

እጃችሁን ወደ ጐን በመዘርጋት ቀጥ ብላችሁ ቁሙ፡፡ አውራ ጣታችሁን በማንቀሳቀስ ፊታችሁን ሳታዞሩ፣ የአውራ ጣታችሁን እንቅስቃሴ ማየት ትችሉ እንደሆነ እና እንዳልሆነ ደጋግማችሁ ሞክሩ፡፡ አውራ ጣታችሁን በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሆናችሁ ማየት አትችሉም፡፡ እይታችሁን ፊት ለፊት ብቻ ካደረጋችሁ ማየት የምትችሉት ከፊት ለፊት ያሉ ነገሮችን እንጂ ከጐን ያሉ ነገሮችን አይደለም፡፡ በጐን በኩል ያሉ ነገሮችን ማየት ስትፈልጉ የግድ የእይታ አቅጣጫችሁን ማዞር ይገባችኋል፡፡ ስለዚህ የመኪና መንገድ ለማቋ ረጥ ፊት ለፊት ብቻ መመልከቱ የተሟላ የጥንቃቄ ዘዴ አለመሆኑን በመረዳት ለማቋረጥ ከመሞከራችሁ በፊት ዞር ዞር በላችሁ መመልከት ይገባችኋል፡፡

**ተግባር አራት**

በመኪና መንገድ ላይ ከሚንቀሳቀሱና አደጋ ሊያደርሱ ከሚችሉ ተሽከርካሪዎች ውስጥ በጐላ መልኩ ድምፃቸው የማይሰማው የየትኞቹ መሆኑን ግለጹ፡፡

ድምፃቸው ከማያሰሙ ነገሮች አንዱ በኤሌክትሪክ ሀይል የሚሰራ መኪና ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአገራችን የሌለ ቢሆንም፣ በሌሎች ያደጉ አገሮች እንደዚህ ዓይነት ተሽከርካሪዎች ለትሪንስፖርት አገልግሎት ውለዋል፡፡ እኛም የዚህ አገልግሎት ተካፋይ ስንሆን ሊደርስ የሚችለውን አደጋ ለመቀነስ ከወዲሁ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል፡፡



ስዕል 44
የትኛው ተሽከርካሪ በቀርብ ርቀት ላይ ነው?

ሞተር ብስክሌት፣ የቤት መኪና እና አውቶቡስ እየሄዱ ሶስቱም ተሽከርካሪዎች በእኩል ርቀት ላይ ያሉ ሆነው ብናይ አውቶቡሱ ጐላ ብሎ ስለሚታይ በቅርብ ርቀት ላይ ያለ ሊመስለን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ለእይታችን ሰፊ ቦታ ስላለው መሆኑን መገንዘብ ይኖርባችኋል፡፡ እርግጠኛ ለመሆን የመንገዱን ማካፈያ ነጭ መስመር በመቁጠር ሁኔታውን ማረጋገጥ ትችላላችሁ፡፡

የመኪና መንገድ ለማቋረጥ ተዘጋጅታችኋል እንበል፡፡ ከፊት ለፊት የሚመጣው መኪና 25 ሜትር በሰኮንድ ይበራል (ይሄዳል)፣ ከማቋረጣችሁ በፊት የመንገዱን ግራና ቀኝ በድጋሚ ግራን ለማየት ስድስት ሰኮንዶች ይፈጃል፡፡ እንግዲህ ግራ ቀኝ ግራ ለማየት በምንወስደው ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪው 6X25=150ሜትር ይጓዛል ማለት ነው፡፡




ስዕል 45
መኪና በምን ያህል ርቀት እንዳለ ስእሉን ተመልክታችሁ ገምቱ

አንድ መኪና 250 ሜትር ርቀት ላይ ቢደርስ፣ መንገዱን ለማቋረጥ 3 ሴኮንድ ቢወስድ፡፡
1. መንገዱን ሙሉ በሙሉ ለማቋረጥ ከእይታው ጋር ስንት ሰኮንድ ይወስድባችኋል?
2. እናንተ መንገዱን አቋርጣችሁ ስትጨርሱ መኪናው ስንት ሜትር ሊጓዝ ይችላል?
3. በዚህ ሁኔታ መንገዱን አቋርጣችሁ ለማለፍ በቂ ጊዜ ይኖራችኋል እንዴት?

ከላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች በሚከተለው መልክ መልሱን ከሰጣችሁ ትክክል ናችሁ፡፡
1. መንገዱን አይቶ ለማቋረጥ የሚፈጀው 3+6= 9 ሰኮንድ ነው፡፡
2. መንገዱን አቋርጣችሁ ስትጨርሱ መኪናው ከናንተ 25 ሜትር ርቀት ላይ ይደርሳል፤ ይህም በሰኮንድ 25 ሜትር ከተጓዘ በዘጠኝ ሰኮንድ (25X9)=225 ሜትር ይጓዛል ማለት ነው፡፡ እናንተ ያላችሁበት ቦታ ለመድረስ የአንድ ሰኮንድ ጊዜ ብቻ ይቀረዋል፡፡
3. ከላይ ባየነው ሁኔታ መንገዱን ለማቋረጥ የሚያስችለን ጊዜ ያለ ቢመስለንም የናንተን የማቋርጥ ጉዞ የሚያደናቅፉ መሰናክሎች ሊገጥማችሁ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል፣ መኪናው እናንተጋ በአንድ ሰኮንድ ሊደርስ መቻሉ አደገኛ ሁኔታ ውስጥ እንድትገቡ ሊያደርጋችሁ ይችላል፡፡

ስለዚህ ከማቋረጣችሁ በፊት እየመጣ ያለውን መኪና ርቀቱን በትክክል በመገመት መንገዱን ለማቋረጥ የሚያስችለን በቂ ጊዜ መኖርን መገንዘቡ ከአደጋ ሊጠብቀን ይችላል፡፡

<u>የመልመጃው የተግባር ጥቅም</u>

መንገድ በምናቋርጥባቸው ሰኮንዶች መኪናው እየተቃረበን እንደሚመጣ እንገነዘባለን፡፡ የሰው እና የመኪና ፍጥነት አንድ ዓይነት ባለመሆኑ በአንድ ሰኮንድ ጊዜ ውስጥ መኪናው ሊደረስ መቻሉ አደጋ ሊያስከትል የሚችልበት ሁኔታ እንዲፈጠር ሊያደርግ ይችላል፤ ስለዚህ የተሽከርካሪ ርቀትን በማየትና በመገመት የምናደርገው እንቅስቃሴ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

ተማሪዎች! ለዚህ መዝሙር የሚሆን ዜማ መምህራችሁ እንዲያወጡላችሁ ጠይቋቸውና በዜማው መሠረት ዘምሩ

<u>ቆርጠን ተነስተናል</u>

ተጠበቅ ከአደጋ.................... ህይወት አለው ዋጋ
መንገድ ስታቋርጥ................. ተጠቀም ምልክት
መንገድ ላይ ስትጓዝ ............. ግራህን ነው መያዝ
አስበህ ተራመድ .................... ስትጓዝ በመንገድ
ህይወት ህይወት ህይወት ....... ህይወት አለው ዋጋ
ፍፁም ቸል አትበል ................ አስበህ ተቀበል
መምህር ሚነግሩህን ............. ማዳመጥ ነው ሁሉን
መብራቱን ተመልከት ...............መንገድ ስታቋርጥ
መንገድ ላይ መጫወት ..............ህይወት ማበላሸት
መሆኑን አውቀናል ...................ከእንግዲህ አስበናል
ህይወትን ለማትረፍ ................. ቆረጠን ተነስተናል፡፡

## <u>10. ብቻችሁን መንገድ ስታቋርጡ ማወቅ የሚገባችሁ</u>

ስፋ እና ረዘም ባለ መንገድ ከማቋረጥ ይልቅ ጠባብ በሆኑ የመንገድ ጎኖች መሻገሩ ተመራጭ ነው፡፡ ነገር ግን ማቋረጫው አጭር በመሆኑ ብቻ ምን ያህል ለአደጋ የተጋለጠ መሆን አለመሆኑን ሳናረጋግጥ ከማቋርጥ ይልቅ ግራና ቀኛችንን በተማርነው መስረት መመልከት ይኖርብናል፡፡ በቅርብ ርቀት የሚታይ መኪና ካለ መንገዱን ከማቀረጣችን በፊት ሊደርስብን

ስለሚችል መኪናው እስከሚያልፍ ድረስ በመታገስና በድጋሚ መንገዱ ከመኪና አደጋ የተጠበቀ መሆኑን መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡

የምታቋርጡት መንገድ ከዚህ በፊት የማታውቁትና ለእናንተ አዲስ ከሆነ በድፍረት ገብታችሁ አደጋ እንዳይደርስባችሁ ትልቅ ሰው እንዲያሻግራችሁ ትብብር መጠየቅ ይኖርባችኋል፡፡ ምክንያቱም በዚያ መንገድ መኪናዎች በምን ያህል ፍጥነትና ሁኔታ እንደሚመላለሱ ስለማታውቁ አደጋ ላይ ልትወድቁ ትችላላችሁ፡፡ መንገድ በምታቋርጡበት ጊዜ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋወች ምን ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ቀድማችሁ በማወቅ ከእነዚህ አደጋዎች ራሳችሁን እንዴት መጠበቅ እንደምትችሉ መገንዘብ ይኖርባችኋል፡፡

ከቤት ወደ ት/ቤት የሚያደርሳችሁን መንገድ ወይም አዘውተራችሁ የምትጓዙበትን መንገድ ሊያሳይ የሚችል ካርታ በመምህራኖቻችሁ ወይም በወላጆቻችሁ አስርታችሁ አጠቃቀሙን ጭምር ቀድማችሁ ማወቁ የመንገድ አጠቃቀም ችሎታችሁን ሊያዳብር ይችላል፡፡

ግራችሁ ወይም ቀኛችሁ በየት በኩል እንደሆነ ማወቅ የሚጠቅማችሁ ሲሆን፣ የሌሎች ሰዎች ቀኝ ወይም ግራ የትኛው እንደሆነ ማወቁ ይበልጥ የግንዛቤ እውቀታችሁንን ያስፋል፡፡

መንገድ በምታቋርጡበት ጊዜ በፍጥነት ሩጫ ላቋርጥ እችላለሁ በሚል ሀሳብ የሚደረግ ሙከራ ራስን ለአደጋ ስለሚያጋልጥ በጥንቃቄና በፍጥነት በመራመድ ማቋረጡ የሚመረጥ ይሆናል፡፡

ጥድፊያ ውስጥ ሆናችሁ መንገድ የምታቋርጡ ከሆነ ራሳችሁን ለአደጋ እንደምታጋልጡ ማወቅ አለባችሁ፡፡ ከት/ቤት መልስ ስለሚርባችሁ ወይም የተሰጣችሁን የቤት ስራ እንዴት እና መቼ መስራት እንዳለባችሁ ስለምታስቡ ወይም ስለሚደክማችሁ አልያም ከጓደኞቻችሁ ጋር ስለምታደርጉት ጫወታ ስለምታስላስሉ የምታቋርጡት መንገድ ምን ያህል የመኪና አደጋ የሚያስከትል እንደሆነ እንዳታስቡ ሊያደርጋችሁ ይችላል፡፡ ስለዚህ መንገድ በምታቋርጡበት ጊዜ ሙሉ ትኩረታችሁን ማድረግ ያለባችሁ በምታቋርጡት መንገድ ላይ ብቻ መሆን ይገባዋል፡፡

ያስባችኋቸውን ነገሮች ሁሉ የምታሳኩት ራሳችሁን ከአደጋ ጠብቃችሁ ስትገኙ በመሆኑ፣ መንገድ ላይ በምትጓዙበት ወይም የመኪና መንገድ በምታቋርጡበት ጊዜ ከላይ ከተዘረዘሩትና ከሌሎችም ትኩረታችሁን ከሚጋሩ ሀሳቦች ራሳችሁን አርቃችሁ ሙሉ ጥንቃቄያችሁን በመንገዱ እና በጉዞአችሁ ላይ ብቻ ማድረግ ይኖርባችኋል፡፡

<u>የክንውን ተግባራት</u>

- ማንም ሳያግዛችሁ ወይም እንዲህ አድርጉ ሳትባሉ ከምትሰሯቸው ተግባራት ውስጥ የተወሰኑትን ዘርዝሩ፡፡ (ለምሳሌ የቤት ስራ እንደመስራት፣ ወንበር ላይ እንደመቀመጥ፣ የመሳሰሉ ነገሮችን)

  ____________________________________

  ____________________________________

  ____________________________________

  ____________________________________

- ብቻችሁን ያደረጋችሁት የመንገድ ላይ ጉዞ አለ? ዕድሜያችሁ ስንት ሲሆን ነበር ብቻችሁን መጓዝ/መንገድ ማቋረጥ የጀመራችሁት? እንዴት ባለሁኔታ እንዳቋረጣችሁ ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡ ብቻየን መሄድ እችላለሁ ብላችሁ ነው ወይስ ወላጆቻችሁ ብቻችሁን መጓዝ ትችላላችሁ ስላሉአችሁ ነው ብቻችሁን መጓዝ የጀመራችሁት?
- አሁን ካላችሁበት ቦታ (ከክፍላችሁ ውስጥ ሆናችሁ) የት/ቤታችሁ ግቢ መግቢያ በር የሚገኘው ከናንተ ቀኝ በኩል ቢሆን፣ ፊቱን ወደ እናንተ አዙሮ ከቆመው ጓደኛችሁ አንፃር በሩ በየት አቅጣጫ ይገኛል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

- ወደ ት/ቤት የምትሄዱበትን መንገድ፣ የምታቋርጡት የመኪና መንገድ ወይም በዙሪያችሁ ያሉትን መንገዶች በዓይናችሁ ብቻ ካያችሁ በኋላ ት/ቤት ስትደርሱ የመንገዶቹን አቅጣጫ እና አቀማመጥ የሚያመለክት ካርታ ስርታችሁ ለመምህራችሁ ወይም ለጓደኞቻችሁ አሳዩአቸው፡፡
- ከጓደኞቻችሁ ጋር ሳትኮራረጁ የስፈራችሁን ካርታ ለየብቻ ከሰራችሁ በኋላ ተራ በተራ እያሳያችሁ ትክክል ወይም ስህተት ስለሆነው ነገር ተወያዩበት፡፡

<u>ተግባር አንድ</u>
<u>ትክክል የሆነውን ሀሳብ እውነት፣ ትክክል ያልሆነውን ሀሳብ ስህተት በሉ፡፡</u>

1. የመኪና ማቋረጫ መንገዱን ብዙ ጊዜ ስለተመላለስንበት እና ስለምናውቀው በምናቋርጥበት ጊዜ ጥንቃቄ ባናደርግም ምንም ችግር ሊገጥመን አይችልም፡፡
2. ከወላጆቻችን ወይም ከታላላቆቻችን ጋር መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ ትኩረት ባናደርግም እንኳን ፈጽሞ አደጋ ሊደርስብን አይችልም፡፡
3. ት/ቤት የመግቢያ ሰዓት ቢረፍድብን እንኳን የመኪና መንገድ ስናቋርጥ በሩጫ ማቋረጡ ለአደጋ ሊያጋልጠን ይችላል፡፡
4. የመኪና መንገድ ስናቋርጥ ከጓደኞቻችን ጋር እየተቃለድን መጓዙ ለአደጋ ሊያጋልጠን የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡
5. ለመጀመሪያ ጊዜ የምናቋርጠውን የመኪና መንገድ ደጋግመን እስክንለምደው ድረስ ትላልቅ ሰዎች ቢያሻግሩን ተመራጭነት ይኖረዋል፡፡

ልጆች! ከላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች ስህተት የሚል መልስ ከሰጣችሁ ለምን ስህተት እንዳላችሁ ግለፁ፡፡

<u>መከተል የሚገባችሁ የትኩረት ነጥቦች</u>
- ብቻችሁን በምትሆኑበት ጊዜ ለራሳችሁ ዋነኛውን ጥንቃቄ ማድረግ ያለባችሁ እናንተው መሆናችሁን አውቃችሁ፤ ራሳችሁን ከአደጋ ለመጠበቅ ሞክሩ
- ትኩረት የምታደርጉ እና መንገድ ስታቋርጡ ጥንቃቄ የምታደርጉ መሆናችሁን ወላጆቻችሁ ማወቃቸው ብቻችሁን የተለያዩ ነገሮችን የማድረግ ችሎታ እንዳላችሁ ስለሚገነዘቡ ተጨማሪ ሀላፊነት እንዲሰጧችሁ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ስለዚህ ወላጆቻችሁ ብቃታችሁን እንዲያረጋግጡላችሁ ሁል ጊዜ መንገድ ስታቋርጡ ጠንቃቃ መሆን ይገባችኃል፡፡
- ሰፋ ያለ የመንገድ ማቋረጫ ብቻችሁን ለማቋረጥ ከመሞከራችሁ በፊት ጠባብ እና አደጋ የማይኖርባቸውን መንገዶች መርጦ ለማቋረጥ በመሞከር የመንገድ አጠቃቀም ልምዳችሁን ማዳበሩ ይበልጥ ተመራጭ ነው፡፡
- አደጋ በተደጋጋሚ የሚደርስባቸውን እና የማይደርስባቸውን ቦታወች ከወላጆቻችሁ ጋር ተነጋግራችሁ በመለየት መንቀሳቀሱ የምታደርጉትን ጥንቃቄ ይበልጥ እንድታጠናክሩ ያግዛችኋል፡፡ በመሆኑም መላጆቻችሁ ወይም መምህራኖቻችሁ እንዲረዷችሁ በመጠየቅ አደጋ የሚበዙባቸውን መንገዶች ለይታችሁ ለማወቅ በመሞከር ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

## <u>11. አውራ ጐዳናዎችና መጋቢ መንገዶች ያላቸው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ</u>

መንገድ የሰዎችን የኑሮ ጫና ለማቃለል የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ ሰዎች እርስ በርስ ለሚያደርጉት ግኙኝነት በተፋጠነ እና አድካሚ ባልሆነ ሁኔታ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመንቀሳቀስ የሚያስችሉትን ነገሮች መጠቀም የሚችሉት በመንገዶች አማካኝነት ነው፡፡

ሰዎች እራሳቸው ያመረቱትን ምርት ብቻ እየተጠቀሙ የሚኖሩ አይደለም፡፡ አንድ አካባቢ የተመረተ ምርት ሌላ አካባቢ ላይመረት ይችላል፡፡ አንድ አገር የሚሰራው የፋብሪካ ምርት ሌላ አገር ላይሰራ ይችላል፡፡ በመሆኑም ሰዎች ያመረቱትን ምርት ሊለዋወጡ፣ ማለትም ሊገበያዩ፣

የሚችሉት መንገዶችን በመጠቀም በሚንቀሳቀሱ እንደ መኪና እና የጋማ ከብቶች (በቅሎ፣ ፈረስ፣ አህያ) አማካኝነት ነው፡፡ የአገራችን ዋና ከተማ ከሆነችው ከአዲስ አበባ የሚነሱ አምስት ዋና አውራ ጐዳናዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም፡-

1ኛ. ከአዲስ አበባ- ደብረብርሃን-ደሴ-መቀሌ
2ኛ. ከአዲስ አበባ-ሞጆ-ሀረር-ጂጂጋ፤ ሞጆ-ሞያሌ እና ሞጆ - አዋሽ - ጂቡቲ
3ኛ. ከአዲስ አበባ-ደብረማርቆስ-ባህርዳር-ጐንደር
4ኛ. ከአዲስ አበባ-ጂማ-ጋምቤላ
5ኛ. ከአዲስ አበባ-አምቦ-ለቀምት-አሶሳ የሚያደርሱ አውራ ጐዳናዎች ናቸው

እነዚህ አምስት አውራ ጐዳናዎች እስከ ድንበር በመዘርጋት ክልሎችን በማገናኘትና ወደ ወደቦችም በመድረስ ለአገራችን በዋናነት የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር የሚረዱ ናቸው፡፡ ከአገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች ተነስተው ከነዚህ ዋና መንገዶች ጋር የሚያገናኙ በጠጠር ወይም በጥርጊያ የተሠሩ በርካታ ኪሎ ሜትር ርዝማኔ ያላቸው መጋቢ መንገዶች አሉ፡፡

እጅግ ሩቅ ነው ከሚባለው የአገራችን ክፍል የተመረቱ የግብርና ውጤቶች ለምሳሌ ቡና፣ የቅባት እህሎች፣ ቆዳና ሌጦ የመሳሰሉት ምርቶች በጋማ ከብቶች አማካኝነት ተጓጉዘው መኪና የሚደርስባቸው ከተሞች ከደረሱ በኋላ በመኪና ተጭነው ወደሚፈለጉበት ቦታ ይደርሳሉ፡፡ ትናንሽ የጭነት መኪናዎች በጥርጊያ መንገድም መሄድ ስለሚችሉ ወደ ገበሬው አካባቢ ቀረብ ብለው በጋማ ከብቶች የተጓዘውን ተቀብለው በመጫን አውራ ጐዳናዎች አካባቢ ያደርሳሉ፡፡ ከዚያም በትላልቅ መኪናዎች ተጭነው ወደብ ይደርሱና ከዚያም በትላልቅ መርከቦች ተጭነው ወደ ሌላ አገር በመውሰድ ለሽያጭ ይቀርባሉ፡፡ ውጭ አገር የተመረቱ የፋብሪካ ውጤቶችም እስከ አገሪቱ ጫፍ ድረስ ሊደርሱ የሚችሉት በአውራ ጐዳናዎች እና በመጋቢ መንገዶች ተጓጉዘው ነው፡፡

በርትተው የሰሩ ሰዎች ያመረቱትን ሸጠው፣ የፈለጉትን ገዝተው፣ የተሻለ የኢኮኖሚ ገቢ ማዳበር የሚችሉት በመንገድ ትራንስፖርት ስለሆነ የመንገዶች ግንባታ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑ የታመነበት ነው፡፡

<u>ተግባር አንድ</u>
<u>ተገቢውን መልስ ለነዚህ ጥያቄዎች ስጡ፡፡</u>

1. የመንገዶች መኖር ለአንድ አገር ህዝብ ምን ዓይነት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች አሉት ብላችሁ ታስባላችሁ?
2. ከአዲስ አበባ የሚነሱ ስንት ዋና መንገዶች አሉ? ወደ የት ወደ የት አቅጣጫ የተዘረጉ ናቸው፡፡
3. የመጋቢ መንገድ እና የአውራ ጐዳና ተያያዥነት ምንድነው?
4. ሰዎች እራሳቸው ባመረቱት ምርት ብቻ እንዴት መኖር አይችሉም?
5. ከገጠር የተመረተ ቡና እንዴት አድርጐ ተጓጉዞ ለውጭ ገቢያ ይደርሳል?

## <u>12. ቱሪዝምና መንገድ</u>

የመንገዶች ተስፋፍቶ መስራት ለአገራዊ ኢኮኖሚ እድገት የሚኖረው ጥቅም ብዙ ነው፡፡ የአንድ አገር ኢኬኖሚ የሚያድገው ህዝቦች ከሚያመርቷቸው ምርቶች በሚያገኙት ገቢ ብቻ ሳይሆን ታሪካዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርሳቸውን የሌላ አገር ዜጐች እንዲጐበኙላቸው የሚያስችል ሁኔታ በማመቻቸት ከሚያገኙት ገቢ ጭምር ነው፡፡

የሌላ አገርን ታሪካዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርስ ለመጐብኘት ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር የሚሄዱ ሰዎች ቱሪስቶች ተብለው ይጠራሉ፡፡ እንቅስቃሴው ቱሪዝም ይባላል፡፡ ቱሪዝም "ጭስ አልባ

ኢንድስትሪ" ተብሎ ይጠራል፡፡ ፍብሪካ ሳይኖር ነገር ግን የፍብሪካ ውጤቶች ተሸጠው ሊያገኙ የሚችለውን ገንዘብ ያለፍብሪካ ምርት ልናገኝ የምንችልበት መንገድ በመሆኑ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በሌሎች አገሮች የሌሉ ጥንታዊ ቅሪቶች፣ የዱር እንስሳትና አራዊቶች፣ አዕወፋትና ታሪካዊ ቅርሶች ያሏት ሃገር ስትሆን ከታሪካዊ ቅርሶቿም ውስጥ የጎንደር ቤተ መንግስት፣ የአክሱም ሀውልት፣ የላሊበላ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያንና የሃረር ከተማ ይገኙበታል፡፡ ልምላሜዋና የጂኦግራፊ ገጽታዋም የቱሪስቶችን ዓይን የሚማርኩ ነገሮች ናቸው፡፡ ስለዚህም ነው መንገድ ለቱሪዝም ዕድገትና ለአንድ አገር አጠቅላይ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ተብሎ የሚጠቀሰው፡፡

## 13. መንገዶች የሚሠሩባቸው ቁሳቁሶች

መንገዶች የተለያየ የአሠራር ደረጃ አላቸው፡፡ የአገራችን መንገዶች አብዛኛዎቹ ጥርጊያ መንገዶች ናቸው፡፡ በበጋ ወራት መኪናዎችን ሊያስተላልፉ በሚያስችል መልኩ የሚሠሩ ጠጠር ያልተነጠፈባቸው መንገዶች ጥርጊያ መንገድ ይባላሉ፡፡ ጥርጊያ መንገዶች በክረምት ወራት ጭቃማ ስለሚሆኑ ለመኪና መተላለፍያነት የሚሰጡት አገልግሎት በደረቁ ወራት የተወሰነ ነው፡፡

በበጋም ሆነ በክረምት መኪና እንዲተላለፍ የሚያስችሉት ጠጠር የተነጠፈባቸው መንገዶች በአገራችን በበዛት አሉ፡፡ በጠጠር ንጣፍነት የተሠሩ መንገዶች በብዙ የአገራችን ክፍል ተዘርግተዋል፡፡ ይህ ዓይነት መንገድ የጠጠር መንገድ ተብሎ ይጠራል፡፡ የጠጠር መንገዶች አቧራማ ከመሆናቸው በተጨማሪ በቂ ምቾት የሚሰጡ አይደሉም፡፡

በክረምትም ሆነ በበጋ ምቾት ባለው ሁኔታ መክናዎች እንዲጓዙ ተብሎ የተሠሩ መንገዶች አሉ፡፡ እነዚህ መንገዶች ሲሰሩ ከስር መሬቱ ተደልድሎ ምርጥ አፈርና ጠጠር በትክክል እንዲደለደል ይደረጋል፡፡ ከጠጠሩ ላይ ከነዳጅ ዘይት ተረፈ ውጤት የሆነው "ሬንጅ" የሚባል ነገር እየቀለጠ ከትናንሽ ጠጠሮች ጋር እየተደባለቀ በመንገዱ ላይ በማፍሰስ ይሰራል፡፡ በዚህ ዘዴ የሚሠራው መንገድ የአስፋልት መንገድ ተብሎ ይጠራል፡፡ የአስፋልት መንገድ ለመስራት ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቅ ነው፡፡

በአንዳንድ ከተሞች ውስጥ ወደ መንደር የሚያስገቡ የውስጥለውስጥ መንገዶች አሉ፡፡ የሚሠሩትም በድንጋይ ነው፡፡ ትላልቅ ድንጋዮችን በማስተካከል እና በትክክል በመደርደር የሚሰራው መንገድ የድንጋይ ንጣፍ መንገድ ተብሎ ይጠራል፡፡

**ተግባር አንድ**

**ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

1. በናንተ አካባቢ ያለው የመኪና መንገድ ከምን የተሠራ ነው?
2. በአካባቢያችሁ የአስፋልት መንገድ ለመስራት ያልተቻለው ለምን ይመስላችኋል?
3. ቱሪዝምና መንገዶች ያላቸው ተያያዥነት ምንድነው?
4. የመንገዶች መሰራት ለአንድ አገር ኢኮኖሚ ምን ጠቀሜታ ይሰጣል?
5. ቱሪስቶች ከአገራቸው ወደ ሌላ አገር የሚሄድት ምን ለማየት ሲሉ ነው?

## 14. የመንገድ ጠቀሜታ

መንገዶች እንስሳትና መኪናዎች ያለ ችግር እንዲመላለሱባቸው ታስቦ የሚሠሩት በሰዎችና በመሳሪያዎች አማካኝነት ነው፡፡ አመቺ የትራንስፖርት አግልግሎቶችን ለማግኘት የሰው ልጆች የተለያዩ የመንገድ ዓይነቶችን በመስራት ራሳቸውንም ሆነ ያመረቱትን ምርት በመኪና እና በጋማ ከብት በመጫን ወደ ገበያ ያደርሳሉ፡፡

ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የመንገድ መኖር የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ ነው፡፡ በእግር ስንጓዝ ረጅም ጊዜ የሚፈጅብንን የተለያዩ የትራንስፖርት አገለግሎቶችን በመጠቀም ማቅለል የምንችለው መንገዶች ሲኖሩ ነው፡፡

በአንድ አባከባቢ የተመረቱ ምርቶች ወደ ሌላ አካባቢ በቀላሉ ሊደርሱ የሚችሉት መንገድ ሲኖር በመሆኑ የመንገዶች መስፋፋት ህዝቦች እርስ በርስ ለሚያደርጉት ግንኙነት ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡ በፋብሪካዎች የሚመረቱ ምርቶች ወደ ገጠሩ ክፍል የሚደርሱት፣ በገጠሩም የሚመረቱ የእርሻ ውጤቶች ወደ ከተማው ተጠቃሚ የሚደርሱት መንገዶች በመኖራቸው ነው ፡፡

ሰዎች ያመረቱትን ምርት በመሸጥ የሚጠቀሙበትን የተለያዩ ነገሮች በመግዛት ፍላጐታቸውን ማሟላት ይችላሉ፡፡ ምርቶቻቸውን ሸጠው በሚያገኙት ገንዘብም ኑሮአቸውን ያሻሽሉበታል፡፡ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ሊፈፀሙ የሚችሉት መንገድ ሲኖር በመሆኑ የመንገዶች መኖር ለሰው ልጆች ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያስገኝላቸዋል፡፡

<u>ተግባር አንድ</u>
<u>ቀደም ብላችሁ የተማራችሁትን መሰረት በማድረግ እንዚህን ጥያቄዎች መልሱ፡፡</u>

1. መንገዶች የተለያዩ የአሰራር ደረጃዎች አሏቸው፡፡ የተወሰኑትን ጥቀሱ?
2. የአስፋልትና የጠጠር መንገድ ልዩነታቸው ምንድነው?
3. መንገዶች ህዝቦችን እንዴት ያቀራርባሉ?
4. ምርት ማምረት ከመንገድ መኖር ጋር ምን ተያያዥነት አለው?
5. የመኪና መንገድ መኖሩ ለሰው ልጆች ምን ጠቀሜታ አለው?

## <u>15. የትራንስፖርት ዓይነቶች</u>

ሰዎች ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ለመሄድ ወይም የተለያዩ ምርቶችን ለማጓጓዝ የተለያዩ የትራንስፖርት ዓይነቶችን ይጠቀማሉ፡፡ ትራንስፖርት በዋናነት በሶስት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል፡፡ እነሱም የየብስ ትራንስፖርት አገልግሎት፣ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎትና የውሃ ላይ ትራንስፖርት አገልግሎት ናቸው፡፡

### <u>1. የየብስ ትራንስፖርት አገልግሎት</u>

የየብስ ትራንስፖርት የሚባለው በመሬት ላይ በተሰሩ መንገዶች አማካይነት በመጠቀም ለሰውና ለእቃ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ነው፡፡ መካከለኛ እና ከፍተኛ አውቶብሶች፣ ትናንሽ እና ትላልቅ የጭነት መኪናዎች፣ የቤት መኪናዎች፣ ወዘተ ሰዎችን እና የተለያዩ እቃዎችን ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ የማድረስ እና የማመላለስ አገልግሎት የሚሰጡት በየብስ /በመሬት/ ላይ ነው፡፡

ስለዚህ በመሬት ላይ የተሰሩ መንገዶችን ወይም ሀዲዶችን በመጠቀም የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡት መሳሪያዎች የየብስ ትራንስፖርት ተብለው ይታወቃሉ፡፡

### <u>2. የአየር ትራንስፖርት አግልገሎት</u>

የአየር ትራንስፖርት የሚባለው የተለያየ መጠን ያላቸው አውሮኘላኖች እና ሄሊኮፐተሮች በተገጠመላቸው የፐሮፔለር ወይም የጀት ከፍተኛ የሞተር ሀይል ተጠቅመው በሰማይ ላይ በመጓዝ ለሰውና ለእቃ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ነው፡፡



ስእል 46
አይሮፕላን

በአገራችን ትልቁ የአየር ትራንስፖርት መነሻና መድረሻ ቦታ ቦሌ ኢንተርናሽናል አይሮፕላን ማረፊያ ተብሎ የሚታወቀው ሲሆን፣ የሚገኘውም አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ ሌሎች አውሮፕላን ጣቢያዎች በአገራችን የተለያዩ ከተሞች ውስጥ የተሰሩ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ መቀሌ፣ አክሱም፣ ጐንደር፣ ባህር ዳር፣ ላሊበላ፣ ድሬደዋ፣ ጎዴ አርባምንጭ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ከየትኛውም የትራንስፖርት ዓይነት እጅግ ፈጣን የሆነው የአየር ትራንስፖርት ሲሆን አገሮች እርስ በርስ የሚያደርጉት የዜጐች ግንኙኝነት እና ንግድ እንዲጠናከር የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ሆኖ ይገኛል፡፡

ግዙፍና በርካታ መጠን ያላቸው ዕቃዎችን፤ ለምሳሌ ቡና፣ ቆዳና ሌጦ፣ እንደ ማሽነሪ ያሉ የፋብሪካ ምርቶች በአየር ትራንስፖርት አይጓጓዙም፡፡ ምክንያቱም ለአየር ትራንስፖርት የሚከፈለው ወጪ ከሌሎቹ የትራንስፖርት አገልግሎቶች ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን በጉዞ መራዘም ምርቱ የሚበላሽ ከሆነ ወይም ውድ የሆኑ ምርቶች፣ ለምሳሌ መድሐኒት፣ አበባ፣ ፍራፍሬ የመሳሰሉ ፈጥነው ለተጠቃሚው መድረስ ስላለባቸው ከአገር አገር የሚጓጓዙት በአየር ትራንስፖርት ነው፡፡

በመሆኑም የአየር ትራንስፖርት ከሁሉም የትራንስፖርት ዓይነቶች ፈጣኑ ሲሆን ሰዎችንና ምርቶችን በፈጠነ ጊዜ በማጓጓዝ ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጠ ያለ የትራንስፖርት ዓይነት ነው፡፡

3. <u>የውሃ ላይ ትራንስፖርት</u>

በውቅያኖስ፣ በባህር፣ በሀይቅና በትላልቅ ወንዞች ላይ በመርከብ ወይም በጀልባ አማካኝነት የሚሰጥ የትራንስፖርት ዓይነት የውሃ ላይ ትራንስፖርት ተብሎ ይጠራል፡፡

የአንድ አገር የግብርና ውጤትም ሆነ፣ የኢንድስትሪ ውጤት የሆኑ ነገሮች ራቅ ወደ አሉ ሌሎች አገሮች የሚጓጓዙት ወደብ ላይ በመርከብ ተጭነው ነው፡፡ ወደብ የሚባለው መርከቦች ዕቃ የሚጭኑበት ወይም የጫኑትን የሚያራግፉበት ከባህሩ ወይም ከውቅያኖሱ ዳር ላይ ለዚሁ አገልግሎት የተሰራ ቦታ ነው፡፡

ብዙ መኪናዎች ወይም አውሮፕላኖች ሊጭኑት የሚችሉትን ሰው እና ዕቃ አንድ መርከብ በአንድ ጊዜ ሊጭን ይችላል። ትልቅ የሚባለው መርከብ ከአንድ የኳስ ሜዳ ርዝመቱ የማይተናነስ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ እስከ ሶስት ሺህ ሰዎችን መጫን የሚችሉ መርከቦች ተሰርተው አገለግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። ሰዎች የውሃ ላይ ትራንስፖርት የማጠቀሙት ከፍተኛ መጠን ያላቸውን ምርቶች ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር በአንድ ጊዜ ለማመላለስ ስለሚያስችላቸው ነው።

ኢትዩጵያ ምርቶቿን ወደ ውጭ የምትልከው፣ ወይም ከውጭ አገር የተሠሩ የፋብሪካ ምርቶችን ወደ አገር ውስጥ የምታስገባው፣ በየትኛው ወደብ በኩል ነው?

ተማሪዎች መልሱን ካላወቃችሁ መምህራችሁን ጠይቋቸው።

በኢትዮጵያ የውሃ ላይ ትራንስፖርት አልተስፋፋም። በአገራችን ካሉት በርካታ ሀይቆች ውስጥ የጣና ሀይቅ የተሸለ የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል። ከባህርዳር እስከ ጐርጐራ ድርስ ህዝብ እና እቃ የማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጡ በርካታ መካከለኛ ጀልባዎች አሉት። በዝዋይ፣ በአዋሳ፣ በላንጋኖ ሀይቆች ሰዎችን በውሃ ላይ የሚያንሸራሽሩ ጀልባዎች የመዝናኛ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

አብዛኞቹ የአገራችን ወንዞች ለትራንስፖርት አገልግሎት አመቺነት የላቸውም። ፏፏቴዎችና ሸለቆዎች የሚበዙበቸው በመሆናቸው ለትራንስፖርት አገልግሎት አያመቹም። በአገራችን ለውሃ ትራንስፖርት አመቺነት ያለው ወንዝ ባሮ ሲሆን ይህ ወንዝ የሚገኘው በጋምቤላ ብሔራዊ ክልል ውስጥ ነው። ይህ ወንዝ ሜዳማ በሆኑ አካባቢዎች በመጓዝ ሱዳን ውስጥ ከነጭ አባይ ጋር የሚገናኝ ሲሆን የውሃ ትራንስፖርት አገልግሎት ሲሰጥ እንደነበር ይታወቃል።

<u>የተግባር ጥያቄዎች</u>
<u>ለነዚህ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ሰጡ።</u>

1. ስንት ዓይነት የትራንስፖርት ዓይነቶች አሉ? ለምን በተለያዩ ሰሞች ይጠራሉ?
2. ከአየር ትራንስፖርት እና ከውሃ ትራንስፖርት የበለጠ ፈጣኑ የቱ ነው?
3. በአገራችን በብዛት ተግባር ላይ የዋለው የትራንስፖርት ዓይነት የትኛው ነው?
4. ስለየብስ ትራንስፖርት የምታውቁትን ለመምህራችሁ ግለፁ?
5. ከሁሉም የትራንስፖርት ዓይነቶች ፈጣኑ የትኛው ነው?
6. የአየር እና የውሃ ትራንስፖርት አደጋ ሊኖረው ይችላል ብላችሁ ታስባላችሁ?
7. የውሃ ትራንስፖርት በአገራችን ውስጥ ሊያድግ ያልቻለው በምን ምክንያት ይመስላችኋል? የተለያዩ ሰዎችን በመጠየቅ እና የተማራችሁትን መሰረት በማድረግ መልስ ስጡ።
8. የውሃ፣ የየብስና የአየር ትራንስፖርት ያላቸው ጥቅም እና ልዩነት ምንደነው?
9. እናንተ ባላችሁበት አካባቢ የአውሮፕላን ማረፊያ አለ?
10. አውሮፕላኖች እንዴት የሚበሩ ይመስላችኋል?

## 16. የብስክሌት ትራንስፖርት ጥቅም

በአብዛኞ የሀገራችን ከተሞች ብስክሌት ለትራንስፖርት አገለግሎት ሲውል ይታያል፡፡ ብስክሌቶች በብዛት አገልግሎት ላይ ውለው ከሚገኙባቸው ከተሞች የሚጠቀሱት የሚችሉት ባህር ዳር፣ አዋሳ፣ ናዝሬት፣ ሻሸመኔ፣ መቀሌ ጥቂቶቹ ሲሆኑ በእነዚህ እና በሌሎች ከተሞችም በርካታ ሰዎች ወደ ስራ ወይም ወደ ት/ቤት ለመጓጓዝ ይጠቀሙባቸዋል፡፡

አናንትም ብስክሌት የምታሽከረክሩ ከሆነ አደጋ እንዳይደርስባችሁ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባችኃል፡፡

ብስክሌት በምትነዱበት ጊዜ ማድረግ ያለባችሁ ጥንቃቄ

አደጋ በማያስከትል ሁኔታ የብስክሌት ተጠቃሚ ለመሆን ቀጥሎ የተጠቀሱትን ነጥቦች ማስተዋል ይኖርባችኋል፡፡ እነዚህም፡-

- ✓ ንቁ መሆን፤ በአካባቢያችን ምን እንዳለ ማዳመጥና መመልከት፣
- ✓ በመኪና መንገድ ውስጥ በምትነዱበት ጊዜ ወዲያ ወዲህ እያደረጉ መንገዱን ሞልቶ አለመንዳት፣ ተገቢውን መስመር ይዞ ቀጥ አድርጎ ማሽከርከር፣
- ✓ የመንገዱን የድንጋይ ወይም የኮንክሪት ጠርዝ ተጠግቶ አለመንዳት፣ ጠርዙና የብስክሌቱ ጎማ ተጋጭተው አደጋ ሊያስከትል ስለሚችል፡፡
- ✓ መንገዱ ዳር የቆሙ መኪናዎች አጠገብ ስትደርሱ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባችኋል፡፡ ምክንያቱም ከመኪናው መውረድ የፈለጉ ሰዎች ባልታሰበ ሁኔታ በሩን በሚከፍቱበት ጊዜ ተጋጭታችሁ አደጋ ሊፈጠር ይችላል፡፡
- ✓ ከፊት ለፊታችሁ ካለው ተሽከርካሪ ተገቢውን እርቀት ጠብቆ መንዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ ሜዳማ በሆነ መንገድ 4 ሜትር፣ ቁልቁለት ላይ 10 ሜትር ያህል፣ በክረምት ደግሞ ከዚህ የበለጠ ርቀት ይዞ መንዳት ሊፈጠር የሚችለውን አደጋ ሊቀንስ ይችላል፡፡
- ✓ በአንድ ጊዜ ፍሬን መያዝ አደጋ ሊያስከትል ስለሚችል መስቀለኛ መንገድ ከመድረሳችሁ በፊት ፍጥነታችሁን በመቀነስ ዝግ ብላችሁ መንዳት፡፡
- ✓ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ ለመታጠፍ ስትፈልጉ እጃችሁን ወደ ምትዞሩበት አቅጣጫ በመዘርጋት የምትዞሩበትን አቅጣጫ ማመልከት፡፡
- ✓ ቀጥ ብላችሁ እየተጓዛችሁ ቆይታችሁ መታጠፍ ስትፈልጉ አደጋ የሚያደርስ ነገር መኖር አለመኖሩ ዞር ብላችሁ በጥንቃቄ መመልከት፡፡
- ✓ ከፊት ለፊት የምታዩት ነገር አደጋ ሊያመጣብን ይችል ይሆናል ብላችሁ ስትገምቱ ለማስጠየቂያ እንዲረዳ የብስክሌቱን ደውል መደወል አለባችሁ፡፡
- ✓ በምታሽከረክሩበት ጊዜ እግረኞች መንገድ እያቋረጡ ከሆነ ቅድሚያ ለእግረኞች በመስጠት አደጋ እንዳታስከትሉ ወይም አደጋ እንዳይደርስባችሁ ተጠንቅቃችሁ አሳልፉ፡፡
- ✓ ማሽከርከሩን አቋርጣችሁ ብስክሌታችሁን ልታቆሙ የምትፈልጉ ከሆነ የፊትና የኃላ ፍሬኑን ቀስ በቀስ በእኩል ሁኔታ መያዝ ይኖርባችኃል፡፡
- ✓ መንገዱ አንሸራታች ከሆነ፣ እርጥበት ካለው፣ አደጋ እንዳያደርስብን ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል፡፡
- ✓ ብስክሌት በምታሽከረክሩበት ጊዜ የአደጋ መከላከያ ጠንካራ ባርኔጣ "ሄልሚት" ብታደርጉ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡
- ✓ በምሽትና በጭጋጋማ የአየር ሁኔታ፣ ብስክሌት የምትነዱ ከሆነ ነጣ ያሉ እና አንፀባራቂ ልብሶችን በመልበስ ከሩቅ እንድትታዩ ስለሚያደርግ ሊፈጠር የሚችለውን አደጋ ሊያስቀር ይችላል፡፡
- ✓ ከጓደኞቻችሁ ጋር ሆናችሁ በብስክሌት ስትሄዱ ጎን ለጎን ሳይሆን ተከታትላችሁ መንዳቱ ሊደርስ የሚችለውን የመኪና አደጋ ሊቀንስ ይችላል፡፡
- ✓ ብስክሌቶች በምሽት ጊዜ ከሩቅ እንዲታዩ ተገቢ አንፀባራቂ ምልክቶችና መብራቶች አሏቸው፡፡ እነዚ መሳሪያዎች በአግባቡ መስራታቸውን እርግጠኞች መሆን ይገባችኋል፡፡

## ብስክሌት የሚነዱ ሰዎች የሚፈጽሟቸው አደገኛ ተግባራት

ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሆኖ ጐን ለጐን ብስክሌት መንዳት አደገኛ ነው፡፡ መንገዱ ስለሚጣበብ ለሌሎች ተሽከርካሪዎች ችግር ይፈጥራል፡፡ በዚህ ምክንያት መገጨት ሊኖር ይችላል፣ ወይንም ብስክሌተኞቹ እርስ በርስ ተጋጭተው አደጋ ሊፈጥሩ ስለሚችሉ ይህ ሁኔታ አደገኛ ተግባር ተደርጐ ይታያል፡፡

አንዳንድ ብስክሌት አሽከርካሪዎች ዳገታማ ቦታዎችን ለመውጣት እንዲችሉ በአንድ እጃቸው የሚከተሉትን መኪና በእጃቸው በመያዝና እንዲጐትታቸው በማድረግ ብስክሌት ሊያሽክረክሩ ይሞክራሉ፡፡ ይህ በራሱ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ተግባር ነው፡፡

አልፎ አልፎ የሚታይ ቢሆንም አንዳንድ ብስክሌት አሽከርካሪዎች ብስክሌት እያሽከረከሩ ሌላ ብስክሌት በአንደኛው እጃቸው በመያዝ እየጐተቱ ሲሄዱ ይታያሉ፡፡ ይህም አደገኛ ተግባር ነው፡፡

ብስክሌት የሚነዳው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በፍጥነትና ያለድካም ለመጓጓዝ በመፈለግ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ልጆች በሚጓዙ ሰዎችና መኪናዎች መካከል እየተሽለኮለኩ ሲሽቀዳደሙ ይታያል፡፡ ይህ ሁኔታ አደገኛ ተግባር መሆኑን መረዳት ይኖርባችኋል፡፡

ሌላ ሰው በማፈናጠጥ ብስክሌት መንዳት በራሱ የሚፈጥረው አደጋ ይኖራል፡፡ በተፈናጠጠው ሰው ተሰተካክሎ አለመቀመጥ የብስክሌቷ ሚዛን ስለሚያጋድል አደጋ እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆን ስለሚችል ተግባሩ ለአደጋ እንዳያጋልጥ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል፡፡

በምሽት ጊዜ በመንገድ ላይ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎች መብራት መጠቀም ይገባቸዋል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ብስክሌቶች መብራት የላቸውም፡፡ ሆኖም በምሽት ሲሽከረከሩ ይታያሉ፡፡ ይህ ተግባር አደገኛ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል፡፡

## ብስክሌታችሁን ስታቆሙ ልትከተሉት የሚገባው ተግባር

- ✓ ብስክሌታችሁን ስታቆሙ የእግረኞች መተላለፊያ መንገድ በማይዘጋ ሁኔታ ግድግዳ አስደግፎ ማቆም፡፡
- ✓ ገጠር አካባቢ ከሆነ የመንገዱን ጠርዝ አስይዞ ማቆም ይቻላል፡፡
- ✓ የብስክሌቶች ማቆሚያ የተለየ ቦታ ካለ እዚያ ላይ ማቆም ተመራጭነት ያለው ተግባር ነው፡፡

ከዚህ ውጭ ብስክሌቶቻችሁን መንገድ ላይ ማቆም በንብረታችሁም ሆነ በሌሎች መንገድ ተጠቃሚዎች ላይ አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡

## የክፍል ውስጥ ተግባራት

1. እነዚህ የመንገድ ምልክቶች ምን ማለት እንደሆኑ ግለፁ?





ስእል 47

2. ብስክሌት እየነዳችሁ ቀይ መብራት ቢያስቆማችሁ ከስር ከተዘረዘሩት ነጥቦች ውስጥ የተጠቀሱትን ነገሮች በምን ዓይነት ቅደም ተከተል ትፈጽማላችሁ?

   - ✓ የፍሬቻ መብራት ማብራት
   - ✓ በአንድ እግርህ መሬት መርገጥ
   - ✓ ፍሬኑን መልቀቅ
   - ✓ ፍጥነት መቀነስ
   - ✓ ፍሬን መያዝ

3. የትኞቹ ብስክሌተኞች አደገኛ አነዳድ ተጠቅመዋል? ለምን?



አደገኛ የብስክሌት አነዳድ



ትክክለኛ የብስክሌት አነዳድ

ስእል 48

ብስክሌት ስትነዱ ማድረግ ያለባችሁ ጥንቃቄ

1. ከጓደኞቻችሁ ጋር ሆናችሁ ብስክሌት የምትነዱ ከሆነ ጐን ለጐን ሆናችሁ መንዳት የለባችሁም፡፡
2. የመንገዱን ጠርዝ ተጠግቶ አለማሽከርከር፤ ነገር ግን ከጠርዙ ሳትርቁ በትንሹ ወደ መንገዱ ውስጥ ገባ ብላችሁ መንዳት፡፡
3. የመንገድ ላይ ምልክቶችንና የትራፊክ መብራቶችን አክብሮ ማሽከርከር፡፡
4. የቆመ መኪና አጠገብ ስትደርሱ በሮቹ ሊከፈቱ ስለሚችሉ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
5. ብስክሌታችሁን እያሽከረከራችሁ ስትሄዱ አቅጣጫ ከመቀየራችሁ በፊት ወደየት እንደምታዞሩ እጃችሁን በመዘርጋት ምልክት ማሳየት ይኖርባችኋል፡፡
6. የመኪና መንገዱን የሚሻገሩ እግረኞች ካሉ ቆም ብለችሁ አሳልፏቸው
7. ፍሬን ከያዛችሁ ሁለቱንም (የፊትና የኃላ ፍሬኖችን) በአንድነት ግን በዝግታ መያዝ ይኖርባችኋል፡፡
8. የአደጋ መከላከያ ባርኔጣ ማድረግ መወሰድ ካለባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች ውስጥ አንዱ ስለሆነ መጠቀም ይኖርባችኋል፡፡

## 17. አርቆ የሚመለከት ካሰበበት ይደርሳል

ድርፉጮ የዩንቨርስቲ ትምህርቱን ጨርሶ ተመረቀ፡፡ ጥሩ ውጤት ስለነበረው ስራ ያገኘው ወዲያውኑ ነበር፡፡ ትጉህና ጠንቃቃ መሆኑን በስራው በማስመስከሩ በመስሪያ ቤቱ ትልቅ ሃላፊነት ተሰጠው፡፡ ለስራው ማከናወኛ የሚሆን መኪና ስለተሰጠው የመኪና አነዳድ ትምህርት በመማር መንጃ ፍቃድ አውጥቶ የተሰጠውን መኪና ራሱ ያሽከረክራል፡፡

ገጠር ካሉት ዘመዶቹ አንዱ የሆነው አጐቱ መሞቱን የሰማው በድንገት ነበር፡፡ የመስሪያ ቤቱ ሀላፊ ፍቃድ እንዲስጡት ጠየቀ፡፡ በትጉህ ሠራተኛነቱ የሚወዱት አለቃው የመ/ቤቱን መኪና ለጉዞው እንዲጠቀም ፈቀዱለት፡፡

ከተወለደበት መንደር ሲደርስ በርካታ ስዎች የቀብሩን ስነስርዓት ለማስፈፀም ተገኝተው ነበር፡፡ አንድ ዘመናዊ መኪና ወደ እነሱ አቅጣጫ ሲመጣ በማየታቸው "የምን መኪና ነው?" በማለት ይመለከቱ ነበር፡፡ መኪናው አጠገባቸው ሲደርስ ቆመ፡፡

"እንዴ ድርፉጮ ነው፣ የኛው ልጅ ድርፉጮ ነው፣ ይህችን የመሰለች ቆንጆ መኪና እያሽከረከረ የመጣው!" እያሉ እርስ በርስ ይነጋገሩ ነበር፡፡

ልጆቻቸው በተለያዩ ጊዜያት በመኪና አደጋ የሞቱባቸው ወላጆች እና ዘመዶቻቸው የእነሱም ልጆች እንደ ድርፉጮ ጠንቃቃ ባለመሆናቸው የደረሰባቸውን የሞት አደጋ እና የአካል መጉደል አደጋ እያስታወሱ አዘኑ፡፡

ድርፉጮ ዘመዶቹን ሲጠያይቅ ሰነበተ፡፡በአካባቢው ወደ ተሰራው ት/ቤት በመሄድ ተማሪዎች ካሰቡት ለመድረስ የሚችሉት ከማንኛውም አደጋ የሚያመጡ ነገሮች ጠንቃቆች ሆነው ራሳቸውን ሲጠብቁ መሆኑን አስተማራቸው፡፡ብዙልጆች እንደ ደርፉጮ ተግተው በመማር ራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን ለማስደሰት እንደሚችሉ በማሰብ ትጉህና ጠንቃቃ መሆን ጀመሩ፡፡

**የመለማመጃ ጥያቄዎች**
**እነዚህን ጥያቄዎች እያነሳችሁ ተወያዩ**

1. የደህንነት ቀበቶ ማሰር ምን ጥቅም አለው?
2. መኪናዎች ፍሬናቸው ቢያዝም የሚንሸራተቱት በምን ምክንያት ነው?

**ተግባር ሁለት**
**ትክክል የሆነውን ሀሳብ እውነት፣ ትክክል ያልሆነውን ሀሳብ ስህተት በሉ**

1. ድርፉጮ መኪና የሚነዳው መንጃ ፈቃድ ሳይኖረው ነበር፡፡
2. የመኪና መንገድ መብራት አረንጓዴ ሲያበራ መኪናዎች ይቆማሉ፡፡
3. ድርፉጮ ኃላፊነት የተሰጠው መንጃ ፈቃድ ስላለው ነበር፡፡
4. ለትምህርት ትጉህ መሆን፣ አደጋ እንዳይደርስብን ጠንቃቃ ሊያደርገን ይችላል፡፡

**ተጨማሪ ተግባር**

1. ባለፉት የመጽሐፉ ክፍሎች ያነበባችሁትን የድርፉጮን ታሪክ በማስታወስ ለመምህራችሁ እና ለወላጆቻችሁ ንገሯቸው፡፡
2. እናንተም እንደ ድርፉጮ ጠንቃቆች እና ትጉሆች ለመሆን ዝግጁ መሆናችሁን ግለፁላቸው፡፡

## <u>ምስጋና</u>

ይህንን የመኪና መንገድ አጠቃቀም መማሪያ የተማሪው ማጣቀሻ መጽሐፍ ለማዘጋጀት የተባበሩኝ ወገኖች በርካታ ናቸው፡፡ መጽሐፉ ሊይዘው የሚገባውን ይዘት ከጠቃሚ መረጃዎችና ሙያዊ ምክር ጋር የብሔራዊ የመንገድ ደህንነት አስተባባሪ ጽ/ቤት የስራ ኃላፊዎች የሆኑት አቶ አበበ አስራት እና አቶ ጉደታ ረጋሳ ስራው ተገቢውን አቅጣጫ እንዲይዝ ከፍተኛ እገዛ ያደረጉልኝ ሲሆን፣ ከአዲስ አበባ ትራፊክ ቁጥጥርና አደጋ ምርመራ ፖሊስ መምሪያ ጋር በመተባበር የተማሪ ትራፊኮችን በአዲስ አበባ ት/ቤቶች በማቋቋም ሰፊ ልምድ ያላቸው ሻምበል አበበ ዓለማየሁ ለቃለ መጠይቅ ፍቃደኛ በመሆን ያመለከቱት አቅጣጫ እና ለስራው ስኬት ያሳዩት ቅን ፍላጐት እና ማበረታታት የሚዘነጋ አይሆንም፡፡

ረቂቁን በመገምገምና ገንቢ አስተያየቶችን ለሰጡኝ ለሻለቃ ሙላቱ በፍርዱና ለአቶ ተገኜ መንግስቱ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው፡፡ በመጽሐፉ ዝግጅትም ግንዛቤ የሚሰጡ ስዕሎችን ለሳሉልኝ ለወጣት አብደላ አብዱራህማን፣ ሜላት ካህሳይ እና ሌሎችም የትየባ ስራውን ሳይሰለቹ ለሰሩትና ይህ ማጣቀሻ መጽሐፍ እንዲዘጋጅ አቅዶ ተግባራዊ አንዲሆን ላደረገው የብሔራዊ የመንገድ ደህንነት አስተባባሪ ጽ/ቤት፣ ለባለቤቴ፣ ለልጆቼ እና ድጋፍ ላደረጉልኝ ሁሉ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው፡፡

**አዘጋጁ**